# — ክፍል አምስት —

# መንፈስ ቅዱስ
# በአማኞች ውስጥ

# 18

# የመንፈሳዊ ስጦታዎች ባሕርይ

## 1. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም

በክርስቶስ ኢየሱስ ባመነ ሰው መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ፥ የዚህን ርእስ ያህል ከሕይወቱ ጋር ግንኙነት ያለውና ለአሁኑ ጊዜ በጣም አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ጥቂት ነው። ትክክለኛ የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም እና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ግንዛቤ አስፈላጊዎች ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ሥራን በሚገባ መረዳት ግን ከእነዚህ ይበልጥ አስፈላጊነት አለው። ምክንያቱም ከአማኙ ማንኛውም ዓይነት ኑሮና ልምምድ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ስለሆነ ነው። የአማኙ መቀደስ፥ መንፈሳዊ ማስተዋል፥ ዋስትና፥ አገልግሎት፥ ጸሎት እና አምልኮ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የሚመነጩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ስለሚያከናውነው ሥራ የሚናገረውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚገባ መረዳት መንፈሳዊ በረከትና ጥቅም የሚገኝበትን መንገድ ይከፍታል። በዚሁ መሠረት ይህን የሚያስተምሩ እና የሚሰብኩ ሁሉ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በጥልቅ ጥናትና ጥንቃቄ ማወጅ ይጠበቅባቸዋል።

መንፈሳዊ ስጦታዎችን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን ከመነሻው ጀምሮ በሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦች ተቸግራለች። ከመጀመሪያው፥ የቆሮንቶስ መልእክቶች እንደሚያሳዩት፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ያለ አግባብ መጠቀም ታይቶ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደምናየው ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሚመለከት እጅግ በዛ ያሉና የተለያዩ ትምህርቶች ተከሥተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ስጦታዎች የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በመወሰን ረገድ እና ለቤተ ክርስቲያን ፍሬያማነት ያላቸው አስፈላጊነት በቂ ትኩረት አልተሰጠውም። ተገቢና ተመጣጣኝ የሆነው ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው በቀር ሌሎች ነገሮችን መጨመር፥ አስፈላጊ ጉዳዮችን ከመተው የተሻለ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉ መገለጦች ውስጥ የአንዳንዶቹ እውነት ሌሎች ከሚያስገነዝቡት ልዩ መልእክት አንጻር አስፈላጊነታቸው የላቀ ነው። ከዚህ የተነሣ በመጀመሪያ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ባሕርይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልንመረምር ይገባል። ይህ ወዲያውኑ እውነቱን ከሐሰት ይለይልናል። በሁለተኛ ደረጃ፥ በዘመነ ክርስትና ሁሉ በአገልግሎት ላይ ያሉትን ስጦታዎች ለማወቅ መመርመርና መተንተን አለብን። እነዚህ ስጦታዎች

ለሰዎች ያልተሰጡ ቢሆን ኖሮ፥ የዳኑ ሰዎች እንኳን እግዚአብሔርን ማገልገል ይሳናቸው ነበር። በሦስተኛ ደረጃ፥ በሐዋርያት ዘመን የነበሩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከሐዋርያት ዘመን በኋላ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ መካተት አለመካተታቸውን ለመወሰን መጠናት አለባቸው። በሌላ አባባል፥ በጊዜያዊነት ለተለየ ዓላማ ለሐዋርያት የተሰጡ፥ እነርሱ ካለፉ በኋላ ግን የሌሉ አንዳንድ ስጦታዎች ነበሩን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መቻል አለብን።

## 2. የመንፈሳዊ ስጦታዎች አጠቃላይ ባሕርያት

መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ የሚያከናውነውን ሥራ በግልጥና በጥንቃቄ በተብራሩ ሁለት ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን። በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ስጦታዎች፥ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በተቀዳሚነት መጠናት አለባቸው። በሁለተኛ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ አማኙን በመሞላት ረገድ ያለውን እውነት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ሁኔታዎቹና ውጤቶቹ መቅረብ አለባቸው። ሁለቱ አቅጣጫዎች በአንድ ላይ የእያንዳንዱን አማኝ ስፍራና ፍሬያማነት ይወስናሉ።

ይህን አሳብ ለመግለጥ አዲስ ኪዳን የተጠቀመባቸው የተለያዩ ቃላት ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተፈጥሮ የሚናገሩት አላቸው። ስለ ስጦታዎች የሚናገረው ዋና የአዲስ ኪዳን ጥቅስ የሚገኘው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ነው። በዚህ ክፍል የመግቢያ ጥቅስ ላይ 'ኒዩማቲኮን' ['pneumatikon'] የሚለው ቃል የመንፈስ ቅዱስ ነገሮች ይኸውም መንፈሳዊ ስጦታዎች በማለት ዋናውን አሳብ ገልጦት እናገኛለን። ቃሉ የሰውን ትኩረት፥ ምንጩ ወደሆነው መንፈስ ቅዱስ፥ እንዲሁም ወደ እነዚህ ስጦታዎች የሚስብ ነው። ከአገባቡ እንደምንረዳው ይህ ቃል 'ከሪስማቶን' ['charismaton'] በነጠላ ቁጥር "የጸጋ ስጦታ" የሚል ትርጉም አለው። የብዙው ቁጥሩ ከመንፈሳዊ ስጦታዎች አንጻር ሲታይ ደግሞ፥ "አንዳንድ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ይችሉ ዘንድ የሚሰጣቸው በተለምዶ ከሚታወቀው በላይ የሆነ ኃይል ነው። ይህን ኃይል ሊቀበሉ የቻሉት መንፈስ ቅዱስ በነፍሳቸው በሚሠራው መለኮታዊ ጸጋ ምክንያት ነው።" ይህ ቃል ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች መሠረትና ባሕርያቸው ያስረዳል። መንፈሳዊ ስጦታዎች ከጸጋ የተነሣ የሚሰጡ፥ ለኛ የማይገቡ፥ እና ኃይልና ሥራቸው ሙሉ ለሙሉ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ናቸው። ይህ አሳብ 'ድዶታይ' ['didotai'] በሚለው ግሥ አማካይነት ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶታል። ትርጉሙም መስጠት ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡7ቀ.)። እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከማንኛውም የተፈጥሮ ችሎታ የተለዩ ናቸው። በሁሉም አማኞች ከሚገኙት መንፈሳዊ ብቃቶች ጋርም

መምታታት የለባቸውም። መንፈሳዊ ስጦታዎች በባሕርያቸው ግላዊና ከእግዚአብሔር የሚመጡ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመንፈሳዊ ስጦታዎችና ስጦታው ባላቸው ሰዎች መካከል ልዩነቶች ይታዩ ይሆናል። ሁለቱ አሳቦች የማይነጣጠሉ ሲሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለግለሰቦች የተሰጠ ሰማያዊ ኃይልን ያመለክታሉ። ስጦታ ስላላቸው ሰዎች ስንናገር ደግሞ አካሉ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ያገለግሉ ዘንድ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ በቤተ ክርስቲያን ስላስቀመጣቸው ሰዎች እያመለከትን ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ያለው ዋና ትምህርት ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚናገር ሲሆን፥ ኤፌሶን 4፡11 ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎች ስላላቸው ሰዎች የሚናገር ክፍል ነው። ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና ለቤተ ክርስቲያን ስለተሰጡ ሰዎች የሚናገሩት እነዚህ ሁለት አሳቦች በዚህ ክፍል ጠበቅ ባለ ሁኔታ ተለይተው አልቀረቡም። ይሁን እንጂ ስጦታ ያላቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ወይም በክርስቶስ የሚሰጡ ሲሆኑ፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ግን የሦስተኛው የሥላሴ አካል ሥራ መሆናቸው ልብ መባል አለበት። የመንፈሳዊ ስጦታዎች ክልል በተለይ የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አካል ሲሆን፥ የአሁኑ ጥናታችን ቅድሚያ ትኩረትም በዚሁ ላይ የተመሠረተ ነው።

ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ዋና ቃል የሆነው 'ከሪስማ' አዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራ ይገኛል (ሮሜ 1፡11፤ 5፡15፥ 16፤ 6፡23፤ 11፡29፤ 12፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡7፤ 7፡7፤ 12፡4፥ 9፥ 28፥ 30፥ 31፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡11፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡14፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡6፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡10)። አብዛኛዎቹ ጥቅሶች ለዚህ ጉዳይ ማዕከላዊ በሆነው ዋና ክፍል፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ላይ ጥቂት ነገርን ብቻ ይጨምራሉ። በጴጥሮስ መልእክት ከሚገኘው አንድ ጥቅስ ሌላ፥ የቀሩት በሙሉ ጳውሎስ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከአንዳንድ አሳቦች ጋር የተጠቀሰውና 'ከሪስማ' ['charisma'] የሚለው ቃል፥ ያልተለመዱ ኃይሎች በመንፈሳዊ ስጦታዎች የተገለጡ መሆናቸውን የሚያመለክት አይደለም። ለምሳሌ በሮሜ 5፡15-16 ያለው ስጦታ የጽድቅ ሲሆን፥ በሮሜ 6፡23 ያለው ደግሞ የዘላለም ሕይወት ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ያለው ሉዓላዊ ዕቅድ አንዳንዶች እንዲያገቡ ሌሎች ደግሞ እንዳያገቡ ሲሆን፥ ይህም በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡7 እንደ ስጦታ ተጠቅሷል። በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ሰዎች ጸሎት ምክንያት የሚመጡ በረከቶች በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡11 እንደ ስጦታ ቀርበዋል። በሮሜ 1፡11 ጳውሎስ ለሮሜ ቤተ ክርስቲያን ስለተሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይናገራል። ይህም በእርሱ አገልግሎት ስለተገኙ ልዩ በረከቶች ወይም የተለየ መንፈሳዊ

ስጦታ ወይም ልዩ ኃይል ስለማግኘት የሚናገር ነው። እጆችን የመጫን ተግባር ትክክለኛ ትርጉም በእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎችን የማወቅ ጉዳይና በሙሉ ኃይል ተግባራዊ እንዲሆኑ የመለየት ጉዳይ ቢሆንም፥ ምናልባት ሐዋርያት በዚህ ሁኔታ ያልተለመደ ታላቅ ሥልጣን ሊኖራቸው እንደሚችል ለጢሞቴዎስ በተሰጠው መንፈሳዊ ስጦታ መመልከት እንችላለን (1ኛ ጢሞ. 4፡14፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡6)። ከሐዋርያት በኋላ ባለው ዘመን ግን መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመስጠት ከእግዚአብሔር በቀር የሚችል አለ ብሎ የሚያሳምን አሳብ የለም። ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚናገሩት ሌሎች ክፍሎች (ሮሜ 12፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡7፤ 12፡4፥ 9፥ 28፥ 30፥ 31፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡10) የጸጋው መግለጫዎች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር የተሰጡ ተአምራዊ ኃይሎችንና ግለሰቡ በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው ቦታ የሚያበረክተው አገልግሎት እንዲሳካ የሚያደርጉ ናቸው።

## 3. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ልዩ ባሕርያት

*መንፈሳዊ ስጦታዎች እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የሚሰጣቸው ናቸው።* ከዚህ አንጻር ስናያቸው ሰው ስለፈለገ የሚያገኛቸው አይደሉም። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናን ለአንዳንድ ስጦታዎች ከፍተኛ ስፍራ ሰጥተው በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ስጦታዎች ግን ቸል በማለታቸው፥ "ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ" በማለት ጽፎላቸዋል (1ኛ ቆሮ. 12፡31)። በሌሎች መልእክቶቹ ውስጥ ግን መንፈሳዊ ስጦታን ስለመፈለግ የሚያበረታታ ነገር ሲጽፍ አናየውም። ስጦታዎች በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ እንጂ በሰው መንፈሳዊነት ላይ አይደገፉም። አንድ ክርስቲያን ብዙ መንፈሳዊ ስጦታዎች ኖረውት ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አያስገዛ ይሆናል፤ በሌላ በኩል ትንሽ መንፈሳዊ ስጦታ ኖሮት ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን ያስገዛ ክርስቲያን ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ራሳችንን የመስጠት ደረጃ የግድ የሚኖሩንን የመንፈሳዊ ስጦታዎች መጠን አይወስንም ወይም በሌላ አገላለጥ፥ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመስጠታችንን ደረጃ የመንፈሳዊ ስጦታዎቻችን መጠን አይወስነውም። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አባባል፥ "ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። በእርግጥ ስጦታዎች ያሉት ሰው፥ በስጦታዎቹ በሚገባ ለመጠቀም፥ መንፈሳዊ ሕይወቱ በሚገባ መስተካከል አለበት። ነገር ግን መንፈሳዊነት በራሱ መንፈሳዊ ስጦታዎችን አያመጣም።

መንፈሳዊ ስጦታዎች ሰው በደኅንነቱ ጊዜ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ ነው ወይስ ከዳነ በኋላ የሚመጣ? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን ጉዳይ በሚመለከት ግልጥ የሆነ መልስ አይሰጡም። ነገር

ግን በዳግም ልደት ጊዜ ከሚሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንጻርና በዚህም ሳቢያ በክርስቶስ አካል ውስጥ በሚሰጠው አዲስ ስፍራ ምክንያት፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች ወዲያውኑ ባይታዩና ሰውዬው ሲለማመዳቸው ባንመለከትም እንኳ፥ የሚሰጡት በዳግም ልደት ጊዜ ነው ማለት ተገቢ ነው። በዚህ መሠረት አሰጣጣቸው በጥምቀት አፈጻጸም ውስጥ ባይጨመርም እንኳ መንፈሳዊ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሥራ ውስጥ ሳይገኙ አይቀሩም። አንድ ሕፃን ባይገነዘበውም ተፈጥሯዊ ስጦታዎች በውስጡ እንዳሉ ሁሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችም ዳግም በተወለደ ሰው ሕይወትም ውስጥ እንዲሁ ናቸው። ስለዚህ በፍጥረታዊም ሆነ በመንፈሳዊ ክልል ስጦታዎችን በሚገባ የመጠቀም እና የማጎልበት እንጂ ተጨማሪ ስጦታዎችን የማግኘት ጉዳይ አይደለም።

*እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉት።* እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አባባል፥ "መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ጥቅም ይሰጠዋል" (1ኛ ቆሮ. 12፡7)፥ ደግሞም "ይህን ሁሉ ግን ያ አንድ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። ክርስቲያኖች ሁሉ "የክርስቶስ አካላት ናቸው" (1ኛ ቆሮ. 12፡27)፤ "ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን" (ሮሜ 12፡5)። ምንም ያህል ስጦታው ትንሽ፥ ወይም ዝቅተኛ ስፍራ ላይ ይሁን እያንዳንዱ ክርስቲያን ለክርስቶስ አካል በጣም አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፥ "ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው" (1ኛ ቆሮ. 12፡22)። በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር መለኮታዊ ዓላማ ያለው ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም ይህን ዓላማ ለማከናወን የሚሰጡ ናቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያን እግዚአብሔር ባስታጠቀው ስጦታ መሣሪያነት አገልግሎቱን ይፈጽም ዘንድ ሊወጣው የሚገባ ኃላፊነት ነው በፊቱ የቀረበለት (1ኛ ጴጥ. 4፡10)።

*ስጦታዎች በጠቀሜታ ይለያያሉ።* በክርስትና እምነት የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆን የተነሣ ሁሉም እኩል የሆነ መብት ቢኖረውም፥ እያንዳንዱ ያለው ስጦታ ግን እኩል አይደለም። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡28 በተጻፈው መሠረት፥ "እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጓል።" በተለያዩ ስጦታዎች ባሕርይ መሠረት አንዳንዶቹ ከሌሎቹ ይልቅ በጣም አስፈላጊና ውጤታማ ናቸው። ጳውሎስ የትንቢት ስጦታን፥ በልሳን ከመናገር ስጦታ ጋር እንዲህ በማለት አነጻጽሮታል፥ "ሁላችሁ

በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር፥ ትንቢት ልትናገሩ ግን ከዚህ ይልቅ እወዳለሁ" (1ኛ ቆሮ. 14፥5)፤ እንደገናም፥ "ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ" (1ኛ ቆሮ. 14፥19) ብሏል።

*መንፈሳዊ ስጦታዎችን መጠቀም ያለብን በፍቅር ነው።* 1ኛ ቆሮንቶስ 13 በሚሰጠው ምስክርነት መሠረት መንፈሳዊ ስጦታዎች ለታቀዱበት ጥቅም ይውሉ ዘንድ በፍቅር ልንገለገልባቸው ይገባል። መንፈሳዊ ስጦታዎች በራሳቸው ሰውን ትልቅ ክርስቲያን አያደርጉትም። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሆነው መለኮታዊ ፍቅር ቀስቃሽነት በተገቢው ከተጠቀምንባቸው ግን ውጤታማና ለእግዚአብሔር ክብር ፍሬ የሚያፈሩ ይሆናሉ።

*አንዳንድ ስጦታዎች ጊዜያዊ ናቸው።* ሌላው የመንፈሳዊ ስጦታዎች ገጽታ አንዳንድ ስጦታዎች የሚሰጡት ለተወሰነ ጊዜና ጥቅም ብቻ መሆኑ ነው። በአሁኑ ዘመን ባለች ቤተ ክርስቲያን በጥንትዋ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታዩ የነበሩ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሙላት አይታዩባትም። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ስጦታዎች የአሁኑ ስፍረ-ዘመንን ለይተው ያሳያሉ። የእያንዳንዱን ስጦታ ክፍፍል በሚመለከት በተናጠል በምናይበት ጊዜ ይህን በትኩረት እንመለከተዋለን።

*የመንፈሳዊና የተፈጥሮ ስጦታዎች ንጽጽር።* በጣም አስፈላጊ የሆነውን አጠቃላይ የመንፈሳዊ ስጦታ ገጽታ ለመመልከት በመንፈሳዊና በተፈጥሮ ስጦታዎች መካከል ያለውን ሁኔታ ማነጻጸር ይጠቅማል። እግዚአብሔር የተፈጥሮ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች የሚመርጥ ቢሆንም፥ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚገኙት በዳግም ልደት እንጂ በተፈጥሮ ልደት አለመሆኑ ግልጥ ነው። የመንፈሳዊ ስጦታዎች ብቃት በግለሰቦች ውስጥ ከደኅንነት በፊት የሚረጋገጥ አይደለም። መንፈሳዊ ስጦታዎች አዲሱን እንጂ አሮጌውን ፍጥረት አይመለከቱም። መንፈሳዊ ስጦታ የፍጥረታዊ ኃይል ተቀጥላ ወይም መስፋፋት ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር በሚጣጣም አኳኋን ግለሰቡን በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚያኖር ሰማያዊ ወይም ተአምራዊ ስጦታ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል ከፍተኛ ተፈጥሯዊ ችሎታ ካላቸው ይልቅ አነስተኛ ችሎታ ባላቸው ክርስቲያኖች ሲጠቀም በተደጋጋሚ ለማየት እንችላለን። እንግዲህ መንፈሳዊ ስጦታ በምቹ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ቢሆን ሰው ሊያደርግ የሚችለውን የሚያሳይ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በጸጋው የሚያደርገውን የሚያመለክት ነው።

# 19

# ቋሚ መንፈሳዊ ስጦታዎች

በአዲስ ኪዳን የተገለጡትን አሥራ ስድስት መንፈሳዊ ስጦታዎች በምንመረምርበት ጊዜ በስጦታዎቹ ባሕርያት መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት ግልጥ ይሆንልናል። ባለንበት ስፍረ-ዘመን ስጦታው ያላቸው ሰዎች በግልጥ ሲለማመዱት እንደምንመለከተው፥ አንዳንዶቹን ስጦታዎች የዛሬይቱም ቤተ ክርስቲያን የምትለማመዳቸው እንደሆኑ እናያለን። ዛሬም አንዳንድ ሰዎች የሚከተሉት ስጦታዎች እንዳሏቸው የሚያጠራጥር አይደለም። 1. የማስተማር ስጦታ፥ 2. የመርዳት ወይም የማገልገል ስጦታ፥ 3. የአስተዳደር ወይም የአገዛዝ ስጦታ፥ 4. የወንጌላዊነት ስጦታ፥ 5. የመጋቢነት ስጦታ፥ 6. የማጽናናት ወይም የመምከር ስጦታ፥ 7. የመለገስ ወይም የመስጠት ስጦታ፥ 8. ምሕረት የማድረግ ስጦታ፥ 9. የእምነት ስጦታ።

ከነዚህ በተነጻጻሪነት፥ በተናጠል በምናጠናቸው ጊዜ ከግል ሁኔታቸው እንደምንረዳው አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ቢሆኑም ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ግን የሚታዩ አይመስሉም። አንዳንድ የእምነት ክፍሎች እነዚህ ስጦታዎች አሁንም በመሥራት ላይ እንደሆኑ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ በስጦታዎቹ በመጠቀም ረገድ የሚታየው የጥራት ጉድለት የቅዱሳት መጻሕፍት ትእዛዛት ወደ ጎን የተባሉ ለመሆኑ ምስክር ነው። ጊዜያዊ ከነበሩት ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

1. የሐዋርያነት ስጦታ፥ 2. የነቢይነት ስጦታ፥ 3. ተአምራትን የማድረግ ስጦታ፥ 4. የመፈወስ ስጦታ፥ 5. በልሳናት የመናገር ስጦታ፥ 6. በልሳናት የተነገሩትን የመተርጎም ስጦታ፥ 7. መናፍስትን የመለየት ስጦታ።

የዚህ ክፍል ዓላማ፥ መጀመሪያ በሁሉም ዘንድ በዚህ ዘመን እንደሚሠሩ ታውቆ ተቀባይነት ያላቸውን ስጦታዎች አከራካሪ ከሆኑት ለይቶ ማቅረብ ነው።

## 1. የማስተማር ስጦታ

ይህ በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ከተጠቀሱ ስጦታዎች አንዱ ስለሆነ ዋና ዋና ከሚባሉ ስጦታዎች መካከል መቆጠር አለበት (ሮሜ 12፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11)። የማስተማር ስጦታ መሠረታዊ

ባሕርይ በሐዋርያት አገልግሎት ተገልጧል። ዋናው ተግባራቸው ከአረማዊነት ወደ ክርስቶስ የመጣውን አዲስ ክርስቲያን ማስተማር ነበር። የማስተማር ስጦታ ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ የተቀበለችውን እውነት ለመግለጥና ለማስረዳት የሚያበቃ ተአምራዊ ችሎታ ነበር። በዚህ ዓይነት እውነትን መረዳት ከመለኮታዊ አብርሆት ጋር የተያያዘ ቢሆንም አንድ ግን አይደለም። ብዙ ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ የተማሩ ናቸው፤ ነገር ግን የማስተማር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ያህል የማስተማር ችሎታ እንደሌላቸው ግልጥ ነው። አንድ ሰው የማስተማር ስጦታ ያለው መሆኑ ከሰው ይበልጥ ስለ እውነቶች ሁሉ እውቀት ያለው ሰው አያደርገውም። ተናጋሪው እንደ እግዚአብሔር አፍ ከሚቆጠርበት ከነቢይነት ስጦታም ጨርሶ የተለየ ነው። አስተማሪ እውነትን መረዳትና በመንፈስ ቅዱስ መማር አለበት። የማስተማር ስጦታ የሚያመለክተው በመጀመሪያ ሰው እውነትን ከሚቀበልበት መንገድ ይልቅ ያንን እውነት የመግለጥ እና ከሕይወት ጋር የሚያዛምድበትን ችሎታ ነው። በአሁኑ ጊዜ የማስተማር ስጦታ፤ ከመለኮት በተገኘ ችሎታ የእግዚአብሔርን ቃል የማስተላለፍ አገልግሎት ብቻ ነው።

## 2 . የመርዳት ወይም የማገልገል ስጦታ

በደረጃ የሚለያይ ቢሆንም እንኳ ክርስቲያኖች ሁሉ አላቸው ተብሎ የሚታመነው ስጦታ የማገልገል ወይም የመርዳት ስጦታ ነው (ሮሜ 12፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28)። ለማገልገል ወይም በመንፈሳዊ ነገር ሌሎችን ለመርዳት የተወሰነ ችሎታ የሌለው ክርስቲያን አለ ብሎ ለመገመት በጣም ያስቸግራል። ለማስተማር እና ለመምራት ስጦታ ያለው ሰው ጥቂት ቢሆንም፤ ክርስቲያኖች ሁሉ መርዳትና ማገልገል ይችላሉ። ይህ ችሎታ በሁሉም ዘንድ ያለ ቢሆንም፤ እያንዳንዱ ክርስቲያን በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለው ስፍራ መሠረት እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የሚለግሰው ስጦታ ነው። በስጦታዎች መካከል ያለው ልዩነት በርካታ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር በስጦታው ውስጥ ባለው የተለያየ ዓላማ መሠረት የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ያገለግሉበታል። መሪዎችዋ የቱንም ያህል ችሎታ ያላቸው ይሁኑ ከዚህ ስጦታ ውጪ ቤተ ክርስቲያን ተግባርዋን ልታከናውን አትችልም።

## 3. የአስተዳደር ስጦታ

ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ በእግዚአብሔር የሚሰጥ አመራር ነው። ከዚህ አንጻር እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የአስተዳደር እና የአመራር ስጦታን ለጥቂቶች ሰጥቷል (ሮሜ 12፡8፤ 1ኛ

ቆሮ. 12፡28)። መንፈሳዊ ነገሮችን በሚመለከት ክርስቲያኖች ሁሉ ያላቸው ደረጃ እኩል እንደሆነ ግልጥ ነው፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ለአንዳንዶች ከፍተኛ የሥልጣን ስፍራ ሰጥቷል። የአስተዳደርና የአመራር ስጦታ ላላቸው ወገኖች ክርስቲያኖች ተገቢውን አክብሮት ሊሰጧቸውና በመታዘዝ ሊያከብሯቸው ይገባል (ዕብ. 13፡7)።

## 4. የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ

ወንጌልን ለማወጅ ከሚያስፈልጉ ስጦታዎች መካከል ቀዳሚው ወንጌል ሰባኪነት ነው (ኤፌ. 4፡11)። ከዚህ ለማየት እንደሚቻለው ይህ ስጦታ የወንጌልን መልእክት ለማያምኑ ሰዎች ውጤት ባለው መንገድ ለመስበክ አስፈላጊ መሆኑንና፥ በአንጻሩም ለዳኑ ሰዎች መመሪያ የመስጠት ተግባር ካካተተው የማስተማር ስጦታ ጋር ሊወዳደር እንደሚችል በግልጥ እንመለከታለን። ከልምምድ እንደሚታወቀው ወንጌልን ማወቅ ብቻ ውጤት ባለው መንገድ ቃሉን ለመስበክ አያስችልም። ለምሳሌ ሰዎች የማስተማር ስጦታ ኖሯቸው የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ አይኖራቸው ወይም የሰባኪነት ስጦታ ኖሯቸው የማስተማር ስጦታ አይኖራቸው ይሆናል። በሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት እንደታየው፥ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የማስተማርም ሆነ የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን ሰው ሁሉ በምንም መንገድ ይሁን በምን ወንጌልን ለጠፉ ነፍሳት ለመስበክ ተጠርቷል። ስለዚህ እንደ ጢሞቴዎስ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አማኝ ሁሉ መሥራት አለበት (2ኛ ጢሞ. 4፡5)። አንዳንድ ሰዎች ለወንጌል ሰባኪነት ልዩ ስጦታ ይኖራቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዓላማ ነው።

## 5. የእረኝነት ወይም የመጋቢነት ስጦታ

ለክርስቲያን መንጋ አጠቃላይ እንክብካቤ የማድረግ ሥራ የእረኛው ሲሆን፥ ይህን እውን ለማድረግ አንዳንዶች የእረኝነት ስጦታን ተቀብለዋል (ኤፌ. 4፡11)። ከርእሱ እንደምንረዳው፥ ይህ ሥራ እረኛ ለበጎቹ ከሚያደርገው እንክብካቤ ጋር ይነጻጸራል። 'ፖኢሚናስ' ['poimenas'] የሚለው የግሪክ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም እረኛ ማለት ነው። ስለዚህ እረኛ (መጋቢ) መንጋውን የሚመራ፥ የሚንከባከብ፥ የሚጠብቅና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚሰጥ ነው። በተፈጥሮአዊ አፈጻጸሙ እንደምናየው ይህን የእረኝነት ሥራ በተገቢ ሁኔታ ለመወጣት በቂ ችሎታ እንደሚጠይቅ ሁሉ፥ በመንፈሳዊው ዓለምም መጋቢ (እረኛ) ሥራውን ሁሉ በሚገባ ለማከናወን ስማያዊ ስጦታ ያስፈልገዋል።

የእውነተኛ እረኛን (መጋቢ) ሥራ ሁኔታ በጥሩ አኳኋን ማስተዋል የሚቻለው በመጋቢነትና በማስተማር ሥራ መካከል ባለው የጠበቀ ግንኙነት ነው። ኤፌሶን 4፡11 እረኛን ከአስተማሪ ጋር የሚያያይዘው የመስተጻምር 'ካይ' ['kai'] ከተለመደው መስተጻምር 'ዴይ' ['de'] ይልቅ አንድ ሰው አስተማሪ ሳይሆን ጥሩ እረኛ (መጋቢ) ሊሆን እንደማይችል ያሳያል። በዚህ ውስጥ የምናየው መመሪያ እጅግ ታላቅ ነው። የማስተማር ስጦታ ያለው ሰው የእረኝነት (የመጋቢነት) ብቃቶች በሙሉ እንዲኖሩት ባያስፈልግም እውነተኛ እረኛ ግን መንጋውን ለማስተማር መቻሉ እጅግ አስፈላጊ ነው። መንጋውን መመገብ የማይችል እረኛ ይህ መጠሪያ ሊሰጠው ወይም በዚህ ስም ሊጠራ አይገባም። በመንፈሳዊ ክልል የመጋቢ የመጀመሪያ ሥራ መንጋውን በእግዚአብሔር ቃል መመገብ ነው። እውነተኛ እረኛ ከማደራጀት፥ ከማስተባበር እና ማኅበራዊ መሪ ከመሆን ሌላ ለማስተማርና ቃሉን ለመስበክ ሥራ ራሱን መስጠት አለበት።

## 6. የመምከር ስጦታ

መምከር የወንጌል ስብከት ሥራ ክፍል እንደመሆኑ መጠን ትልቅ ስፍራ አለው። ከማስተማር የሚለየው፥ ለተግባር የሚያነሣሣ ወይም የሚያበረታታ መሆኑ ነው። መምከር የስብከት አገልግሎት ተግባራዊ ክፍልም ነው። አንዳንዶች በዚህ ሥራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተግባራዊ ሊያደርጉ በሚችሉበት ሁኔታ እንዲረዱት አድርጎ ክርስቲያኖችን የመምራት ልዩ ስጦታ ተሰጥቷቸዋል። "መምከር" (ሮሜ 12፡8) ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል 'ፓራካሎን' ['parakalon'] (ሮሜ 12፡8) የሚለው ሲሆን ከዚህ ትርጉም ሌላ ማበረታታት፥ ማጽናናት፥ ማረጋጋት፥ የሚሉትን ትርጉሞች ያጠቃልላል።

## 7. የመስጠት ስጦታ

የመስጠት ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ የሚገኝ ነው። ይህ ስጦታ በሮሜ 12፡8 ከተገለጡት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ቢሆንም ከሌሎቹ ስጦታዎች ይልቅ ያለንን ንብረት በተገቢ ሁኔታ የመጠቀም ታማኝነትን ያመለክታል። ይህ ስጦታ በክርስቲያኖች ሁሉ እንደ ግለሰቡ የመስጠት አቅም የሚከናወን ሲሆን፥ በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሕይወት ግን እንደ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ልዩ በሆነ የለጋስነት ባሕርይ ሲገለጥ ይታያል። ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሰዎችና ሥራውን ለመርዳት ንብረታቸውን በፈቃደኝነትና በደስታ የመስጠት ልዩ ችሎታ እንዳላቸው ግልጥ ነው።

## 8. ምሕረት የማድረግ ስጦታ

በሮሜ ምዕራፍ 12 ከተዘረዘሩት መንፈሳዊ ስጦታዎች የመጨረሻው ምሕረት የማድረግ ነው (ሮሜ 12፡8)። የመስጠት ስጦታን በአእምሮአችን የምናስበው ስለ ድሆችና ጊዜያዊ የሆነ እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ችግረኞች ሲሆን፥ ይህ ስጦታ የተያያዘው ግን ከበሽተኞች፥ ወይም በሥቃይ ላይ ካሉ፥ ወይም በጣም መሠረታዊ የሆነ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት በደስታና በልግስና ምሕረት የማድረግ ችሎታ አላቸው። በግሪኩ ‘ሂላሮቴቲ’ [‘hilaroteti’] የሚለው ቃል በስም መልክ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው በዚህ ቦታ ብቻ ሲሆን፥ በውስጡ የአእምሮ ዝግጁነትንና በፍጥነት አንድ ነገር መፈጸምን ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሕይወት የሚያኖረው መልካም እርምጃን ለመውሰድ የተዘጋጀ ቀና አስተሳሰብን ሲሆን፥ ክርስቲያኖች ይህ ስጦታ እንዳላቸው ልንመለከት እንችላለን።

## 9. የእምነት ስጦታ

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 በተዘረዘሩት መንፈሳዊ ስጦታዎችና የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መካከል የእምነት ስጦታም ተጠቅሷል። ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች የሆኑት “የእውቀት ቃል” እና “የጥበብ ቃል” በመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጡ በተጠቀሰበት አንቀጽ የሚገኝ ነው። ይሁን እንጂ እምነት ለየት ባለ ክፍል ያለ የሚመስል ሲሆን፥ ምናልባትም አንዳንድ ክርስቲያኖች ፍጹም የላቀ እምነት እንዳላቸው የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም። ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳላቸው ግልጥ ቢሆንም፥ እምነት ልክ እንደ ስጦታ ለአንዳንዶቹ ለየት ባለ ሁኔታ የሚሰጥ በረከት ነው። በሕይወት ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በመስጠት እና በመምራት በሚሠራው የእግዚአብሔር ኃይልና ፍቅር የመተማመንን ያህል የክርስቶስን አዳኝነት በማመን የሚገለጥ አይደለም። በዚህ መልኩ በአሁኑ የጸጋ ዘመን ያለ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ቋሚ ባሕርይ ነው።

# 20

# ጊዜያዊ መንፈሳዊ ስጦታዎች

## 1. ተአምራት በአሁኑ ጊዜ ባለው የእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ያላቸው ስፍራ

በጊዜያችን ያለውን ክርስቲያናዊ ልምምድና በሐዋርያት ዘመን የነበረውን ስንመለከት አንዳንድ ተነጻጻሪ ነገሮች መኖራቸው ግልጥ ነው።

*የተአምራት እየቀነሱ መሄድ።* ወንጌል የማይለወጥ መሆኑና እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ሰዎች በሚመለከት የሚጠቀምበት አብዛኛው መንገድ ባለንበት ስፍረ-ዘመንም የቀጠለ ሲሆን፥ አንዳንድ ነገሮች ግን ከሐዋርያትና ከነርሱ ትውልድ ማለፍ በኋላ ጠፍተዋል። ይህን ለማብራራትም የተለያዩ መግለጫዎች ተሰጥተዋል። ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ቀድሞ ከነበረችበት ስፍራ ማፈግፈግዋና ከዚህ ቀደም የነበራትን መንፈሳዊ ኃይል ለማሳየት ብቃቱ ያነሳት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ በየዘመናቱ እውነተኞች ሆነው የሚኖሩ ታማኝ ቅዱሳን ስላሉ፥ እግዚአብሔር ራሱን በሙላት ለነርሱ ያለማቋረጥ ሊገልጥላቸው ይችላል። ቢሆንም ለሐዋርያት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት እጅግ ቅርበት ያላቸው እንኳ ሐዋርያት ያደርጉት የነበረውን ሲያደርጉ አይታዩም።

*የተአምራት ዓላማ።* አንዳንድ ስጦታዎች የተገለጡበት ሁኔታ የታየው በሐዋርያት ዘመን ብቻ ነው ለሚለው አሳብ ጥሩ መግለጫ የምናገኘው፥ እግዚአብሔር በሐዋርያት ዘመን የነበረውን ዓላማ በምናጠናበት ጊዜ ነው። በሐዋርያት ዘመን እግዚአብሔር (አንዳንድ ጊዜ የሚሰጡት ጥቅም አስፈላጊነት በማይጠየቅበት ሁኔታ እንኳ) በርካታ ተአምራትን ማድረግ ያስደስተው ነበር። ተአምራት የተፈጸሙባቸው ዘመናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ነቢያት እውነተኛነት ልዩ ምስክርነት የሚያስፈልግባቸው ጊዜያት ነበሩ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ የተአምራት ታሪክ።* ታላላቅና የታወቁ ተአምራት የተመዘገቡባቸው ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመናት አሉ፦ 1. የሙሴ ዘመን፥ 2. የኤልያስ እና የኤልሳዕ ዘመን፥ 3. የክርስቶስና የሐዋርያት ዘመን።

በነዚህ ሦስት ዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔርን መልእክት እውነተኛነት የሚያረጋግጡ መረጃዎች አስፈላጊ ነበሩ። የሙሴን ሁኔታ ስንመለከት ያደረጋቸው ተአምራት ያስፈለጉት፥ ሕዝቡ እንደ ነቢይና እንደ መሪ እንዲቀበሉት፥ መልእክቱም ከእግዚአብሔር እንደሆነ እንዲያውቁ

ነበር። ውድቀትና ክህደት በዝቶ በነበረበት በኤልያስና በኤልሳዕ ዘመን ደግሞ፥ ሕዝቡን ለመመለስ በተለይም ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ካህናትን አገልግሎት የሚተካና ተግባራቸውን በሚገባ ላከናወኑ ሥራ ያልተለመደ ዓይነት የእግዚአብሔር ኃይል ምስክርነት ያስፈልግ ነበር። በክርስቶስ ጊዜ ደግሞ ስለ ሰብዕናው ምስክርነት ለመስጠትና መሢሕነቱም ተአማኒ እንዲሆን ለማድረግ ተአምራት በተለየ ሁኔታ ያስፈልጉ ነበር። በሐዋርያት ዘመንም ወንጌላቸው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነበር። ልዩ የተአምራት መገለጥ የእያንዳንዱ ትውልድ የተለመደ ገጽታ አልነበረም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማራመድ ከርሱ ዕቅድ ጋር የተጣመረ ነበር።

*ከአዲስ ኪዳን መሟላት ጋር ያለው ግንኙነት።* የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከተሟሉና ለእግዚአብሔር እውነተኛ የሆኑ ወገኖች ሁሉ አዲስ ኪዳንን ከተቀበሉ በኋላ፥ ያልተለመዱ ታላላቅ ተአምራት አስፈላጊነት አብቅቷል። የአሁኑ ዘመን የወንጌል ሰባኪ የሚሰብከውን ወንጌል እውነተኛነት ለማሳየት የመፈወስ ወይም በልሳን የመናገር ውጫዊ ምልክት አያስፈልገውም። የተጻፈው ቃል በራሱ ይናገራል፥ ደግሞም ሰውን በመንፈስ ቅዱስ ወቅሶ በማሳመን ኃይል ይደገፋል። ይህ የእግዚአብሔርን ተአምራት የመሥራት ኃይል የመጠየቅ ወይም የመፈታተን ጉዳይ ሳይሆን፥ ልክ በሐዋርያት ዘመን በነበረው የመለኮታዊ ኃይል መግለጫ መንገድ፥ እግዚአብሔር አሁንም የመሥራት ዓላማ ያለውና የሌለው መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ነው። አንዳንድ የእምነት ክፍሎች በየትኛውም ዘመን ያሉ ሰዎች በእምነትና በእውነት ቢፈልጉት በሐዋርያት ዘመን የተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል ያልተለመዱ ገጽታዎች ሊታዩ ይችላሉ የሚለውን አሳብ አጥብቀው ይዘዋል። ነገር ግን ፍጹም የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው ብለን በምንገምታቸው ባለፉት ትውልድ በነበሩ ሰዎች ሕይወት እንኳ ለጊዜው የተሰጡ ናቸው ብለን ያቀረብናቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች የሌሏቸው እንደነበሩ ግልጥ ወይም የተረጋገጠ ነው። ደግሞም በዚህ ዘመን እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች በተለያዩ አሀጉራት ዜና እንደሚሰማው፥ በአጠቃላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ፥ ለክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባርና ለከፍተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው አመለካከት እጅግ ደካማና ለዘብተኛ መሆኑ በግልጥ ታይቷል። የእነዚህ የእምነት ክፍሎች ታሪክ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ከመጠን በላይ መፈለግ ወዳልተቀደሰና ወደ በርካታ የተበላሸ ነገር የሚመራ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።

*ቅዱሳት መጻሕፍት ከልምምዶች ሲነጻጸሩ።* ከባሕርዩ የተነሣ የክርስትናን ልምምድ በጠቅላላው ለማዳረስ የሚቻለው የለም። መሠረታዊ

የእምነት ትምህርትን በተለያዩ ልምምዶች ላይ መሥርተው እውነትነታቸውን ለማሳየት የሚጥሩ ሰዎች ሲያጋጥሙ ሁልጊዜ የመጨረሻው መመዘኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ? የሚል መሆን አለበት። ለማጠቃለል ልምምዶች ከፊል መመዘኛዎች ቢሆኑም፥ የመጨረሻው ሥልጣን ተደርጎ መወሰድ ያለበት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ልምምድ ሁልጊዜ ለስሕተት የሚያጋልጡ ሁለት አደገኛ መሠረቶች አሉት፡- 1. በይዘትና በመለኮታዊ ጅማሬው ልምምድን በተሳሳተ መንገድ መረዳት፥ 2. የልምምድን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትርጉም በተሳሳተ መንገድ ማጠቃለል።

ስለዚህ በአንድ በኩል የመለኮት ጅማሬ ያለው ነው የምንለው ልምምድ፥ የሥነ-ልቦና ጉዳይ ወይም ከዚህ ከባሰ የሰይጣን የማጭበርበሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሥራ እንደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተደርጎ እንደተወሰደ ሁሉ፥ ትክክለኛና እውነተኛ ልምምድን በተሳሳተ መንገድ መረዳት ወይም መሰየም ይቻላል። እውነትን የሚፈልግ ክርስቲያን፥ በማናቸውም ሁኔታ እውነትን ከሚያጣምም እምነት በመራቅ ለእውነተኛ ትምህርት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ታምኖና ተደግፎ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለበት።

## 2. የሐዋርያነት ስጦታ

*የሐዋርያነት አገልግሎት መጠን።* ‘አፖስቶሎስ’ [‘apostolos’] ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣው ሐዋርያ የሚለው ቃል ትርጉም “ተወካይ፥ መልእክተኛ፥ ወይም በትእዛዝ የተላከ” ማለት ነው። ታየር የተባለ ሰው እንደተናገረው፥ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን 78 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፥ ከእነዚህ መካከል 38ቱ የሚገኙት በሉቃስ ወንጌል፥ በሐዋርያት ሥራና በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ነው። ቃሉ በመጀመሪያ ሥራ ላይ ውሎ የምናገኘው፥ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የእግዚአብሔርን መንግሥት መቅረብ ይሰብኩ ዘንድ በተላኩ ጊዜ ነው (ማቴ. 10፡2፤ ማር. 3፡14፤ 6፡30፤ ሉቃስ 6፡13)። ወደ ሐዋርያነት አገልግሎት ከተጠሩት መካከል ጳውሎስ (ሮሜ 1፡1፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡1 ወዘተ.)፥ በርናባስ (ሐዋ. 14፡14፤ ገላ. 2፡9ን ይመልከቱ)፥ ማትያስ (ሐዋ. 1፡25-26) ፤ እና ምናልባት ያዕቆብ (1ኛ ቆሮ. 15፡7፤ ገላ. 1፡19)፤ አጵሎስ (1ኛ ቆሮ. 4፡6-9) ይገኙበታል። አንዳንዶች ደግሞ ከእነዚህ ሌላ ስልዋኖስና ጢሞቴዎስ (1ኛ ተሰ. 1፡1፤ 2፡6)፥ አፍሮዲጡ (ፊልጵ. 2፡25)፥ ስማቸው ያልተጠቀሰ ወንድማማቾች (2ኛ ቆሮ. 8፡23)፥ አንዲራኒቆንና ዩልያንን (ሮሜ 16፡7) ይጨምራሉ።

ይህ ቃል ለተለያዩ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የዋለ በመሆኑ፥ አንዳንድ ሰዎች ሐዋርያ በተለይ ለሚሲዮናዊነት ሥራ በእግዚአብሔር የተጠራ

ማንኛውም ሰው ነው የሚል አቋም ይዘዋል። ጄ. ሲ. ላምበርት [J. C. Lambert] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፥ "ሐዋርያነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለየና የተወሰነ ሥልጣንና ኃላፊነት ለያዘ ሰው የሚሰጥ ስም አይደለም። ነገር ግን አንድና ታላቅ ማለትም ውጤቱ የነቢይነት አገልግሎት የሆነ ተግባር መፈጸም ለሚችሉ በርካታ ሰዎች የተሰጠ ስም ነው" (1ኛ ቆሮ. 12፥28፤ ኤፌ. 4፥11) ብሏል። ይበልጥ የተለመደው አቋም ግን፥ በመጀመሪያ በዚህ ስም በቀጥታ ሊጠሩ የሚገባቸው፥ የክርስቶስ ኢየሱስ ትንሣኤ ምስክሮች የሆኑና፥ በክርስቶስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ለዚህ ዓላማ በወጉ የተጠሩት ሲሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ምስክር ይሆኑ ዘንድ በአጠቃላይ የተጠሩትንም ሊያመለክት ይችላል። በማንኛውም ረገድ ቢሆን በሐዋርያት ዘመን የነበረ የወንጌል አገልጋይ ሁሉ ሐዋርያ ተብሎ እንዳልተጠራ ሁሉ፥ እንደ ላምበርት አስተሳሰብ ሐዋርያት ሁሉ ሚሲዮናውያን ነበሩ ብሎ ማረጋገጥም የማይቻል ነው።

*ለሐዋርያነት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች።* ሲ. አይ. ስኮፊልድ የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ፥ ወደ አዲስ ኪዳን ሐዋርያነት ለመግባት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ግሩም በሆነ መንገድ አሳጥሮ አቅርቧቸዋል።

"1. ሐዋርያት የተመረጡት በቀጥታ በጌታ ወይም እንደ በርናባስ አመራረጥ በመንፈስ ቅዱስ ነበር (ማቴ. 10፥1፥ 2፤ ማር. 3፥13፥ 14፤ ሉቃስ 6፥13፤ ሐዋ. 9፥6፥ 15፤ 13፥2፤ 22፥10፥ 14፥ 15፤ ሮሚ 1፥11)፤

"2. የአገልግሎታቸው መለኮታዊ የሹመት ማስረጃ ይሆን ዘንድ የምልክት ስጦታዎች ማለትም ተአምራትን የማድረግ ኃይል ተሰጣቸው (ማቴ. 10፥1፤ ሐዋ. 5፥15-16፤ 16፥16-18፤ 28፥8-9)፤

"3. ከዳዊት መንግሥት ወራሽነት ጋር ካላቸው ግንኙነት ይህን መንግሥት ለእስራኤል ብቻ ማወጅ (ማቴ. 10፥5-6)፥ መንግሥቱ በደጅ እንደሆነ መናገር (ማቴ. 4፥17)፥ የመንግሥቱን ኃይል መግለጥ (ማቴ. 10፥7-8) ነበር፤

"4. የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ፥ በማቴዎስ 13 እንደተገለጠው ክርስቲያን ለተባለ ሁሉ ጠቃሚ እንዲሆን፥ ከሐዋርያት አንዱ ለሆነው ለጴጥሮስ ተሰጥቷል (ማቴ. 16፥19)።

"5. ከሚመጣው መንግሥት ጋር ያላቸው የወደፊት ግንኙነት በአሥራ ሁለቱ ነገዶች ላይ ፈራጅ መሆን ነው (ማቴ. 19፥28)፤

"6. አይሁድ ክርስቶስንና ክርስቶስ ሊመሠርተው የመጣውን የዳዊት መንግሥት ባለመቀበላቸው፥ ሐዋርያት ከዚህ ቀደም ያልታወቀ

ምስጢርን ማለት "ቤተ ክርስቲያን" መግለጥ ጀመሩ (ማቴ. 16፡18፤ ኤፌ. 3፡1-12)። ለሐዋርያት አገልግሎት አዲስ ምልክት ተሰጠ፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነበር። ለእያንዳንዱ አይሁዳዊ ክርስቲያን አዲስ ኃይል ማለትም መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶታል (ሐዋ. 2፡1-4)። በመካከላቸው የተፈጠረው አዲስ ግንኙነት ለአዲሱ ቤተ መቅደስ መሠረት ነበር (ኤፌ. 2፡20-22)። የነበራቸውም አገልግሎት መልካሙን የምስራች ማለትም ስለተሰቀለውና ስለተነሣው ጌታ ለአይሁድም ሆነ ለአሕዛብ መስበክ ነበር።

"7. ለሐዋርያነት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ መመዘኛዎች አንዱ የትንሣኤው የዓይን ምስክር መሆን ነበር" (ሐዋ. 1፡22፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡1)።

*ሐዋርያነት ስጦታ ነው።* ከሐዋርያነት የሹመት ባሕርይ ልዩ መሆን አንጻር ሲታይ በአዲስ ኪዳን እንደ ስጦታ ቀርቧል (1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11)። እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ስጦታዎች ዋናው መሆኑን ለመግለጥ፥ "እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶችን አስቀድሞ ሐዋርያትን" (1ኛ ቆሮ. 12፡28) በሚለው ቃል ቀርቧል። ሐዋርያት ከነቢያት፥ ከአስተማሪዎች፥ ከተአምራት አድራጊዎች፥ ወዘተ. (1ኛ ቆሮ. 12፡28) ተለይተው ቀርበዋል። ስለዚህ ሐዋርያነት የተሰጠው ውሱን ከሆነው የቃሉ ትርጉም የተነሣ በቀጥታ ሐዋርያት ብለን ለምንጠራቸው ሰዎች ነው። ከላይ ያመለከትነውን ጥቅስ ስኮፊልድ እንዳመለከተው፥ ከጰንጠቆስጤ ዕለት በፊት የነበረው የሐዋርያነት አገልግሎት ከዚያ በኋላ ከነበረው የተለየ መሆን አለበት። ከጰንጠቆስጤ ዕለት በፊት የነበረው የሐዋርያት አገልግሎት የእግዚአብሔር መንግሥት በደጅ መሆኑን ማወጅ ነበር። ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ የደኅንነትን ወንጌል የሚያስተዋውቁ መሪዎች፥ መለኮታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት፥ ደግሞም ለትምህርታቸው መሠረት የሚሆን ልዩ መገለጥ የተሰጣቸው ሆኑ። የነቢይነትና ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ያላቸው ሁሉ ሐዋርያት ባይሆኑም፥ ሐዋርያት ሁሉ ግን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ሁለት ስጦታዎች ነበሯቸው (2ኛ ቆሮ. 12፡12)። የሐዋርያነት አገልግሎት በመጀመሪያው የክርስትና ክፍለ-ዘመን ያበቃለት ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት በኋላ እንዴት እንደሚቀጥል የተገለጠ ነገር የለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥም ከሐዋርያት ጋር ተስተካክሎ ሊቆም የሚችል አይገኝም። እነዚህ ሐዋርያት ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በዓይን ካዩት መካከል መመረጣቸው በኋለኛው ዘመን የሐዋርያነት ጥሪ ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች የመኖራቸውን ዕድል እንዲያከትም አድርጎታል። ከዚህም የተነሣ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያነትን አገልግሎት ለመቀጠል የምታደርገው ሙከራ በተደጋጋሚ ተቃውሞ ገጥሞታል።

## 3. የነቢይነት ስጦታ

*የነቢይነት ስጦታ መጠን።* በመንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ በሁለተኛነት ደረጃ የሚቀርበው የነቢይነት ስጦታ ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡28)። የዚህ ስጦታ አስፈላጊነትና ዋናነት በሌሎች ክፍሎች በእርግጠኝነት መጠቀሱን ያረጋግጥልናል (ሮሜ 12፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡10፤ 14፡1-40)። በሐዋርያት ዘመን ይህ ስጦታ የነበራቸው በርካታ ሰዎች ነበሩ። የነቢይነት ስጦታ በእርግጥ የነበረው አጋቦስ፥ ሊመጣ ስላለው ረሀብ አመለከተ (ሐዋ. 11፡27-28)። ደግሞም ጳውሎስን ሊደርስበት ስላለው መከራ በማመልከት አስጠንቀቀው (ሐዋ. 21፡10-11)። በርናባስ፥ ስምዖን፥ ሉክዮስ፥ ምናሔና ጳውሎስ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት "መምህራንና ነቢያት" መካከል እንደሆኑ ተጠቅሷል (ሐዋ. 13፡1)። የወንጌላዊው ፊልጶስ አራት ሴት ልጆች የነቢይነት ስጦታ ነበራቸው (ሐዋ. 21፡9)። ይህም ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን፥ በአዲስ ኪዳንም የነቢይነት ስጦታ ለወንዶች ብቻ የተሰጠ እንዳልነበረ ያመለክታል። በጳውሎስ ውስጥ የምናየው የእግዚአብሔር አመራር፥ የነቢይነት ማስተዋል እንደነበረው በግልጥ ያስረዳናል (ሐዋ. 16፡6ቀ.፤ 18፡9-10፤ 22፡17-21፤ 27፡23-24)። ይሁዳና ሲላስም ነቢያት እንደነበሩ ተነግሯል (ሐዋ. 15፡32)። ሐዋርያት ሁሉ የነቢይነት ስጦታ ነበራቸው ቢባል እውነት ይመስላል።

*የአዲስ ኪዳን ነቢይ ባሕርያት።* አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ነቢያት፥ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ባሕርይ ወስደዋል። ሁሉም የሚናገሩት ለእግዚአብሔር ነበር። ሁሉም በኃጢአት ላይ ስለሚመጣ ፍርድ ተናግረዋል። መልእክታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ አስተላልፈዋል። ሁሉም ስለ ጊዜያቸውም ሆነ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ተናግረዋል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ነቢያት የብሔራዊ መሪነት ወይም የጀግና ባሕርይ የነበራቸው ሲሆን፥ መልእክታቸውን ያስተላለፉት በተለይ ለእስራኤል ሕዝብ ነበር። የአዲስ ኪዳን ነቢያት ግን፥ ምንም ዓይነት የብሔርተኝነት ባሕርይ አናይባቸውም። መልእክታቸው ግላዊና ለእያንዳንዱ ሰው የሚሆን ሆኖ፥ እርሱ ካልገለጠው በቀር የማይታወቀውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይገልጡ ነበር። ይህም በኋላ በጽሑፍ በቀረልን አዲስ ኪዳን ውስጥ ያገኘነውን ነገር ያሟላል።

*በነቢይነት ስጦታ ውስጥ ያሉ ነገሮች።* በነቢይነት ስጦታ ውስጥ የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮች አሉ:-

1. ነቢዩ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክቱን በአንድ በተለየ መገለጥ መቀበል አለበት። መልእክቱም በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተላለፈና ከዚያ በፊት ያልታወቀ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ የተገለጠ

አይደለም። እንዲሁም መልእክቱ ለነቢዩ ሳይሆን እግዚአብሔር ላሰባቸው ሕዝቦች ጥቅም ነው፤

2. አንድ ነቢይ የተገለጠለትን መልእክት ለማስተላለፍ፥ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተሰጠው ቃል መለኮታዊ ምሪት የሚያስፈልገውን ያህል፥ ነቢይም መለኮታዊ ምሪት ያስፈልገዋል፤

3. የሚያስተላልፈው መልእክት በውስጡ የእግዚአብሔር ሥልጣን ሊኖርበት ይገባል።

የነቢዩ መልእክት የግድ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች መሆን እንደሌለበት በተደጋጋሚ ታይቷል። አሁን ስለሚሆኑ ነገሮች ወይም ስለ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትርጓሜ ሊሆን ይችላል። ይህ አለመሆኑ ግን መልእክቱ ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን የሚሽር አይደለም። አማኝ በዘመናችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ማስተማሩ የነቢይነት ስጦታ ማረጋገጫ አይደለም። አንድ ነቢይ እውነተኛ ከሆነ፥ የራሱን የአእምሮ ሥራ ውጤት ሳይሆን ከስሕተት ነጻ የሆነና ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነን መገለጥ ማቅረብ አለበት። ነቢያት ጴጥሮስ አመለካከቱን ከሕግ አክራሪነት ጋር ለማመሳሰል በሞከረ ጊዜ እንዳደረገው ስሕተት ቢሠሩም እንኳን፥ መልእክታቸው ግን ከስሕተት ፍጹም ነጻ መሆን አለበት። በመሆኑም በአዲስ ኪዳን ስሕተትን አስተምሮ እንደ እውነተኛ ነቢይ የተቆጠረ ማንም የለም።

*በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የነቢይነት ስጦታ አስፈላጊነት።* በሐዋርያት ዘመን የነቢይነት አገልግሎት አስፈላጊ እንደነበረ ግልጥ ነው። በተለምዶ የአይሁድ እምነት ከነበረው ወደ ክርስትና ለመምጣት ሰፊ የሆነ የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ሽግግር የሚጠይቅ ነበረ። አዲስ ኪዳን የተጻፈው ወዲያውኑ አልነበረም። ለእግዚአብሔር ፈቃድ ዳግም መገለጥ ሥልጣን ያለው ምንጭ የግድ አስፈላጊ ነበር። በተለምዶ የሚታመነውን የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በሥርዓት ለማዘጋጀትም ምሪት አስፈልጓል። ይህን ለማሟላት እግዚአብሔር ሰማያዊ የሆነ የነቢይነት ስጦታ ያላቸውን ነቢያት ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ። አብዛኛዎቹ የመጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እስኪሟሉ ድረስ በሕይወት ባይኖሩም፥ በእነርሱ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ለነቢያት አገልግሎት በቂ ትኩረትን መስጠቷ ተገቢ ሆኗል።

ነቢይነት ለማነጽ፥ ለመምከርና ለማጽናናት (1ኛ ቆሮ. 14፡3) የሚጠቅም ታላቅ ስጦታ እንደሆነ በግልጥ ቀርቧል። በልሳን ከመናገር ስጦታ ጋር ሲወዳደር፥ የማስተማርና የነቢይነት ስጦታን መጠቀም እጅግ የላቀ መሆኑ ተገልጧል። “ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ” (1ኛ ቆሮ. 14፡19)። በተለይ አማኞችን ለማስተማር

ትንቢት ልዩ ጥቅም ያለው መሆኑ ተገልጧል (1ኛ ቆሮ. 14፡22)። በቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ውስጥ ሥርዓት ለማክበር ነቢያት ተራ በተራ መናገር እንዳለባቸው ጳውሎስ ያመለክታል፥ "ሁሉም እንዲማሩ፥ ሁሉም እንዲመከሩ፥ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ" (1ኛ ቆሮ. 14፡31)። "የጥበብ ቃል" እና "የእውቀት ቃል" ከነቢያት ስጦታ ጋር የተያያዙ ሳይሆኑ አይቀሩም (1ኛ ቆሮ. 12፡8)።

*የነቢይነት ስጦታ ጊዜያዊ ባሕርይ።* በአሁኑ ጊዜ ሰዎች የማስተማር፥ የመምከርና ወንጌልን የመስበክ ስጦታ እንዳላቸው ብንስማማም የነቢይነት ስጦታ ግን ማንም እንደሌለው መቀበል ተገቢ ውሳኔ ነው። አዲስ ኪዳን ሙሉ በሙሉ ከተጻፈ በኋላ ሌላ መገለጥ እንደማያስፈልግ ተረጋግጧል። የእግዚአብሔር ዓላማ ራሱን በቃሉ ውስጥ ብቻ መግለጥ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ውጤት ነው ብሎ ሌላ መጽሐፍ መጨመር እንደማይቻል ሁሉ፥ የነቢይነት ስጦታም በዚህ ዘመን አለ ብሎ መናገር አይቻልም። በ1ኛ ቆሮንቶስ 13፡8 መሠረት ፍቅር ለዘላለም የሚኖር መሆኑ ሲገለጥ፥ ትንቢት ግን የሚሻር እንደሆነ ተገልጧል። በራእይ 22፡18-19 በዚህ መጽሐፍ ላይ አንዳች ነገር የሚጨምሩ ፍርድ እንዳለባቸው በማስገንዘብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል።

## 4. ተአምራት የማድረግ ስጦታ

*ተአምራት ማድረግ አነስተኛው ስጦታ ነው።* ተአምራት የማድረግ ስጦታ ከአናሳ ስጦታዎች የመጀመሪያው ሆኖ ቀርቧል (1ኛ ቆሮ. 12፡28)። ሐዋርያነት፥ ነቢይነትና አስተማሪነት በቅድሚያ የሚያስፈልጉ ስጦታዎች ሲሆኑ፥ ተአምራትን ማድረግና ሌሎች ስጦታዎች በሁለተኛነት ቀርበዋል። ጸሐፊው የተጠቀመበት "ቀጥሎም" የሚለው ቃል ቅደም ተከተል፥ ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ያሳያል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እነዚህ ነገሮች ሲጽፍ፥ መጀመሪያ መሆን ያለበትን ነገር መጀመሪያ ገልጧል። ተአምራትን የሚገልጠው 'ዱናሚስ' የተሰኘው ቃል የተፈጥሮን ኃይል ማለት፥ አንድ ነገር በራሱ ተፈጥሮ ውስጥ የሚኖረውን ኃይል የሚያመለክት ነው። ከዚህ አሳብ ተአምራትን ለማድረግ የተለየ የኃይል አጠቃቀምን ማውጣት ይቻላል። የተአምራትን ባሕርይና ዓላማ ለመግለጥ ከሌሎች ቃላት ጋር በቅንጅት የቀረበ ቢሆንም፥ ክርስቶስ ያደረጋቸውን ተአምራት ለመግለጥ የዋለና የተለመደ ቃል ነው (ማር. 5፡30፤ ሉቃስ 5፡17፤ 6፡19 ፤ 8፡46 ወዘተ.)። በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፡12፥ ተአምራትን ማድረግ ከምልክት፥ ከድንቅ ነገር፥ እና ከታላላቅ ሥራዎች ጋር በአንድ ላይ ተዳብሎ "የሐዋርያነት ምልክት" ሆኖ ቀርቧል። በዚህ መሠረት

ተአምራትን ማድረግ፥ የሐዋርያነትና የነቢይነትን አገልግሎት ሥልጣን ለማሳወቅ የሚያስችል መለኮታዊ ኃይል መግለጫ ነው።

*ተአምራትን የማድረግ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን መጨረሻ ላይ አብቅቷል።* አስቀድመን እንደተመለከትነው ይህ ያልተለመደ የመለኮታዊ ኃይል መግለጥ ተግባር፥ እግዚአብሔር ለሐዋርያት ዘመን ብቻ ያቀደው ዓላማ ነበር። ስለዚህ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈው ቃል ከተሰጠን በኋላ ተአምራትን የማድረግ ሥራ አክትሟል። ተአምራትን የማድረግ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ብቻ የተወሰነ ነበር በሚለው አቋም ላይ ብዙ ጊዜ ተቃውሞ የሚነሣው፥ ተአምራትን ሁሉ ተአምራት ከማድረግ ስጦታ ጋር በማያያዝ ከሚሰጥ አደናጋሪ አሳብ የተነሣ ነው። የሐዋርያትን ዘመን ልዩ የሚያደርገው፥ አንዳንድ ሰዎች በፈለጉ ጊዜ በክርስቶስ ስም ተአምራት የማድረግ ኃይል ስለነበራቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ነበራቸው።

*ስጦታው ያበቃ ቢሆንም ተአምራት ቀጥለዋል።* በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ ተአምራት መታየታቸው እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ በመስጠት ታላላቅ ሥራዎችን የሚፈጽም መሆኑን ያመለክታል። ነገር ግን ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የታመሙትን ሁሉ ለመፈወስ፥ ሙታንን ለማስነሣት፥ በሌላ አነጋገር ያልተለመዱ ታላላቅ ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ለማንም አልተሰጠም። የሐዋርያነትና የነቢይነት ስጦታ እንዳበቃ ሁሉ፥ የምልክቶች ስጦታም አብቅቷል። ለስጦታዎቹ ማብቃት ምክንያት የሆነው ጌታ ቃሉን በጽሑፍ ለኛ በማስቀረቱ ነው። ክርስቲያን አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ድንቅ ሥራን እንዲሠራ ለመለመን ይችላል። እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ ይሰጣል። እግዚአብሔር ከፈለገ አሁንም ቢሆን በሽተኞችን ሊፈውስም ሆነ ሙታንን ሊያስነሣ ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ለሰዎች ፈቃድ የማይገዙ ወይም እንደ መንፈሳዊ ስጦታ የማይሰጡ፥ ሉዓላዊና ግላዊ ስጦታዎች ናቸው። ስለዚህ ምንም እንኳ ተአምራትን የማድረግ ስጦታዎች በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር እቅድ ባይሆኑም፥ የእርሱ ተአምራትን የማድረግ ኃይል ግን ጨርሶ ያልተቋረጠና የሚሠራ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

## 5. የፈውስ ስጦታ

ፈውስን እንደ ስጦታ የሚያቀርብ ብቸኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚገኘው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥9፥ 28፥ 30 ነው። በሦስቱም ቦታዎች ፈውስ የገባው ከስጦታዎች ጋር ነው። ፈውስ በተለይ የእግዚአብሔር ኃይል ከሚገለጥባቸው ተአምራት አንዱ ገጽታ ነው። ተአምራትን ማድረግ ግን ከፈውስ በተለየ መንገድ ይከናወናል። ለምሳሌ ኤልማስ በተአምራት

ማድረግ ስጦታ አማካይነት ከመፈወስ ይልቅ እንዲታወር ሆኗል (ሐዋ. 13፡11)። የፈውስ ስጦታ በተለይ አካላዊ ጤንነትን ከመመለስ ጋር የተያያዘ ነው። ተአምራትን እንደማድረግ ስጦታ ለታወጀው እውነት ምስክር ይሆን ዘንድ የቆመ ሲሆን፥ ስጦታነቱ ከሐዋርያት ማለፍ ጋር አብቅቷል። ተአምራትን ማድረግ ያለ ስጦታ ሊኖር እንደቻለ ሁሉ፥ ያለ ፈውስ ስጦታም ፈውስ ሊኖር ይችላል። የፈውስ ስጦታ የቀረ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በእምነት የሚደረግን ጸሎት በመመለስ ረገድ ፈውስ ሊሰጥ ይችላል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ጸሎት አድርገው በሚያገኙት ፈውስ ያልተለመደ ልምምድ ሊኖራቸው ቢችልም፥ ፈውስ እንደ ስጦታ ለሰዎች የመሰጠቱና በተሰጣቸው ሰዎች ፈቃድ የመፈጸሙ ጉዳይ ግን ያከተመ ይመስላል። በሁሉም ረገድ ፈውስ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የሚሰጥ ነው። በአሁኑ ጊዜ አንድ ሰው ምንም እንኳን በጸሎት ብርቱ፥ በእምነትም የተሞላ ቢሆን የፈውስ ስጦታ ሁሌ በእርሱ ኖሮ ይፈውሳል ማለት አንችልም።

## 6. በልሳናት የመናገር ስጦታ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጠቃላይ በልሳናት የመናገር ስጦታን ያህል በተከታታይ ውዝግብ ያስነሣ መንፈሳዊ ስጦታ የለም። በዚህ ስጦታ ባሕርይ ምክንያት ለተፈጠሩ ችግሮች ሁሉ በርካታ መፍትሔ የተሰጠ ቢሆንም፥ መፍትሔዎቹ የራሳቸው ድክመት ይታይባቸዋል። ይሁን እንጂ ሰፊና የተሟላ ገለጣ መስጠት የሚቻለው በዚሁ ርእስ ላይ ብቻ በተጻፈ ሥራ ቢሆንም፥ በዚህ ውሱን ጥናት ችግሮቹን መግለጥ፥ በልሳናት የመናገርን ባሕርይ መመርመርና ይህ ስጦታ ጊዜያዊ የመሆኑን አሳብ አቅርቦ ለማጠቃለል ይቻላል።

*ችግሩን መግለጥ።* በልሳናት የመናገር ስጦታን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለመመርመር፥ በመጀመሪያ ልንመለከተው የሚገባ ነገር የጴንጠቆስጤ ታሪክ ነው (ሐዋ. 2፡1-13)። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚገልጡት ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ያገኙት፥ በዚያ ተሰብስበው የነበሩት ሁሉ "መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" (ሐዋ. 2፡4) በሚለው መሠረት ነው። ሁኔታው የሚሉትን እስኪያጡ ድረስ በዚያ የነበሩትንና በጌታ ያላመኑትን ሰዎች አስደንቋቸው ነበር። እያንዳንዱ በገዛ ቋንቋው ሲናገር ሰሙ። የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራ በልሳኖቻቸው ተገለጠ (ሐዋ. 2፡8-11)። አንዳንዶች ይህ የስካር ነገር ነው አሉ። ጴጥሮስ ግን "ደግሞ በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ" የሚለውን ከኢዩኤል 2፡29 ጠቅሶ አስቀድሞ የተተነበየ ነው ሲል አሳባቸውን

በመቃወም ያ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ምልክት መሆኑን ተናገረ (ሐዋ. 2፡18)።

በሌሎች ቋንቋዎች መናገራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ይህ አሳብ ግልጥ በሆነ ዓረፍተ ነገር ከመነገሩም በላይ፥ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሰዎች እንደሰሟቸውና የሚሉትም ነገር እንደገባቸው መጠቀሱ የተረጋገጠ ነው። ተፈጥሮአዊ የሆኑ ማብራሪያዎች ሁሉ መወገድ አለባቸው። በልሳን መናገር፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት ለተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል ምልክት ይሆን ዘንድ የታሰበ የእግዚአብሔር ተአምራዊ ሥራ መሆኑ ግልጥ ነው።

በሐዋርያት ሥራ 10፡46፥ የቆርኔሌዎስንና የቤተሰቡን መለወጥ በሚመለከት በተጻፈው ታሪክ ላይ በልሳናት የመናገር ነገር ለሁለተኛ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን። ጴጥሮስ የወንጌሉን ቃል በሚናገርበት ጊዜ በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፥ "በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና" (ሐዋ. 10፡46)። የወንጌልን በአሕዛብ ዘንድ መስፋትና መድረስ ድርጊቱን ከጰንጠቆስጤ ጋር የሚያያዝ ይመስል በልሳን መናገር ተደግሞ እናገኛለን። ጴጥሮስ ያን ታሪካዊ ድርጊት በመጥቀስ ይህንኑ አመልክቷል፡- "ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ደግሞ መጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው" (ሐዋ. 11፡15)።

ሦስተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሐዋርያት ሥራ 19፡6 ነው። ጳውሎስ የጸጋን ወንጌል ጨርሰው ያልሰሙና በዚህም ምክንያት በእምነት ወደ ክርስቶስ ዘወር ያላሉ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መኖራቸውን አወቀ። እነርሱ ከተጠመቁ በኋላ፥ "ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ" (ሐዋ. 19፡6)። በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ (12፡10፥ 28፥ 30፤ 14፡1-40) ከተጠቀሱት ሌላ በልሳናት ስለመናገር የሚገልጡ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ከፍ ብለን ያየናቸው ሦስቱ ናቸው። በሐዋርያት ሥራ የሚገኙት እነዚህ ጥቅሶች በልሳን ስለመናገር ስጦታ አያብራሩም። ወይም ደግሞ በእነዚህ ሦስት ክፍሎች በልሳን ስለመናገራቸው የተጠቀሰላቸው ሰዎች በሌላ ጊዜ ደግመው በልሳን ስለመናገራቸው የተጠቀሰ ነገር የለም። ከ1ኛ ቆሮንቶስ ውጭ ስለ መሠረታዊው የእምነት ትምህርት በየትኛውም መልእክት መግለጫ አልተሰጠም። በዚሁ መሠረት የስጦታውን ባሕርይ ለማጥናት የሚያስችል ፍንጭ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ የተፈጸሙ ድርጊቶችን በማጥናት ሲሆን፥ የአጠቃቀሙን ደንብና መጠን ደግሞ በ1ኛ ቆሮንቶስ መሠረት መወሰን ይቻላል።

ለችግሩ የተለያዩ መፍትሔዎች። መሠረታዊውን የእምነት ትምህርት በሚመለከት አጠቃላይ ወደሆነ ውሳኔ ከመድረሳችን በፊት፥ ችግሩን በተለያዩ ቀላል መንገዶች ለመፍታት የሚቻለው ሁሉ መደረግ አለበት። የለዘብተኛ (ሊበራል) ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ይህን ችግር ለማቃለል የሞከሩት፥ የሐዋርያት ሥራ የተጻፈበትን ጊዜ ዘግየት በማድረግና፥ እነዚህ ክፍሎች በመጀመሪያው የሐዋርያት ሥራ ያልነበሩና በኋላ የተጨመሩ ናቸው ከሚል ፅንሰ-አሳብ በመጀመር ነው። ይህ ፅንሰ-አሳብ ምኞታዊ ለው ከማለት ውጪ አሳቡን ለመደገፍ ምንም ዓይነት የጠለቀ ማስረጃ ለማቅረብ እንደማይቻል እርግጥ ነው።

በሁሉም የሥነ-መለኮት ትምህርት ክፍሎች በሚገኙ አንዳንድ ጸሐፊዎች ዘንድ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 እና በ1ኛ ቆሮንቶስ ምንባቦች መካከል ልዩነት አለ የማለት አዝማሚያ ይታያል። አንዳንዶች በሐዋርያት ሥራ 2 ያለው በልሳን የመናገር ጉዳይ፥ ባዕድ በሆኑ በሌሎች ሰዎች ቋንቋዎች መናገርን የሚጨምርና የቋንቋዎቹ ተናጋሪዎችም የሚረዱት ዓይነት ቋንቋዎች እንደነበሩ ያምናሉ። በ1ኛ ቆሮንቶስ የተጻፈው ግን በልሳናት መናገር የሰው ቋንቋን ሳይጠቀሙ ውስጣዊ የሆነ ፍላጎት የሚገለጥበትና ከልሳናቱ የሚወጣው እንግዳ የሆነ ድምፅ፥ የመተርጎም ስጦታ ባላቸው ሰዎች የሚተረጎም መሆኑን ነው። በዚህ መሠረት በ1ኛ ቆሮንቶስ የተጠቀሰውን በልሳን የመናገር ስጦታ ታየር እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፡- ‘‘በታላቅ ደስታ ተመስጠው የማስተዋል ኃይልና ሕሊናቸውን መቆጣጠር የማይችሉ፥ አዲስ በሆነ ቋንቋ መንፈሳዊ ስሜታቸውን የሚገልጡ፥ የሌሎችን አስተሳሰብ ለመምራትም ሆነ ለመሳብ የማይችሉ ሰዎች ልምምድ ነው’’ (ሐዋ. 10፡46፤ 19፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡30፤ 13፡1፤ 14፡2፥ 4-6፥ 13፥ 18፥ 23፥ 27፥ 39)።

አንዳንድ ጸሐፊዎች ዘመናዊውን በልሳን የመናገር እንቅስቃሴ* ለመቃወም በሚያደርጉት ሙከራ፥ በልሳን የመናገር ስጦታን የሚያሳንሱ ሲሆን፥ በተናጋሪው የማይታወቅ ቋንቋ የመኖሩን እውነታ ይክዳሉ። እንደ ታየር ያሉ አንዳንዶች ይህን አሳብ በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ያለውን አሳብ ብቻ እንደሚደግፍ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ያለውን ክፍል በማከል፥ አንዳንድ ባዕድ ቋንቋዎችን እና ከውስጥ ስሜት የተነሣ በመፈንደቅ፥ ትርጉም የማይሰጥ ድምፅን (ቃላትን) ማስወጣትን የሚጨምር ንግግር ነው ይላሉ። በልሳን መናገርን በሰዎች እንደሚነገር እንደ ማንኛውም ቋንቋ መሆኑን የማይገልጥ ማንኛውም ዓይነት አመለካከት፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈሳዊ ስጦታ ከሚገልጡት ጋር

---

* በምእራፍ 15 መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአሳታሚውን መግለጫ ይመልከቱ።

ለማስማማት የማይችል አስቸጋሪ አሳብ ነው። መንፈሳዊ ስጦታ በባሕርዩ እውን እና መለኮታዊ በመሆኑ ተፈጥሮአዊ ማብራሪያ አያስፈልገውም። በልሳን መናገርም በአማኞች ዘንድ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ሆኖ ተቀባይነት ያገኘ ነገር ነው። አንዳንዶች እንደሚያደርጉት፥ በልሳን መናገርን ከንቱ መዘላበድ ከሚታይበት ከአረማውያን አምልኮና ከጠንቋዮች አሠራር ጋር ማያያዝ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትክክለኛነት የሚያፋልስ ስለሆነ ልንቃወመው ይገባል።

በልሳን ስለመናገር የተጻፉ ጥቅሶች በሙሉ በመሠረቱ አንድ ናቸው የሚለውን ለዘብ ያለ የተቃውሞ አመለካከት የሚገልጠው የታየር አቋም የተመሠረተው፥ ስለ ስጦታው ባለ የግንዛቤ ጉድለት ላይ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያቶች አሉ። በሐዋርያት ሥራ 11፡15 በግልጥ እንደተጻፈው በቂሣርያ የታየው በልሳን የመናገር ክሥተት፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለት ጊዜ የተፈጸሙት እነዚህ ድርጊቶች በመሠረቱ በሐዋርያት ሥራ 19 ከተፈጸመው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ስለዚህ በጥቅሱ የማናየውን ልዩነት ለመፍጠር መሞከር እውነትነት የሌለውና ትክክለኛ ያልሆነ አተረጓጎም ነው።

በልሳን መናገርን በሚመለከት በሐዋርያት ሥራና በ1ኛ ቆሮንቶስ ያሉት ቃላት ተመሳሳይ መሆን በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ለመግለጥ የሚደረገውን ሙከራ መሠረት ያሳጣዋል። በሁሉም ክፍሎች ልዩ ልዩ ሰዋሰዋዊ አገባቦች 'ላሌዮ' ['laleo'] እና 'ግሎሳ' ['glossa'] የሚሉ ተመሳሳይ የግሪክ ቃላት ናቸው የተጠቀሱት። በግሪክኛውም ሆነ በክፍሉ በቀረበው ዓረፍተ ነገር ምንም ልዩነት አናገኝባቸውም።

አንዳንዶች ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ያለውን ችግር በመተው፥ ልሳንን በሚመለከት በ1ኛ ቆሮንቶስ የምናገኘው ችግር በቆሮንቶስ ሰዎች ዘንድ ያልታወቀውን የዕብራይስጥ ቋንቋ የሚመለከት ነው ይላሉ። ይህን አሳብ በሚመለከት በክፍሉ የምናገኘው ምንም ማስረጃ ካለመኖሩም ሌላ ለተናጋሪዎቹ በተፈጥሮአዊ መንገድ የሚታወቅ ቋንቋ መንፈሳዊ ስጦታ ተብሎ የሚሰየምበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም።

*ለችግሩ መፍትሔ ለማስገኘት የሚጠቅም መመሪያ።* በልሳን የመናገርን መሠረታዊ ትምህርት ለመለየት ልንጠቀምበት የሚገባ ብቸኛውና ትክክለኛው መመሪያ፥ ስለዚህ ጉዳይ የተጠቀሱት ክፍሎች በሙሉ ስለ አንድ ስጦታ የሚናገሩ መሆናቸውን አምኖ መቀበል ነው። በአጠቃቀሱ ላይ አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም፥ በልሳን የመናገር ስጦታ በግልጥ ልንረዳው የምንችለው አሳብ ብቻ ሳይሆን እውነታ መሆኑን፥ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን መለኮታዊ መሆኑን፥ የሥነ-ልቦና ወይም የትምህርት

ጉዳይ ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑንና በተለይም ለማያምኑ ሰዎች የተሰጠ ምልክት መሆኑን በሁሉም ረገድ ልንረዳ ይገባል።

በልሳን የመናገር ስጦታ ለሐዋርያት ጊዜ ብቻ የተሰጠ ጊዜያዊ ስጦታ ወይም ቋሚና በዘመናት ሁሉ የሚሠራ መሆኑን መወሰን የሚቻለው፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ ባለው ቃል ላይ በመመሥረት ብቻ ነው። በልሳን የመናገር ስጦታ እውነተኛ ባሕርይ አስቀድሞ ከተወሰነ ችግሩን ቀላል ያደርገዋል። የተገለጡትን ማስረጃዎች ሁሉ መመርመር፥ በልሳን የመናገር ስጦታ ላለንበት ዘመን በሙሉ የተለመደ ያለመሆኑን እውነት የሚያረጋግጥ ነው።

*በሐዋርያት ሥራ የተገለጠው ልሳን ጠቃሚነቱ እንደ ምልክት ማገልገሉ ነው።* ቀደም ብለን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተመለከትናቸው ሦስት ጥቅሶች (2፡4፤ 10፡46፤ 19፡6)፥ ድርጊቶቹን በአንድነት የሚያጣምር የቃላት አንድነት እንዳላቸው ያሳያሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትና የሰሙትም ሰዎች እንዳረጋገጡት፥ የተጠቀሱት ሁሉ እውነት ናቸው። ሁሉም በባሕርይ መለኮታዊ ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ናቸው። በሦስቱም ጊዜ የሆኑት ነገሮች፥ የምልክትነት ባሕርያቸው እንደተገለጠ መጠቆም መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

አማኞች አሁን የሚጠቀሙበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሙላት የተጀመረው፥ በጰንጠቆስጤ ዕለት ነው። የዳግም መወለድ እውነታ ሙሉ በሙሉ ግልጥ ከመሆኑ ባሻገር አማኞች ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆኑ፤ እስከ መዋጀት ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ታተሙ፤ በመንፈስ ቅዱስም ተሞሉ። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በጰንጠቆስጤ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሥራ ጀመረች። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የሚያሳዩ አንዳንድ ውጫዊ መግለጫዎች ያስፈልጉ ነበር። በልሳን የመናገር ችሎታ እግዚአብሔር በቸርነቱ በውስጣቸው እንደሚሠራ ለማረጋገጥና ወንጌልን ለዓለም ሁሉ የማድረስን የመጨረሻ ዓላማ ለማሳየት ሲባል ተሰጠ።

ለቆርኔሌዎስ ወንጌልን በመስበክ ሥራ ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ሌላ እርምጃ ተወሰደ፥ ምልክትም አስፈለገ። ቀደም ሲል ወንጌል ለአሕዛብ የተሰበከ ቢሆንም፥ አሁን ግን አይሁድ በሚቀበሉበት ሁኔታ አሕዛብም ሊቀበሉ እንደሚችሉ ለማሳየት ተገለጠ። እኩል መብት እንዳላቸውም ታወቀ። ይህ እውነት ለጴጥሮስም ግልጥ ሆኗል፡- እግዚአብሔር በጰንጠቆስጤ ዕለት እንዳደረገው በልሳን መናገርን የሚያጠቃልለውን መለኮታዊ ኃይሉን አሳየ። ምልክት አስፈልጎ ነበር፥ እግዚአብሔር ሰጠ።

ግልጥ ማረጋገጫ ያስፈለገበትን ሦስተኛ ሁኔታ የምናየው ደግሞ በሐዋርያት ሥራ 19፥6 ነው። ምልክቱ ያስፈለገው የማያምኑ ሰዎችን ለማሳመን ብቻ ሳይሆን፥ አማኞችም መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረለትን አውቀው እምነታቸው እንዲጸና ለማድረግ ነበር።

ይህ በልሳን የመናገር ልምምድ ተደግሟል ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። እስካሁን ባየናቸው ሦስት ክፍሎች በልሳን የመናገር ጉዳይ የተፈጸመው በመጀመሪያው የክርስትና ልምምድ ወቅት ብቻ መሆኑን ነው።* የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ተመሳሳይ ስለሆነ ሌላ ልምምድ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም።

ከዚህ እውነታ እንደምንረዳው፥ በልሳን መናገር በምንም አኳኋን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊነት ወይም የደኅንነት ምልክት አልነበረም። በእውነተኛ መልኩ የመገኘቱ ጉዳይ ለደኅንነት እርግጠኝነት ምስክር ነበር፥ ቢሆንም የግድ አስፈላጊ አልነበረም። የሚታየውም አልፎ አልፎ ነበር። የአረማውያን ባዕድ አምልኮና ክፋት በበዛበት ሁኔታ ውስጥ በነበረችው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ እግዚአብሔር ይህንን ስጦታ አትረፍርፎ መለገሱ ግልጥ ነው። ለደኅንነት መነሻ ምልክት በሆነውና በክርስትና ልምምድ ውስጥ ቋሚ በሆነው የልሳን ስጦታ መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል። በሐዋርያት ሥራ 11፥17፥ የቆርኔሌዎስ ልምምድ እንደ ስጦታ ተገልጧል። በሁለቱ መካከል ልዩነት ቢኖርም በመጽሐፍ ቅዱስ ግን አልተጠቀሰም።

*በልሳን መናገር በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ።* በ1ኛ ቆሮንቶስ እንደተገለጠው፥ ስጦታዎችን ለመተንተን አስቸጋሪ የሆነው፥ መልእክቱ በተጻፈላት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ በነበረው መንፈሳዊ ችግር ምክንያት ነው። በማንኛውም ረገድ በጣም ጠቃሚ ስለሆኑ ስጦታዎች ሁሉ የተሰጠው ገለጣ የተሟላ ነው። ይህ ጉዳይ የተነሣው፥ መንፈሳዊ ስጦታዎችና አማኞችም በክርስቶስ አካል ውስጥ ስላላቸው ስፍራ በተነገረበት ክፍል ነው። በልሳን ስለ መናገር የተጠቀሰው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥10፥ 28 ሲሆን፥ በመንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ የመጨረሻው ነው። የስጦታዎቹ ዝርዝር ቅደም ተከተል በአስፈላጊነታቸው መጠን የተደረገ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ስጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ በተገኘ ፍቅር አገልግሎት ላይ ካልዋሉ፥ ዋጋ የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ

* ሀ. በጰንጠቆስጤ ዕለት በክርስቶስ ያመኑ አይሁዶች ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨምረው ነበር። ለ. ከአጭር ጊዜ በኋላ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ወንጌል ደርሶ አሕዛብ ተቀብለውታል። ሐ. የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮች ከሦስት ዓመት በፊት የመጥምቁን ትምህርት ማለት "ንስሐ ግቡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና" የሚለውን ተቀብለው የነበሩ ቢሆንም ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 19፥6 እስካስረዳቸው ድረስ ሙሉ ለሙሉ እውነቱን አልተገነዘቡም ነበር።

እጅግ አስፈላጊ መገለጥ ተሰጥቷል። በልሳን የመናገር ጉዳይ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። በመጀመሪያ በልሳን የመናገር ስጦታ በፍቅር ካልሆነ "እንደሚጮኽ ነሀስ ወይም እንደሚሿሿ ጽናጽል" መሆኑ የተገለጠ ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ልሳን ከትንቢትና ከእውቀት ጋር ጊዜያዊ መሆኑ ተጠቅሷል። "ልሳኖችም ቢሆኑ ይቀራሉ" (ቁ. 8)። ቀጥሎ ያለው ምዕራፍ በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልሳን ስለመናገርና በትንቢት አጠቃቀም ረገድ ስላለው ችግር የሚያወሳ ነው።

ምዕራፍ 14 ውስጥ በርካታ ጠቃሚ ነጥቦች ተጠቅሰዋል። በመጀመሪያ፥ በልሳን መናገር የማነጽ፥ የመምከርና የማጽናናት ጠቀሜታ ካለው ከትንቢት ያነሰ መሆኑ ተጠቅሷል (1ኛ ቆሮ. 14፡1-12)። ከትንቢት ያነሰበት ምክንያት ማንም ሊረዳው አለመቻሉ ነው። በዚሁ ክፍል ትንሽ ዝቅ ብሎ፥ ጳውሎስ እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ሰው ሊገባውና ሊረዳው የሚችል አምስት ቃላት፥ መናገር እንደሚሻል ተናግሯል (1ኛ ቆሮ. 14፡19)።

ሁለተኛ፥ ተርጓሚ እስከሌለ ድረስ በልሳን የመናገርን ስጦታ በጉባዔ መጠቀም ተገቢ እንዳልሆነ ተጽፏል (1ኛ ቆሮ. 14፡13-28)። የቆሮንቶስ ሰዎች ልሳንን በግል የጸሎት ጊዜያቸው ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ የተጠቀሰ ቢሆንም፥ ጳውሎስ ሰው ሊረዳው በሚችልበት መንገድ መጸለይ እንደሚሻል ገልጧል (1ኛ ቆሮ. 14፡15)።

ሦስተኛ፥ ልሳን የተሰጠው ለማያምኑ ሰዎች ምልክት ይሆን ዘንድ እንጂ፥ በቅድሚያ አማኞችን ለማነጽ አይደለም (1ኛ ቆሮ. 14፡21-22)። በልሳን መናገር በሥርዓት እስካልተከናወነ ድረስ የማሳመኑ ተግባር ከግብ አይደርስም (ቁ. 23)። በዚህም ቢሆን ትንቢት የማያምነውን ሰው ወደ እምነትና አምልኮ ስለሚመራ የበለጠ ስፍራ አለው (ቁ. 24-25)።

አራተኛ፥ በልሳን መናገርና የትንቢት ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን በማነጽ ረገድ ብቻ በሥርዓት ጥቅም ላይ መዋል ይገባዋል (ቁ. 26-38)። በአንድ ጉባዔ በልሳን መናገር የሚፈቀድላቸው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ብቻ ሲሆኑ ያውም ተርጓሚ ካለ ነው (ቁ. 27-28)። ሴቶች በማኅበር በልሳንም ሆነ ትንቢት መናገር አልተፈቀደላቸውም (ቁ. 34-35)። "ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን" (ቁ. 40) በማለት ይመክራቸዋል። እነዚህ ሕግጋት በትክክል በሥራ ላይ ቢውሉ በልሳን መናገርን አስመልክቶ በዘመናችን ያለውንና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሠረተውን ጎጂ አሠራር ያስወግዳሉ።

አምስተኛ፥ በልሳን መናገር መከልከል የሌለበት ቢሆንም፥ የነቢይነት ስጦታ ደግሞ የተሻለና አጥብቀን ልንፈልገው የሚገባ ነው (ቁ. 39)።

*በልሳን መናገር ጊዜያዊ ስጦታ ነበር።* ማንም ቢሆን በልሳን መናገር በአሁኑ ጊዜ ሊሆን የማይችል ነው ብሎ በማስረጃ ሊያረጋግጥ አይችልም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አሁን ላለው ዓላማ ስጦታው የማያስፈልግ መሆኑን ማሳየት ይቻላል። ዘመናዊውን በልሳን የመናገር ስጦታ ለማረጋገጥ የሚገለጥ ሁሉም ባይሆን አብዛኛው ከሥነት ሥነ-ልቦናዊ ወይም የአጋንንት ተግባር መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት አለ። ከሁሉ የተሻለው ማስረጃ በልሳን መናገርን አስመልክቶ ባለው ታሪክ* ውስጥ ከልክ ያለፈና አብሮት ይገለጥ የነበረ ክፉ ባሕርይ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ እውነተኛ ክርስቲያኖችም በልሳናት እንናገራለን ከሚሉት ጋር መቀላቀላቸው የሁሉንም ልምምድ መመርመር የማይቻል አድርጎታል። በልሳን የመናገር እንቅስቃሴ ክፋት መነሻው በልሳን ከመናገር እምነት አይደለም። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ስጦታዎች የሚያስተምሩትንና ስለአጠቃቀማቸው የተሰጠውን ትምህርት ቸል ከማለትና በዘመናዊው የእምነት ትምህርት በልሳን ስለመናገር የሚሰጠው የተሳሳተ ትምህርት ነው።

በልሳን የመናገር ስጦታ ጊዜያዊ እንደሆነ የሚያረጋግጡ አራት የተለያዩ የመከራከሪያ አሳቦች አሉ። በመጀመሪያ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ የተጀመረው በጰንጠቆስጤ ዕለት ነው። ከዚህ ታሪካዊ ድርጊት አስቀድሞ ክርስቶስም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ በልሳን ስለመናገራቸው የተጻፈ ነገር የለም። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በወንጌላት ጊዜ ያልተሰጠ መንፈሳዊ ስጦታ ነው። ስጦታው የተጀመረው በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በጰንጠቆስጤ ዕለት ከሆነ፥ በሱ ፈቃድ ሊቋረጥ ይችላል።

ሁለተኛ፥ ልሳን ለእስራኤል ምልክት የመሆን ባሕርይም አለው። የጸጋ ዘመን በሚጀመርበት ጊዜ፥ የወንጌል መልእክት ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲህ ያለው ምልክት አስፈላጊ ነበር። በነቢያት የተነገረ ስለሆነ፥ ትንቢቱ መፈጸም ነበረበት። ኢሳይያስ "በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል" ሲል ተንብዮ ነበር (ኢሳ. 28፥11)። ይህ የኢሳይያስ ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፥21-22 ተጠቅሷል፦ "ሌሎችን ልሳኖች በሚናገሩ ሰዎችና በሌላ አንደበት ለዚህ ሕዝብ እነግራቸዋለሁ፥ እንዲህም ቢሆን አይሰሙኝም ይላል ጌታ ተብሎ በሕግ ተጽፏል። እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።" ትንቢቱ ሙሉ በሙሉ የተፈጸመ በመሆኑ ምልክቱ የሚያስፈልግበት ሌላ ምክንያት የለም።

---

* ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ፥ ስለ ሞንታነስና ትምህርቱ በገጽ 297 ላይ የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

ሦስተኛ፥ በሐዋርያነት፥ በነቢይነት፥ ተአምራትን በማድረግና በፈውስ ስጦታ እንዳየነው፥ አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት ለጊዜው ነበር። በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን አገልግሎት ያገዙና ያልተለመዱ ምልክቶች የታለመላቸውን ተግባር ካከናወኑ በኋላ መወሰዳቸው የእግዚአብሔር ዓላማ ይመስላል።

አራተኛ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ እንደሚያበቃ አስቀድሞ ተነግሯል (1ኛ ቆሮ. 13፥8)። በአገባቡ መሠረት ልሳን የተጠቀሰው፥ በልሳን ስለ መናገር ስጦታ ነው ለማለት ይቻላል። በተለይ ስለዚህ በሚናገሩ ጥቅሶችና በሌሎችም አመልካች ጥቅሶች ላይ በመመሥረት፥ በልሳን የመናገር ስጦታ ለሐዋርያት ዘመን በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ መገለጡን ለማየት እንችላለን።

ስጦታውን ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመጠቀም አደገኛነት። ከ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት በግልጥ እንደምንረዳው፥ በልሳን መናገር በባሕርይው ለተሳሳተ አጠቃቀም የተጋለጠ ነው። ይህን በአሳባችን ይዘን፥ በማጠቃለያ ላይ አንዳንድ እውነታዎችን እንደገና ማንሣት እንችላለን።

በመጀመሪያ፥ የምንመለከተው በልሳን መናገር፥ ከስጦታዎች ሁሉ አነስተኛው መሆኑን ነው። በመሆኑም የታላቅ መንፈሳዊ ኃይል ወይም ጠቀሜታ ማስረጃ ሆኖ ከፍተኛ ስፍራ ሊሰጠው አይገባም። በአንዳንድ የእምነት ክፍሎች የተሰጠው ስፍራ ከቅዱሳት መጻሕፍት አሳብ ጨርሶ የራቀ ነው።

ሁለተኛ፥ በልሳን መናገር በማንኛውም ረገድ የደኅንነት ማስረጃ አይደለም። በባሕርይው ስጦታ በመሆኑ በሐዋርያት ዘመን እንኳን ስጦታው የነበራቸው ክርስቲያኖች ሁሉ እንዳልነበሩ ግልጥ ነው። ከሐዋርያት ሥራና ከ1ኛ ቆሮንቶስ ውጪ፥ በሌላ ስፍራ አለመጠቀሱ እምብዛም አስፈላጊ ያለመሆኑን ያመለክታል። በልሳን መናገር እንደ ውጫዊ የደኅንነት ምልክት አስፈላጊ ሆኖ ቢቆጠር ኖሮ፥ በደኅንነት ዕቅድ ውስጥ ዋና ስፍራ ይሰጠው ነበር። የዮሐንስ ወንጌልም ሆነ ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከው መልእክት ስለ ልሳን ምንም አለመናገራቸው፥ በጉዳዩ ልንጠነቀቅ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ሦስተኛ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ የመንፈሳዊነት ምልክት አይደለም። ጳውሎስ ከጻፈላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሥጋዊነትና የጅምላ ኃጢአት የሚገኘው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ሳለ፥ በልሳን የመናገር ስጦታ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይልቅ በዚያችው ቤተ ክርስቲያን ይታይ እንደነበር ግልጥ ነው። በልሳን የመናገር እንቅስቃሴ ወደ ቅድስና አለመምራቱ በታሪክ የታየ ጉዳይ ሲሆን፥ ከመጠን በላይ የመሆኑ

ነገርም ወደ ጥፋት መርቷል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እግዚአብሔርን የሚመስሉ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ከማንኛውም ዓይነት በልሳን የመናገር ልምምድ የራቁ ነበሩ።

አራተኛ፥ በልሳን መናገር ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይለያል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 መሠረት እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል። ክርስቲያኖች ሁሉ ግን በልሳን አይናገሩም። በልሳን መናገርን ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚያበቃ አድርጎ የማቅረብ ሙከራ የቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከመረዳት በርካታ ስሕተቶች መካከል አንዱ ነው።

## 7. በልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ

በጥንት ቤተ ክርስቲያን ለአንዳንዶች በልሳን የመናገር ስጦታ ከመስጠቱ ጋር የተነገረውን የሚተረጉሙ ሌሎች ሰዎች ያስፈልጉ ነበር። በልሳን የመናገር ስጦታ ከነቢይነት በግልጥ የተለየ ቢሆንም፥ በአንዳንድ ሁኔታ የመገለጥ መነሻ ሆኖ ነበር። ብዙውን ጊዜ ከልዩ ደስታ ጋር የተያያዘ ክብር መስጠትና አምልኮ ነው። በልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ (1ኛ ቆሮ. 12፡10፥ 14፡26-28)፥ በልሳን የተነገረውን ነገር የመተርጎም መለኮታዊ ችሎታ ነው። በልሳን የመናገር ስጦታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሌለ፥ የመተርጎም ስጦታም በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ ካለው የእግዚአብሔር ዓላማ ውጭ የሆነና ያለፈ ነገር ነው።

## 8. መናፍስትን የመለየት ስጦታ

በቃል የሚሰጡ ብዙ የተለያዩ መገለጦች በነበሩባት ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን፥ እውነቱን ከሐሰት ለመለየት መለኮታዊ እገዛ ያስፈልግ ነበር። ሰይጣን አሁን እንደሚያደርገው ማንኛውንም የማጭበርበሪያ መሣሪያ ይጠቀም ነበርና መናፍስትን የመለየት ስጦታ (1ኛ ቆሮ. 12፡10)፥ በቃል የተሰጠውን ሰማያዊ መገለጥ እውነተኝነት ከሐሰት ለመለየት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጥ ችሎታ ነበር። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስላልተጠናቀቁ፥ ከብሉይ ኪዳን በቀር ምንም ዓይነት የጽሑፍ ማረጋገጫ ያኔ አልነበረም። አዲስ ኪዳን በእጃችን ከገባ በኋላ ግን ይህን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የማያስፈልግ አደረገው።

በክርስቲያኖች ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ፥ ስሕተትን ሁሉ በመግለጥ የሚረዳ መሆኑ እርግጥ ነው። በ1ኛ ዮሐንስ 2፡27 እንደተገለጠው፥ “እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፥ ነገር ግን የእርሱ

ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ” የሚለው ቃል ሁለንተናዊና የእያንዳንዱ ክርስቲያን ንብረት ነው።

አማኞች ምንጊዜም አደገኛ ወደሆነ ስሕተት እንዳያመሩ “መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ እንዲፈትኑ” (1ኛ ዮሐ. 4፡1) ተመክረዋል። መመርመሪያውም፡- “ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው የሚል ነው” (1ኛ ዮሐ. 4፡2)። እዚህ ላይ መንፈስ የሚለው ቃል የሰው ልጆችን የሚያመለክት እንደሆነ ለመገመት ይቻላል። በዚህ መሠረት ማንኛውም የሥነ-መለኮት መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱን ማመን አለማመኑ በማንኛውም አማኝ ይፈተናል። አንዳንድ ሰባኪዎችን እንደሚገጥማቸው፥ በአጋንንት የተያዙ ሰዎችን በሚመለከት የእነዚህን ሰዎች ማንነት በዚህ መመዘኛ ዘዴ መፈተን መቻሉ አያጠራጥርም። ነገር ግን በማንኛውም ረገድ መናፍስትን የመለየት ስጦታ ያቆመ ይመስላል። በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች የሚታመኑት የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ቅዱስ ባበራላቸው መጠን ሲሆን፥ ለክርስቲያኖች ሁሉ ከሚሆነው ውጭ መናፍስትን የመለየት ሥልጣን የመስጠቱ ነገር አብቅቷል።

የመንፈሳዊ ስጦታዎች መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር ጸጋ፥ ለሉዓላዊነቱ፥ ለጥበቡ እንዲሁም ለችሮታው ሌላ ምስክር ነው። በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን መለኮታዊ ዓላማ የማሟላት ምስጢር በአምላካዊ አሠራር መሠረት ይገለጣል። ይህም በተሻለ መንገድ ሊታይ የሚችለው፥ በእግዚአብሔር ታምኖ ለፈቃዱ ራስን በፍቅር በመስጠት ነው።

# 21

# የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባሕርይ

## 1. የትምህርቱ መሠረታዊ አስፈላጊነት

ከተግባራዊ አመለካከት አንጻር ስናየው፥ ለክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን ያህል እጅግ አስፈላጊ ትምህርት የለም። በእግዚ የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ከተግባራዊ ተዛምዶው ጋር እጅግ የተተወና የተረሳ ትምህርት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሠረታዊ ትምህርት ከሥነ-መለኮት እውቀት በተጨማሪ የተግባራዊ ልምምድን እውነት ይጠይቃል። ስለ ሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ስንነጋገር፥ ተግባራዊ ለሆነው የሕይወት ልምድ እጅግ ጠቃሚ መሠረት የሆኑ የእምነት ትምህርቶችን ከቅዱሳት መጻሕፍት እውነታ ጋር በማጣመር መሆኑን ልናስታውስ ይገባል። ብዙ ሰዎች ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ትምህርት መሠረት የሚሆኑትን፥ እንደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር፥ ዳግም ልደትና መታተም ያሉትን ሌሎች መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በሚገባ ሳይረዱ ጉዳዩን ለመግለጥ ሙከራ አድርገዋል። ሌሎች ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ሙሉ በሙሉ ትተውና በልምምድ ላይ ብቻ ተመሥርተው ውሳኔ ላይ ደርሰዋል። ስለዚህ በፊታችን ያለው ተግባር፥ ይህን መሠረታዊ ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት፥ በተለይም በክርስቲያናዊ ልምምዶች ውስጥ አጉልቶ መግለጥ ይሆናል። ስለዚህ ይህ ርእስ በዚህ ክፍል በሦስት አቅጣጫዎች ይገመገማል። እነርሱም፦ 1. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባሕርይ፥ 2. ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮች፥ 3. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤት ናቸው።

## 2. የመንፈሳዊ ልምምድ ተቀዳሚ ምንጭ

የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ባሕርይ በጥንቃቄ በምንመረምርበት ጊዜ፥ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ የመንፈሳዊ ልምምዶች ሁሉ ምንጭ እርሱ መሆኑን እንረዳለን። በዚህ መልኩ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከደኅንነት በፊት ከሚሆኑ እንደ መውቀስ ካሉ ሥራዎችም ሆነ፥ በደኅንነት ጊዜ ከሚፈጸሙ አገልግሎቶች ሁሉ የተለየ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ ግልጥ ይሆናል። እነዚህን መደምደሚያዎች የሚደግፉ መሠረታዊ እውነቶች የሚገኙት፥ ለሙላት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎችና ውጤቶች ጨምሮ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን በሚወክለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።

## 3. የተለያዩ መንፈሳዊ ልምምዶች

እጅግ ሰፊና በርካታ የሆኑ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ልምምዶችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘውን ያህል የትም አናገኝም። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፡- "በዕለታዊ የክርስቲያኖች አኗኗር ውስጥ የባሕርይና የብቃት ልዩነት መኖሩ አያጠራጥርም። ይህ ልዩነት በአዲስ ኪዳን ውስጥም የታወቀና ግልጥ ነው" ብሏል። ቅዱሳት መጻሕፍት በዳነውና ባልዳነው ሰው መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት በርካታና ግልጥ በሆኑ ቃላት የገለጡ ሲሆን፥ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ልዩነት ግን በዚህ የሚያበቃ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ "በመንፈሳዊ" እና "በሥጋዊ" ሰው መካከል (1ኛ ቆሮ. 2፡9-3፡4) "እንደ ሰው ፈቃድ" በሚመላለሱና "የበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ" በሚያፈሩ (1ኛ ቆሮ. 3፡3፤ ቈላ. 1፡10) መካከል ያለውን ልዩነት ያቀርባል። በእነዚህ ተደጋጋሚ ንጽጽሮች የሚታየው ልዩነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው ግንኙነት መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። በዚህ መሠረት ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዲህ ሲል ጽፏል፡- "ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ" (ገላ. 5፡16)።

## 4. መንፈሳዊነት ከብስለት ጋር ሲነጻጸር

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ የሆነው መንፈሳዊ ልምምድና በረከት፥ አስፈላጊ ከሆነ ሌላ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ይኸውም ከክርስቲያን በጸጋ ማደግ ጋር ተነጻጽሯል። ማንኛውም ክርስቲያን፥ አዲስ የተወለደ ቢሆን፥ መንፈሳዊ ቢሆን፥ በመንፈስ ቢመላለስ፥ በክርስቶስ ውስጥ ቢኖር፥ እስኪሞት ወይም ክርስቶስ የራሱ ለሆኑት እስኪመጣ ድረስ እርሱን ወደመምሰል ቀስ በቀስ በሚከናወን መንፈሳዊ እድገት ውስጥ ይኖራል። ይህ ዝግተኛ እድገት በግለሰቡ መንፈሳዊነት ላይ በተወሰነ መጠን የተመሠረተ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ቁጥጥር ሥር ስለሆነ፥ በመጨረሻ ፍጹምነትን እንደሚያገኝ ለክርስቲያን ቃል ተገብቶለታል። ይህ ጉዳይ በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሱ፥ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ዋና ነገር መሆኑን የሚያሳይ ነው። ለአጨዳ እስኪደርስ ድረስ ስንዴውና እንክርዳዱ በአንድነት ያድጋሉ (ማቴ. 13፡30)። ስጦታው ያላቸው ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን የመሰጠታቸው ዓላማ የሚከተለው ነው፡- "ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል

ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ. . . ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም። ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ" (ኤፌ. 4፡12-13፥ 15)። ክርስቲያኖች፡- "ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ" ተብለው ተመክረዋል (1ኛ ጴጥ. 2፡2)። ደግሞም፥ "ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ" ተብለው ተመክረዋል (2ኛ ጴጥ. 3፡18)።

በክርስቲያን የጸጋ እድገትና መንፈሳዊነት መካከል እጅግ አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ። ክርስቲያን በሰማይ ፍጹምነት እንደሚያገኝ የተረጋገጠ ቢሆንም፥ በምድር ላይ እያለም ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርስ ከፍተኛ ማበረታቻ ተሰጥቶታል። ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለመድረስ ከዚህ የቀስ በቀስ ሂደት ውጭ የተሰጠው መንገድ ባይኖርም፥ ሁኔታዎችን አሟልቶ ከተገኘ፥ በአንድ ጊዜ ወደ መንፈስ ቅዱስ በረከት ሙላት ለመግባት ይችላል። በሥጋዊ አካል እድገት የጤንነትና የመጎልመስ ሂደት እንዳለ ሁሉ በመንፈሳዊነት ውስጥም ተመሳሳይ ሂደት አለ። አንድ ሕፃን በእድገት አንጻር ገና ያልበረታ ሆኖ ፍጹም ጤነኛ ሊሆን ይችላል። የአካል እድገት ጊዜ ይጠይቃል፤ ጤንነት ግን አካል አሁን ባለበት ሁኔታ የሚያገኘውን ደስታና እድገት የሚወስን ነው። በመንፈሳዊው ዓለምም አዲስ የተወለደ ሰው እድገቱ ከበሰለ ክርስቲያን ጋር የሚወዳደር ባይሆንም፥ የመንፈስ ሙላት ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን በመንፈሳዊነትና በብስለት መካከል በጣም አስፈላጊ ግንኙነት አለ። አንድ ቅዱስ ሰው በሥጋዊነት በመመላለስ ፋንታ ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረትና በመንፈስ ሙላት መኖር ሲጀምር፥ በእምነቱ በፍጥነት ያድጋል። "በክርስቶስ ሕፃን ነው" የምንለው ሰው፥ ወደ አንድ የተወሰነ የብስለት ደረጃ ለመድረስ ጊዜ የነበረው፥ ነገር ግን እድገቱ በሥጋዊነት የተገታበት ሰው ነው። የሥጋዊ አካል ጤንነት ለሥጋዊ አካል እድገት የሚያበረክተው ድርሻ እንዳለ ሁሉ፥ የመንፈስ ሙላትም ለመንፈሳዊ እድገት የሚያበረክተው ነገር አለ።

አንድ ክርስቲያን ብስለት ባይኖረው እንኳ፥ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች ካሟላ፥ ወደ መንፈሳዊነት ወዲያውኑ ይደርሳል የሚለውን አሳብ የሚቃወሙ አመለካከቶችም አሉ። ክርስቲያኖች መንፈስ በሙላት እንዲኖርባቸው የተሰጠው የማበረታቻ ምክር ከእነዚህ አመለካከቶች የተለየና የሚቃረን ነው። ጄ. ኢስት ሄሪሰን [J. East Harrison] እንዳለው፡-

> "በዝቅተኛ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች በዚያው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን የሚሻልና የሚበልጥ ነገር አለ በሚለው አሳብ ቅር ይሰኛሉ። ሌሎች ደግሞ ሁልጊዜ በማጉረምረምና

በማልቀስ፥ ምድረ በዳና አስከፊ በሆነው መንገዳቸው ይጓዛሉ። በሁለቱም ሁኔታዎች በቃል ሊገለጥ የማይችል ኪሳራ አለ። ጉድለት በሞላበት በዚህ ምስክርነታቸውና አሳዛኝ በሆነው ባሕርያቸው አማካይነት በክርስትና ላይ ሳይቀር ጉዳት አድርሰዋል።''

ስለዚህ የመንፈሳዊ ልምምድ የተለያዩ ገጽታዎች የሚፈጠሩት የመንፈስ ሙላትና መንፈሳዊ ብስለት ከምንላቸው ሁለት ነገሮች የተነሣ ነው። ከሁለቱ በመንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ የመንፈስ ሙላት እጅግ አስፈላጊ ነው። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች በተገቢው ሁኔታ ተስተካክሎ በሚኖር ግን ባልበሰለ ክርስቲያን እንኳ ሊታወቁ ይችላሉ። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፥ መንፈስ በሙላት በማረከው በማንኛውም ክርስቲያን ውስጥ እንዲታይ የእግዚአብሔር እቅድ ነው። አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው የሚያከናውነውን ሙሉ አገልግሎት ያለማወቃቸው ግልጥ እውነት ሲሆን፥ ይህ የእውነትን አንድ ገጽታ የማወጅ አገልግሎት፥ ቤተ ክርስቲያን ልትወጣው የሚገባት ዋና ሥራ መሆኑን ያሳያል።

## 5. በውስጣችን ያደረውና ሊታገድ የማይችለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት

"የመንፈስ ቅዱስ አማኝን የመሙላት ሥራ"፥ አማኙ ራሱን ሙሉ በሙሉ በውስጡ ላደረው መንፈስ ቅዱስ በሚሰጥ ጊዜ በሕይወቱ የሚፈጸም አገልግሎት ነው ብለን በቀላሉ ልንተረጉመው እንችላለን። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገር ማንኛውም ጥቅስ፥ በተሞላው ሰው ሕይወት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ተቆጣጣሪነት ምክንያት የመጣን መንፈሳዊ ሁኔታ ያመለክታል። በወንጌላት የተጠቀሰውን ጨምሮ በአዲስ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገሩ አሥራ አራት ጥቅሶች አሉ። 'ፒምፕሌሚ' ['pimplemi'] የሚለው የግሪክ ግሥ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስምንት ጊዜ ተጠቅሷል (ሉቃስ 1፡15፥ 41፥ 67፤ ሐዋ. 2፡4፤ 4፡8፥ 31፤ 9፡17፤ 13፡9)። የዚሁ ግሥ ሌላ ቅርፅ የሆነው 'ፕሊሩ' ['pleroo'] የሚለው ቃል ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል (ሐዋ. 13፡52፤ ኤፌ. 5፡18)። እሳቡን ለመግለጥ ሥራ ላይ ከዋሉት ከእነዚህ ሁለት ግሦች ሌላ 'ፕሊሬስ' ['pleres'] የሚለው ቅጽል አራት ጊዜ ተጠቅሷል (ሉቃስ 4፡1፤ ሐዋ. 6፡3፤ 7፡55፤ 11፡24)።

ከእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የምንገነዘበው፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ያለምንም መከልከል በነጻነት

የሚያገለግላቸው መሆኑን ነው። ይህ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚፈጸም የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን የሚያሳይ ውጫዊ ማረጋገጫም ይገኛል። አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራን መሥራት የቻሉት መንፈስ ቅዱስ ላቅ ባለ ሁኔታ ስለተሰጣቸው ነው ማለት ትክክለኛ አባባል አይደለም። አማኞች ሁሉ ዳግም በተወለዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል። ስለዚህ የአማኝ መንፈሳዊ እድገት ወይም ሥራ የሚወሰነው፥ ግለሰቡ ፍላጎቱንና ዝንባሌውን ደግሞም ራሱን በፈቃደኝነትና ሙሉ በሙሉ በመስጠት የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱ እንዲከናወን በማድረጉ ላይ ነው። ዋናው ነገር እግዚአብሔር ይበልጥ በውስጣችን ይሁን ማለት ሳይሆን እኔነትንና የሥጋ ፍላጎትን ጥሎ፥ የእግዚአብሔር ኃይል በእኛ ውስጥ እና በእኛ እንዲሠራ ማድረግ ነው።* ምንም እንኳን አማኞች "የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ" (1ኛ ቆሮ. 6፡19) እንደሆኑ ቢታወቅም፥ ብዙዎች ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ በሚገባ አለመስጠታቸው የሚያሳዝን ነው። በዚህ የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸው የነበረ ገደብ የለሽ የበረከት አገልግሎት በሕይወታቸው አይታይም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገሩ የተለያዩ ክፍሎች ጥናት ይህን ሁኔታ ግልጥ ያደርገዋል። በሉቃስ 4፡1 መሠረት ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ይህም ከሥላሴ አካላት አንድነት በላይ የሚናገር ሲሆን፥ በተለይ ለክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ የተሰጠ አገልግሎት መሆኑን እናያለን። መጥምቁ ዮሐንስ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ እንደሚሆን አስቀድሞ ተተንብዮአል (ሉቃስ 1፡15)፤ እናቱ ኤልሳቤጥና አባቱ ዘካርያስም በተለያየ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር (ሉቃስ 1፡41፥ 67)። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚናገሩና በወንጌላት የሚገኙ እነዚህ ክፍሎች በብሉይ ከነበሩት ጋር ይመሳሰላሉ (የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ይመልከቱ)። ይህ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዓላማ የሚመራና ጊዜያዊ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንጂ፥ አሁን እንደሚሆነው ራሳቸውን ለሰጡ ቅዱሳን ሁሉ የሚሆን ሁለንተናዊ መብት አይደለም። በሐዋርያት ሥራና በኤፌሶን ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ የሚያመለክቱት ጥቅሶች ሁሉ በዚህ ስፍረ-ዘመን ስለተለመዱ ተግባራት የሚናገሩ ናቸው።

የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ቀስ በቀስ የተገለጠ ሲሆን፥ የአገልግሎቱ አንዳንድ ሁኔታ ግን የሐዋርያትን ውክልና

---

* ዲ. ኤል. ሙዲ [D. L. Moody] (1837-89) "ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለጌታ ፍቃድ በማስገዛት እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን የሚሠራበትን ሰው ዓለም እስካሁን አላየችም። በእግዚአብሔር እርዳታ ያ ሰው እኔ እሆናለሁ" ብሎ ተናግሮ ነበር። በእርግጥ እግዚአብሔር ይህን ትሑት ሰው በሺ የሚቆጠሩ ነፍሳትን ለደኅንነት ወደሚያበቃ እምነት ለማምጫ ተጠቅሞበታል።

የሚጠይቅ ነበር። ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ማንኛውም የአገልግሎት ሁኔታ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡ ክርስቲያኖች ውስጥ ብቻ የሚገኝ እንደሆነ እናያለን። በዚህ መሠረት በሐዋርያት ሥራ 2፡4፥ በጴንጠቆስጤ ዕለት በስገነት ሆነው ይጠባበቁ የነበሩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን ተረድተናል። እግዚአብሔርን ለማክበር ይሻ የነበረው ጴጥሮስ በካህናት አለቆች ጉባዔ ፊት በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ (ሐዋ. 4፡8)። ጥንት ክርስቲያኖች ከጸለዩ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ እናያለን (ሐዋ. 4፡31)። የመጀመሪያዎቹን ዲያቆናት ለመምረጥ ያስፈልግ የነበረው መመዘኛ "መንፈስ ቅዱስ .... የሞላባቸው" መሆናቸው ነበር (ሐዋ. 6፡3)። እስጢፋኖስ በገዳዮቹ ፊት ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር" (ሐዋ. 7፡55)። ጳውሎስ የጌታ መልእክተኛ የሆነውን ሐናንያን ከተቀበለ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ (ሐዋ. 9፡17)። በዚህ ሁኔታ የምናየው ያልተለመደ ነገር ሐናንያ እጅ እስኪጭንበት ድረስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ አለመሞላቱ ነው። ይህም ሐናንያ የእግዚአብሔር መልእክተኛ መሆኑን ለማሳየት የተደረገ ጊዜያዊ ሁኔታ ነበር። ቆየት ብሎም ጳውሎስ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላቱ የምናየው ነገር አለ (ሐዋ. 13፡9)። በርናባስም "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር" (ሐዋ. 11፡24)። "በአንጾኪያና በጲስድያ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ደስታና መንፈስ ቅዱስ እንደሞላባቸው" እናያለን (ሐዋ. 13፡52)። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የተነገረው እያንዳንዱ ታሪክ፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው የሚለውን መሪ አሳብ የሚገልጥ ነው።

## 6. በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ትእዛዝ

አማኝን በመሙላት ረገድ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ልዩ የሚያደርገው፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን እንዲሞላ የታዘዘ መሆኑ ነው። በኤፌሶን 5፡18 መሠረት ሁሉም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ኃላፊነት አለበት፦ "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ።" ከዚህ አንጻር የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በቀጥታ ይነጻጸራል። ሰዎች ለወንጌል እንዲገዙና በክርስቶስ እንዲያምኑ እንጂ፥ ዳግም መወለዳቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸውና መጠመቃቸው በሥጋ ጥረት እንዲሆን አልታዘዙም። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች፥ ሰው በክርስቶስ አምኖ በሚድንበት ጊዜ ወዲያውኑ የሚገኙ ናቸው። የክርስቲያንን መንፈሳዊ ሕይወት ሳይሆን ደኅንነቱን ይመለከታሉ። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ይሞሉ

ዘንድ ታዘዋል። በእርግጥ ማንኛውም ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት በምኞት ወይም በመፈለግ ብቻ አያገኘውም። ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት አስፈላጊ የሆነው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጧል። እነዚህን ራስን የመስጠት መመዘኛዎች ማሟላት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በክርስቲያኑ ሕይወት ከተገለጡ ያ ሰው በመንፈስ ቅዱስ መሙላቱ አያጠራጥርም።

ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ከመታዘዛቸው እውነታ አንጻር፥ በመንፈስ ያልተሞሉ ክርስቲያኖች የመኖራቸው ነገርም ግልጥ ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ሌሎቹን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ይፈልግ ዘንድ አልታዘዘም። ምክንያቱም አገልግሎቶቹ በባሕርያቸው በደኅንነት የሚገኙ ናቸውና። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለዳኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ ነገር ቢሆንም፥ የደኅንነት አካል ግን አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር በቀጥታ በተነጻጻሪነት የቀረበ መሆኑም ግልጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል የሚሆንበት መንገድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ጋር መነጻጸር አለበት። ምክንያቱም ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆኑት ከደኅንነታቸው ቅጽበት ጀምሮ ሲሆን (ሮሜ 8፡9)፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉት ግን አንዳንዶች ብቻ ናቸው። ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ እስካልተሞላ ድረስ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ነው ሊባል አይችልም። ይህ ለክርስቲያኖች ሁሉ በእኩልነት የተሰጠ ኃላፊነትና መብትም ነው። የማያምኑትን ግን ጨርሶ አይመለከትም።

## 7. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በተደጋጋሚ የሚፈጸም ልምምድ ነው

ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሠረታዊ ትምህርት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያለው በኤፌሶን 5፡18 ይሙላባችሁ በሚለው ትእዛዝ ውስጥ ያለው ግሥ ነው። 'ፕሌሮስቴ' ['plerousthe'] የሚለው ግሥ የአሁን ጊዜንና ትእዛዝን ያዘለ ነው። የአሁን ጊዜን አሳብ ያዘለ መሆኑ "ሳታቋርጡ ተሞሉ" የሚል ትርጉም እንዲኖረው አድርጎታል። በተነጻጻሪነት የቀረበው በወይን ጠጅ የመስከር አሳብም ግልጥ ነው። በጥቅሱ እንደተገለጠው ያለማቋረጥ በወይን ጠጅ ከመስከር ፋንታ፥ በአጠቃላይ በእርሱ ኃይልና ተጽዕኖ ሥር ይሆኑ ዘንድ፥ ክርስቲያኖች ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለባቸው። የአንድ ግሥ የአሁን ጊዜ ትእዛዝ ማስተላለፊያ ይዘቱ የማያቋርጥ አሳብን

ያዘለ ነው። ይህን መሰሎቹ ግሦች አዲስ ኪዳን ውስጥ በመደበኛነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆኑ ቋሚ አሳብን ለመግለጥ አገልግለዋል። ይህ አሳብም እዚህ ስፍራ ላይ ትልቅ ዋጋ አለው። የሚቀጥልን አሳብ ለማመልከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በማዘውተር ጥቅም ላይ ውሎ የሚገኘው ሰዋስዋዊ አጠቃቀም "የትእዛዝ አንቀጽ" ነው። ይህ አጠቃቀም በዚህ ነጥብ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ይህ አገባብ በግልጥ የሚያመለክተው መሠረታዊ አሳብ፥ የማያቋርጥ የመንፈስ ቅዱስ የመሙላት አገልግሎትን ነው።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በተሰጠው ትእዛዝ ውስጥ ዓረፍተ ነገሩ በአሁን ጊዜ መጻፉ፥ ከንውኑ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የማያቋርጥ አገልግሎት መሆኑን ያሳያል። በኃጢአት ሊታገድ የሚችል ቢሆንም የዕለት ተዕለት ግንኙነት ነው። "ሁለተኛው የጸጋ ሥራ"* (ወይም "ዳግመኛ በረከት") ተብሎ የሚታወቅ ነገር ወይም የአንድ የተወሰነ ጊዜ ታሪካዊ ልምምድ አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጫዊ ማረጋገጫ የተለያየ ቢሆንም፥ መሠረታዊው ጉዳይ እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት ሁሉ የደነገገው ልምምድ መሆኑ ነው። ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን እውንነት በሕይወቱ ሲለማመድ፥ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት አገልግሎት በሚገባ ይገነዘበዋል።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሰው ሕይወት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚፈጸም ተግባር ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ወሳኝ ምስክር ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በጰንጠቆስጤ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች (ሐዋ. 2፡4)። በሐዋርያት ሥራ 4፡8፥ ጴጥሮስ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላቱ የተጻፈ ነገር አለ። በጉባዔው መካከል እሱ ያቀረበውን የመከላከያ ገለጣ ለመስማት በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ (ሐዋ. 4፡31)። በመንፈስ ቅዱስ በመሞላቱ ምክንያት አስቀድሞ ለዲቁና ተመርጦ የነበረው እስጢፋኖስ፥ በሰማዕትነት በመሞቻው ቅጽበት "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ" እንደነበር ተገልጧል (ሐዋ. 7፡55)። ጳውሎስና በርናባስ በተለያየ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው እንደነበር ተጽፏል (ሐዋ. 9፡17፤ 11፡24፤ 13፡9፥ 52)። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልምምድ መሆኑ በተጠቀሱት ሁኔታዎች በማስረጃ ተጠቅሷል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አገልግሎት በሚያመለክተው መሠረት፥ በዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጥናት የምንደርስበት ማጠቃለያ ይህ አገልግሎት በርከት ያሉና የተለያየ ደረጃ ያላቸው መንፈሳዊ ልምምዶች እንዲኖሩ የሚያስችል መሆኑን ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ራሱን ሙሉ

---

* በምእራፍ 15 መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአሳታሚውን መግለጫ ይመልከቱ።

በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር በሰጠ ሰው ሕይወት የሚፈጸም አገልግሎት መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ይታያል። የክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሁለንተናዊ ኃላፊነት ግልጥ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ተደንግጓል። ክርስቲያን ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላቱ ነገር በቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ልምምድ ታይቷል። በማንኛውም ሁኔታ የሚከናወን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በደኅንነት ወቅት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሚፈጸሙት ማለት፥ ከዳግም ልደት፥ መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ከማደሩ፥ ከመታተምና ከጥምቀት ከንውን ጋር በቀጥታ በተነጻጻሪነት የሚቀርብ ነው።

# 22

# ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር፥ "መንፈሳዊው ሰው" በሚል ርእስ ስለ መንፈስ ቅዱስ በጻፈው እውቅ ሥራው፥ እንዲሁም፥ "ሥርዓታዊ የሥነ-መለኮት ትምህርት" በተሰኘው ባለ ስምንት ቅጾች መጽሐፉ ስድስተኛ ቅጽ ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት አስፈላጊ የሆኑ ወይም መሟላት ያለባቸው ነገሮች በሚለው ርእስ ሥር ቀላልና ውጤታማ የሆነውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኘውን ዝርዝር ጠቁሟል። በዚያ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሟላት ያለባቸው ሦስት ነገሮች ተጠቅሰዋል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19፥ "መንፈስን አታጥፉ" የሚል ትእዛዝ ይገኛል። በኤፌሶን 4፡30 ደግሞ፥ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ሦስተኛ፥ በገላትያ 5፡16 ልንከተለው የሚገባን ትእዛዝ ተሰጥቷል፡- "ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።"

እነዚህ ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በመለኮት የታቀዱና ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያመለክታሉ። በርካታ መንፈሳዊ ልምምዶች ቢኖሩም፥ ሁሉም ከእነዚህ ሦስት ቀላል ትእዛዛት ጋር ይያያዛሉ። እነዚህ ጥቅሶች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላትን ሁኔታ ለመረዳት እንደ ቁልፍ ያገለግላሉ ቢባል የተጋነነ አይሆንም። ለሽንፈትና ለመንፈሳዊ ድካም ተቀዳሚ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ ብዙው ጊዜ የሚጠፋው "ምክር" ተብሎ በሚነገር ውጫዊ ነገር ላይ መሆኑን ማየቱ ያሳዝናል። ወደዚህ ነገር የሚያተኩር ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች አንዱ መሆኑን በአዲስ ግንዛቤ ሊያጤነው ይገባል።

## 1. መንፈስን አታጥፉ

ፍችሽ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19 "መንፈስን አታጥፉ" የሚለው ቃል በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በወጉ አልተገለጠም። ማጥፋት የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለው የሚታይ አካላዊ ነገር ወይም ድርጊትን ለመግለጫነት ነው። ይህን እንደሚከተለው ለማየት እንችላለን፡- ክርስቶስ በማቴዎስ 12፡20፥ የጥዋፍ

ክር ስለማጥፋት ተናገረ። በዕብራውያን 11፡34 የእምነት አርበኞች ‘‘የእሳትን ኃይል እንዳጠፉ’’ ተገልጧል። በኤፌሶን 6፡16 የእምነት ጋሻ ‘‘የክፉውን ፍላጻ ሁሉ ሊያጠፉ እንደሚችል’’ ተገልጧል። በ1ኛ ተሰሎንቄ ግን ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው በምሳሌያዊ ገለጣ ነው። ታየር የተባለ ሰው እንደገለጠው፥ በዚህ ስፍራ የቃሉ ትርጉም ‘‘ማፈን፥ መጨቆን’’ ነው። መንፈስ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ወይም ማግለል በአንድ መልኩ የሚቻል አይደለም። በክርስቲያኖች ሁሉ ውስጥ የማደሩ ነገር የተረጋገጠ ነው። ሕልውናው አይገሰስም። ስለዚህ ማጥፋት፥ ፈቃዱን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን ወይም መቃወም ነው። መንፈስን ማጥፋት ለእርሱ አለመገዛት ወይም ‘‘እምቢ ማለት’’ ተብሎ በቀላሉ ሊተረጎም ይችላል። ስለዚህ ጉዳዩ፥ ለፈቃዱ ለመገዛት ፈቃደኛ የመሆንና ያለመሆን ጥያቄ ነው።

*የሰይጣን ኃጢአት።* በእግዚአብሔር ፍጥረታት መካከል ኃጢአት የገባው በሰይጣን ዓመፅ ነው። ሳጥናኤል አምስት ጊዜ ‘‘እሆናለሁ’’ በማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደተቃወመ ልብ እንላለን። አምስተኛው በአጭሩ እንዲህ ይላል፡- ‘‘በልዑል እመስላለሁ’’ (ኢሳ. 14፡14)። የመጀመሪያው ዓመፅ በእግዚአብሔር ላይ የተካሄደው በሰይጣንና አብረውት በወደቁት መላእክት አማካይነት ነው። በአዳም በተሠራው ኃጢአት ሳቢያ የዓመፅ ሥራ ወደ ሰው ዘር በመግባት ተስፋፋ። ከመንፈሳዊ ሞትና ከኩነኔ እንደገና ነጻ የወጣው ክርስቲያን በተፈጥሮው ወደ ኃጢአት ከሚያደላው ሥጋዊ ኃይል፥ ከዓለምና ከሰይጣን ኃይል ጋር ፊት ለፊት ይፋጠጣል። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ግንዛቤ ካለ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ድርድር ሊኖር አይችልም። የአገልግሎቱን የተሟላ በረከት ለማግኘት ራስን ለእግዚአብሔር ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ ነው። ራስን የመስጠት ሕይወት ቀጥለን እንደምንመለከተው በርካታ ገጽታዎች አሉት።

*ራስን የመስጠት የመጀመሪያ ተግባር።* አንድ ሰው ለሁለት ጌቶች ሊገዛ ያለመቻሉ እውነታ (ማቴ. 6፡24)፥ ማንኛውም ክርስቲያን የሚጋፈጠው ነገር ነው። አዳኙን ጌታ ሳይቀበሉ አሁን ወዳለው የደኅንነት ደስታ መግባት የማይቻል ቢሆንም፥ ይህ እውነት ግን በመሠረታዊ የእምነት ትምህርትና በልምምድ ከግንዛቤ ሊገባ የሚችል ነው። በዚህ መሠረት ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ተመክረዋል። በሮሜ 6፡13 እንዲህ የሚል ምክር ይገኛል፡- ‘‘ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።’’

በመጀመሪያ ‘‘አቅርቡ’’ የሚለው ቃል በአሁን ጊዜ ‘ፓሪስታኔተ’ [‘paristanete’] ሲሆን ትርጉሙም፦ ‘‘ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ’’ የሚል ነው። ቋሚ የኃጢአተኛነት ልምምድን ማቆም እንደሚገባ ያሳያል። ከዚህ ጋር ሲነጻጸር ኃላፊነት የተሰጠው ምክር፥ ራስን ለእግዚአብሔር ስለማቅረብ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ‘ፓራስቴሳተ’ [‘parastesate’] የሚለው የግሪኩ ቃል ‘የኤሪስት’* ጊዜን ያመለክታል። ይህ ግሥ ‘‘ወዲያውኑ ራስን ለእግዚአብሔር የመስጠትን አሳብ’’፥ ማለትም የወደፊት ወቅትን መስጠት እንደማያስፈልግ ያሳያል። ክርስቲያኖች በበረከት የተሞላና ውጤታማ የሆነ ኑሮን ለመኖር ያለ ቀን ቀጠሮ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው እንዲሰጡ ተመክረዋል። (ይህ ራስን የመስጠት አሳብ መሠረታዊነት ልክ ለደኅንነት ሰዎች እምነት የሚያስፈልጋቸውን ያህል ነው።) በሮሜ 12፡1 ደግሞ ጳውሎስ ‘‘ራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንድንሰጥ’’ ያዛል። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ከላይ ያየነውን ቃል በመጠቀም ክርስቲያኖች በማመከር ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ያሳስባል። ሕይወትንና ፈቃድን ለእግዚአብሔር ምሪት አሳልፎ መስጠት በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ቅድመ ሁኔታ ነው። ራስን የመስጠት የመጀመሪያው ተግባር ፈቃድን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠት ሲሆን፥ በየትኛውም ሁኔታ የሚገኝ የፈቃድ ግጭት ጥያቄ አይደለም።

ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ይህን ጉዳይ በዚህ መልኩ አጠር አድርጎ አጠቃሎታል፦ ‘‘ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራስን የመስጠት ጉዳይ በአንድ ልዩ ተግባር የሚገለጥ አይደለም፤ ይልቁንም ሕይወትን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ተገዥ ማድረግ ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆን ማለት ትእዛዛቱን ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው። እርሱ እንድናደርግ የሚፈልግብንን ነገር ከማወቃችን በፊት እንኳ ፍጹም እንደሆነ አድርገን ፈቃዱን መቀበል ማለት ነው። ስለዚህ አንድን የተለየ ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ የመሆን ጥያቄ አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር የፍቅር ልብ የተሻለ በሚመስል መንገድ መቼም ይሁን የት፥ እንዴትም ይደረግ በምን፥ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የመፍቀድ ጥያቄ ነው። ተለምዶአዊና

* የግሪክኛ ግሥ ብዙ ጊዜያት አሉት። እያንዳንዱ ጊዜም ተናጋሪው ስለ ድርጊቱ ዓይነት ያለውን አመለካከት፦ ማለትም ድርጊቱ በመፈጸም ላይ ያለ፥ ወይም የተፈጸመ፥ ወይም ያልተወሰነ መሆኑን ያመለክታል። የአሁን ጊዜ ዋና አገልግሎት የማያቋርጥ ወይም በአሁኑ ጊዜ በመከናወን ላይ ያለ ድርጊትን ለመግለጥ ነው። በሌላ በኩል የኤሪስት ጊዜ አንድ የሆነ ድርጊት መፈጸሙን ብቻ የሚያመለክት ነው። ድርጊቱ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ወይም መቼ ተፈጽሞ እንደነበር ግን አይገልጥም። የኤሪስት ጊዜ ዋና አሳብ መላውን ድርጊት በአንድ ቅፅበት በሚያስቀምጥ ፎቶግራፍ ይመስላል።

ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ በአባቱ ላይ እምነት ያለው ልጅ የአባቱ ፈቃድ፥ አሠራርና ምንነት ባይገለጥለት እንኳ፥ ለመታዘዝ ፈቃደኛ እንደሚሆን ማለት ነው።”

*ያለማቋረጥ ራስን የመስጠት ሕይወት።* ራስን የመስጠት ጉዳይ፥ በመጀመሪያው እርምጃ የሚያበቃ ሳይሆን፥ የልምምድና የመገለጥ ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው ተግባር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመታወቁ በፊት በእምነት መቀበል ነው። የመንፈስ ቅዱስን ምሪት፥ የቃሉን ቀጥተኛ ትምህርትና የእግዚአብሔርን ሥራ በመለማመድ ረገድ ከውስጣዊው ሰው ጋር ሁልጊዜ ትግል አለ። ይህን አስመልክቶ ነው “መንፈስን አታጥፉ” የሚለው ቃል ተግባራዊ የሚሆነው። ማጥፋት የሚለው ቃል በአሁን ጊዜና በትእዛዝ መልክ ነው የተጻፈው። ስለዚህ “መንፈስን አታጥፉ” የሚለው ትእዛዝ መንፈስን ለማጥፋት አትነሣሡ፥ ወይም መንፈስን ማጥፋት ለጀመሩት መንፈስን ማጥፋታችሁን አቁሙ ማለት ሊሆን ይችላል። አማኞች እራስን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠትን በተመለከተ የመጀመሪያውን አቅጣጫ እንዲከተሉ የተሰጣቸው ምክር ነው። ጥሪው እንደገና ራስን የመስጠት ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ በላያችን የመሠልጠን መብት እንዳለው የመገንዘብ ጉዳይ ነው። አማኙ ሕይወቱንና ፈቃዱን ለርሱ አስገዝቷልና መንፈስ ቅዱስን ሊቃወመው አይገባም።

ራስን ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር መስጠት ከፈቃዱ ጋር በተለያየ አቅጣጫ የሚኖርን ግንኙነት ያካትታል። ራሱን የሰጠ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ልዩና አስደናቂ ግንኙነት አለው። አንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች በሚገባ እየተረዳ ሲመጣና፥ ሕይወቱም በእነዚህ እውነቶች ሲመራ፥ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት የመስጠቱ ጉዳይ የሚያስደስትና ቀላል እየሆነ ይመጣለታል። ለእግዚአብሔር ቃል ራስን አሳልፎ የመስጠትን ነገር መቃወም ወይም ፈቃደኛ አለመሆን፥ የመንፈስ ሙላትን የሚያግድና መንፈስን የሚያጠፋ መሆኑ ግልጥ ነው።

መንፈስን ማጥፋት እርሱ ከሚሰጠው ምሪት ጋር በጣም የተገናኘ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግልጥ መመሪያ የማይሰጥባቸው፥ ግን ውሳኔ ልናደርግባቸው የሚገቡ ብዙ መንፈሳዊ ጉዳዮች አሉ። የቅዱሳት መጻሕፍት አጠቃላይ እውነትም ከአንድ የተለየ ሕይወትና ሁኔታ ጋር ሊዛመድ ይገባል። ይህን እውነት በሚመለከት የእግዚአብሔር ቃል መመሪያን፥ መንፈሱ ደግሞ ትእዛዝን ይሰጣል። ይህ እጅግ ውድ የሆነ የአማኝ መብትና የልጅነቱ ምልክት ነው (ሮሜ 8፡14)። ይህን ማስረጃ መቃወም መንፈስን ወደ ማጥፋት ያደርሳል። ምሪት በተለያየ መልክ የሚከናወን እንጂ፥ ቋሚ የሆነ ሥርዓትን የሚከተል አይደለም። መንፈስ

ቅዱስ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለተለያዩ ሰዎች ይሰጣል። ምሪት ብዙ ጊዜ ከአገልግሎት ጋር የተያያዘና እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ሰው ራሱን ለመምራት በሚያስችለው ሁኔታ የተፈጠረ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ምሪት የሚደገፍ ነው። መንፈስ ቅዱስ በእስያና በቢታንያ ወንጌል እንዳይሰብክ ጳውሎስን እንደከለከለውና በኋላ ወደዚሁ ሥራ እንደመራው፥ በቃሉም አገልግሎቱን እንደባረከ ሁሉ፥ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ተግባራትን ይከለክላል (ሐዋ. 16፡6-7፤ 19፡10)። ለውጤታማ አገልግሎትና በማስተዋል ለሚወሰድ እርምጃ በመለኮታዊ ምሪት ላይ መደገፍ፥ እንዲሁም ሥርዓትን መከተል አስፈላጊ ነው። የበረከቱ ሙላት የሚገኘው ከመለኮት በሚሰጥ መንገድ ሲኬድ ብቻ ነው።

ራስን መስጠት ከእግዚአብሔር ቸርነት ጋር የተዛመደና የልባችንን ተፈጥሯዊ ፍላጎት የሚጻረር ነው። ስለዚህ ከሰው አመለካከት አንጻር ውጫዊ ገጽታው ከመልካም ይልቅ ክፉ ይመስላል። የ"ሥጋ መውጊያ" ባሕርይ ምንም ይሁን ምን በእምነት፥ በፍቅርና በእግዚአብሔር ጥበብ ተቀባይነት ማግኘት አለበት። መንፈስን ሳያጠፉ መኖር የሚፈልግ አማኝ፥ የራስን ፍቃድ የማስገዛትን ሕይወት ጣፋጭነት በትክክል ሊረዳ ይገባል። በሥቃይ ውስጥ ያሉ ቅዱሳን ሌሎች ሊያውቁት የማይቻላቸውን ጣፋጭ ምስክርነትና የመንፈስ ሙላት ሲገልጡ የምንሰማቸው ለዚህ ነው። ስለዚህ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ለቀጥተኛ ቃሉ ትምህርት መገዛትን፥ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት መታዘዝንና ቸርነት የተሞላ ሥራውን በእምነት መቀበልን ያጠቃልላል። እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በመኖር የሚከናወኑ ራስን የመስጠትና መንፈስን ያለማጥፋት የዕለት ከዕለት ልምምዶች ናቸው።

*የክርስቶስ ታላቅ ምሳሌነት።* ብዙ ጸሐፊዎች እንደሚያመለክቱት ክርስቶስ ራሱ የመንፈስ ሙላት ያለማቋረጥ የተገለጠበት ታላቅ ምሳሌያችን ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን በአጠቃላይ ያስገዛ ነው። በፊልጵስዩስ 2፡5-11 ያለው ክፍል የጌታችንን ድልና ክብር የሚገልጥ ብቻ ሳይሆን፥ ራሱን ለመስቀል ሞት ታዛዥነት እስከ ማስገዛት ድረስ ዝቅ ማድረጉን ይጨምራል። ክርስቶስ፥ እግዚአብሔር የመረጠውን ነገር ለመሆን ፈቃደኛ ሆነ:- "የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ።" እግዚአብሔር ወደመረጠው፥ እርሱን ወደማይቀበለውና ወደሚሰቅለው ኃጢአተኛ ዓለም ለመምጣት ፈቃደኛ ሆነ። እግዚአብሔር የመረጠውን ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር:- "እስከ መስቀል ሞት ድረስ እንኳ የታዘዘ ሆነ።" የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ትግል:- "ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ" በሚልና እጅግ ሰፊ አሳብ በያዘ ቃል ቀርቧል (ሉቃስ 22፡42)። የህን መሰሉ ባሕርይ በአንጋፋ ክርስቲያኖች

ሕይወት እንኳ የተከሠተው በመጠኑ ነው። “የክርስቶስ አሳብ” ያለው ክርስቲያን፥ ክርስቶስ በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደፈጸመ ሁሉ ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሰጠ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ለማግኘት ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት የግድ ይሆናል።

## 2. መንፈስን አታሳዝኑ

ፍችⅡ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ቅዱስ እንደሆነና አካላዊ ሕልውና እንዳለው ይመሰክራል። የዚህ ቅዱስ አካል በአማኙ ሕይወት ውስጥ ማደር፥ ያን ሰው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያደርገዋል። በምንም ሁኔታ ቢሆን የኃጢአት መኖር የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዝነዋል። በዚህ መሠረት ክርስቲያን “ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ” ተብሎ ሲመከር (ኤፌ. 4፡30)፥ የመንፈስ ቅዱስ ተጻራሪ የሆነ ነገር በሕይወቱ እንዳይኖር መጠየቁ ነው። መንፈስ ቅዱስን ከሚያሳዝኑ ነገሮች አንዱ ኃጢአት መሆኑ ይታወቃል።

መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ብዙ ነገሮችን ያካትታል። ይህም ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ያልሰጡ ክርስቲያኖች መለያ ነው። የመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስን ማጥፋት ሲሆን፥ ይህም አመራሩን ለመከተል እምቢ ማለትና ፈቃዱን መቃወም ነው። መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን የደኅንነት ጉዳይ አይደለም፤ ደኅንነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚሆን ነገር ነውና። ሁልጊዜ የመንፈስ ቅዱስን አመራር መቃወም ከእግዚአብሔር ፈቃድ መራቅን ያመጣል። አገልግሎቱን እስከተቃወምን ድረስ በሙላት ሊባርከንና ሊመራን አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “የእግዚአብሔርን መንፈስ ማሳዘን” ተብሎ የተጠቀሰው ይህ ነው።

የእግዚአብሔርን መንፈስ የማሳዘኑ እውነታ በክርስቲያን ልምምድ ውስጥ ይገለጣል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ማጣትና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አለማፍራት፥ የማያምኑ ሰዎችን አእምሮ የያዘ ሲሆን፥ የዚህ አንዳንድ ሁኔታ የአማኙንም ሕሊና ሊውጠው ይችላል። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዘኑ ክርስቲያኖች አኗኗር ልክ የማያምን ሰው እንደሚኖረው ይሆን ይሆናል።

ይሁን እንጂ ልምምድን በሚመለከት መሳሳት ሊኖር ይችላል። የአካል ሁኔታ በመንፈሳዊ ልምምድ ላይ ብዙ ጊዜ ተጽእኖ ሊፈጥር እንደሚችል ጠንቃቃ ጸሐፊዎች ይጠቁማሉ። የራበውና የደከመ ወይም የታመመ ሰው በኃጢአት ውስጥ ሳይኖር፥ የተትረፈረፈ መንፈሳዊ ሕይወት ማሳየት ይሳነው ይሆናል። ነገሩ በክርስቲያኑ ዘንድ የተሸሸገ ኃጢአት

ሊሆንም ይችላል። መንፈስ የሚያዝነው ግልጥ በሆነ ኃጢአት እንጂ፥ በኃጢአታዊ ተፈጥሮ ላይ አይደለም። መንፈሳዊ ኅብረትና ኃይል እንደጎደለው የተሰማው አማኝ መነሾውን በጸሎትና ቃሉን በማጥናት የመፈለግ ኃላፊነት አለበት። እኛ ወደ እግዚአብሔር ከቀረብን፥ እግዚአብሔር ወደ እኛ መቅረቡ ምንጊዜም እውነት ነው።

ለመንፈስ ቅዱስ ማዘን ምክንያቱ ኃጢአት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ ነገሮች ግልጥ እንደሆኑ ሁሉ መፍትሔውም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ ቀርቧል።

*መፍትሔው ኃጢአትን መናዘዝ ነው።* ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አስመልክቶ በሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዘንድ የሚያስገርም አለመረዳት አለ። ካይፐር በጻፈው ታላቅ ሥራ ውስጥ እንኳ በኤፌሶን 4፡30 ያለው አሳብም ሆነ በ1ኛ ዮሐንስ 1፡9 ያለው ኃጢአትን የመናዘዝ አሳብ በሚገባ አልተጠቀሰም። ስለ መንፈስ ቅዱስ ከተካሄዱ አብዛኛዎቹ ጥናቶች ማረጋገጥ እንደሚቻለው፥ ይህንን እውነት ቸል ማለት በጣም የተለመደ ሆኖ እናገኛለን። እጅግ የሚያሳዝነው ጉድለት የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከአማኝ መንፈሳዊ ሕይወት ጋር አለማዛመድና መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ናቸው። እነዚህም ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኙትን ሙሉ በረከቶች ያግዳሉ። አሁንም ቢሆን ለመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከሁሉም የተሻለ ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ይህን ቃል በጥንቃቄ የሚያነቡ ሁሉ ለችግሮቹ መፍትሔ ያገኛሉ።

መንፈስ ቅዱስን የማሳዘን መፍትሔው ተናዘዝ በሚል ቀላል ቃል ተገልጧል። በ1ኛ ዮሐንስ 1፡9 መሠረት፡- "በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፥ ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።" ይህ ቃል ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረትና በተሰጣቸው መገለጥ ውስጥ መካከለኛ ስፍራ ይዞ የሚገኝና (1ኛ ዮሐ. 1፡5-2፡2)፥ ለነሱ የተሰጠ መልእክት ነው። መልእክቱ ለኃጢአታቸው መሥዋዕት የሆነ ክርስቶስን ላልተቀበሉና ላልዳኑ ሰዎች አይደለም። ለነሱ የሚሰጣቸው ምክር፥ "እመኑ" በሚል አንድ ቃል ይጠቃለላል። በሚያድን እምነት ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለ የተባረከ ግንኙነት የገባ ክርስቲያን የሚቀረው ነገር ቢኖር፥ ይህን ኅብረት እንዲቀጥል ማድረግ ነው። 1ኛ ዮሐንስ ውስጥ የሚገለጠው ነገር ይህ ነው። ይቅር የመባል ተስፋ ከጽድቅ ወይም ከበደለኛነት ጥያቄ ጋር መምታታት የለበትም። ከፍርድ አንጻር ስናየው፥ የኃጢአት ጉዳይ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያድን እምነት በተገለጠ ጊዜ አብቅቷል። ይሁን እንጂ የኃጢአት በክርስቲያን ሕይወት

ውስጥ መኖር ለዚህ ኅብረት እንቅፋት ከሆኑ ነገሮች አንዱ ሆኗል። የክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅነት በምንም ሁኔታ የማይነካ ቢሆንም፥ በኃጢአት ሳቢያ የደስተኛ ቤተሰብ ኅብረት መዛባቱ ግን አይቀርም። ከእግዚአብሔር ጋር የኅብረት ተሐድሶ ከመሆኑ በፊት ከሰው በኩል ንስሐ መኖር አለበት። መንፈስ ቅዱስ የሚያዝንበት ነገር እንደ ኃጢአት ተቆጥሮ ልንናዘዘው ይገባል። ንስሐ ክርስቲያን እንደ ዳኛ ሆኖ፥ በራሱ ኃጢአት ላይ መፍረድን፥ ኃጢአቱን መኮነንና ለሰማያዊ አባቱ መናዘዝን ያካትታል (1ኛ ቆሮ. 11፡31)።

ኃጢአትን ለሚመለከት ችግር እንዲህ ያለው አቀራረብ በእግዚአብሔር ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት እንደሚኖረው ተገቢ ዋስትና ተሰጥቷል። ይህ ለኃጢአት ዋጋ የመክፈል ወይም በራስ ላይ የሥነ-ሥርዓት ቅጣት የመፈጸም ጥያቄ አይደለም። እንዲሁም እግዚአብሔር ንስሐን በሚቀበልበት ጊዜ ቀላል አባታዊ ቅጣት መቅጣቱም አይደለም። ጠቅላላው ድርጊት ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ ቅጣትን የሚመለከተው ጥያቄ በዚህ አመለካከት ውስጥ ጨርሶ የለም። ምሕረትን የሚያሰጠው ዋጋ ተከፍሎ ያለቀ ጉዳይ ነው። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር አብ ኃጢአትን ይቅር ለማለት የታመነና ጻድቅ እንጂ፥ ቀለል ባለ ቅጣት የሚቀጣና ምሕረት የሚያደርግ ብቻ አይደለም። አንድያ ልጁ ለኃጢአት በቂ ዋጋ ባይከፍል ኖሮ፥ ይቅርታን የሚሻ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይቅርታ አያገኝም ነበር። በዚህ መሠረት ሰው የሚፈለግበት ነገር እጅግ ቀላል ነው።

ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ ሰዎች የተሰጠው ተጨማሪ ተስፋ ብዙ ጊዜ በቂ ትኩረት ሳያገኝ ይታለፋል። ከዚህ ቀደም ለተፈጸሙ ኃጢአቶች ይቅርታ ከማግኘት ሌላ "ከዓመፃ ሁሉ የመንጻት" ተስፋም ተሰጥቷል። ይህ ተስፋ ለኃጢአት ሙሉ በሙሉ መወገድ የተሰጠ መተማመኛ ወይም ክርስቲያን ወደፊት ኃጢአት እንዳይሠራ ሊያደርገው የሚችል ነገር ባይሆንም፥ ተጨማሪ ኃጢአትን ለመከላከል እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ በሚመለከት ደግሞ መገለጥን የሚያካትት መሆኑን ለማየት እንችላለን። ንስሐ የመቀደስ ኃይል ነው። ጥፋተኛነቱን በመረዳት በእግዚአብሔር ፊት በኃጢአቱ እጅግ የተጸጸተና የክርስቶስ ውድ ደም እንዲያነጻው ልመና ያቀረበ ክርስቲያን፥ በዚህ አሠራር ወደ ኃጢአት መንገድ የመመለስ አዝማሚያው በጣም ዝቅተኛ ነው። የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ከተመለሰ በኋላ፥ ከአባቱ ቤት ውጭ የነበረውን ኑሮ እንደገና ሲፈልግ አናየውም። ንስሐ ድካምን አውቆ መለኮታዊ ኃይልን በመፈለግ ለውጤቱ በእግዚአብሔር ላይ የመደገፍ ተግባር ነው። ይህ ጉዳይ በመንፈስ መመላለስ

በሚለው ርእስ ሥር በተብራራው መሠረት በኃጢአት ላይ ድል ማግኘትን በሚመለከት እጅግ አስፈላጊነት ያለው እውነት ተደርጎ ቀርቧል።

ንስሐ ሙሉ በሙሉ የሰው ኃላፊነት ነው። በ1ኛ ዮሐንስ 2፥1-2 ያለው መገለጥ የሚያመለክተው፥ በኃጢአት ምክንያት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚታየው ነገር ወዲያውኑ በመለኮት በኩል የሚስተካከል መሆኑን ነው:- "ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህንን እጽፍላችኋለሁ፥ ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እርሱም የኃጢአታችን ማስተስረያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ።" ክርስቲያን ኃጢአትን በሚያደርግበት ጊዜ፥ ክርስቶስ ወዲያውኑ የጠበቃነትን ሥራ በመጀመር የራሱን ጽድቅና የተሟላ ተግባር ይዞ በኃጢአተኛው ምትክ መቅረቡ የተባረከ እውነት ነው። በመለኮት በኩል ያለው ነገር ምንጊዜም የሚለወጥ አይደለም። አማኝ ከመለኮት ጋር ያለውን ኅብረት በንስሐ ማስተካከልን እስካልተረዳ ድረስ፥ ይህ እውነት የማይገነዘበው ነገር ሆኖ ይቆያል። የኤሌትሪክ መሥመር ከተቋረጠ የኤሌትሪክ ብርሃን እንደማይተላለፍ ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረትም እንዲሁ ነው። ሁልጊዜ ግንኙነቱ የሚቋረጠው፥ ከእኛ ከሰዎች በኩል መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ ይናገራሉ። የተቋረጠው ግንኙነት በፍጥነት ተስተካክሎ በኅብረቱ የሚገኘው ሙሉ ኃይልና በረከት እንደገና የሚታወቀው ኃጢአትን በመናዘዝ ነው። በኃጢአት ለረጅም ጊዜ የኖረ ክርስቲያን፥ ከመታደሱ በፊት ራሱን የመመርመሪያ ጊዜ የሚያስፈልገው ቢሆንም፥ መፍትሔው በምንም አኳኋን ይሁን ያው ንስሐ ነው።

*ያለማቋረጥ በኃጢአት ስለመኖር የተሰጠ ማስጠንቀቂያ።* የሰው ልጅ ሥቃይ አሳሳቢ የሆነው ለሥነ-መለኮት ሊቃውንትና ለፈላስፎች ብቻ ሳይሆን፥ በመጽሐፈ ኢዮብ እንደተገለጠው ለቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችም ጭምር ነው። በመሠረቱ የሰው ዘር መከራ የሚቀበለው በአዳም ኃጢአት ምክንያት ነው። በዚህ ሳቢያ በሰው አካል ላይ ሕመም መጣ፥ ስሜቱ ተመረዘ፥ የኃጢአት ተፈጥሮ የሚተላለፍ ስለሆነ፥ ፍጥረት ሁሉ ከመርገም በታች ሆነ። የነፍስ መዳን እነዚህን የሥቃይ መሠረታዊ ምክንያቶች ሁሉ አያስወግድም። በዕብራውያን 12፥5-6 እንደተገለጠው አባት የቅጣት እጁን የሚያሳርፈው በልጆቹ ሁሉ ላይ ነው:- "ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፤ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል።" የእግዚአብሔር ልጅ በቅጣት ይሠለጥናል፤ እውቀት ያገኛል፥ ኃጢአትን

ይከላከላል፥ ጠቅላላ ሕይወቱም ለበለጠ ጥቅም የተዘጋጀ ይሆናል። ታላላቅ ክርስቲያኖች በከፍተኛ መከራ ውስጥ ማለፋቸው እውነት ነው።

ይሁን እንጂ በተገቢ ሁኔታ እራስን በማስተካከልና ኃጢአትን በመናዘዝ ቅጣቶችን መከላከል እንደሚቻል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡31-32 እንዲህ ይላል፦ "ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር። ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኰነን በጌታ እንገሠጻለን።" በእነዚህ ቀላል ቃላት መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ክርስቲያን ራሱን ለማስተካከልና ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ እንዲናዘዝ ጊዜና ዕድል ተሰጥቶታል። ይህን ዕድል ሳይጠቀምበት ቢቀርና በኃጢአት ውስጥ ቢቆይ፥ እግዚአብሔር አብ ጣልቃ ይገባል። በመቅጣት አማካይነት ሥነ-ሥርዓት ያስይዘዋል። ከዚያ በፊት ለመናዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነበትን ኃጢአት እንዲናዘዝ ያደርገዋል። በዚህ ምክንያት በኃጢአት መጫወት አደገኛ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት በቀጥታ ይናገራሉ። የሕይወት ልምድም ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ያረጋግጥልናል። ለዚህ ነው ክርስቲያኖች ሁሉ አለመናዘዝና በኃጢአት መቀጠል ጠቃሚ እንዳልሆነ ሊመሰክሩ የሚችሉት። ኪሳራው በማንኛውም ረገድ ቢሆን ከፍተኛ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ካለመኖሩ የተነሣ ከኅብረቱ የሚገኘው በረከትና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን፥ የልብ ኀዘንና ፈተና ጭምር ይከተላል። ጌታውን በመካዱ ምክንያት መራራ ልቅሶ ያለቀሰው ሐዋርያ በመልእክቱ እንደጻፈው፦ "ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ። ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል" (1ኛ ጴጥ. 4፡14-15)።

## 3. በመንፈስ ተመላለሱ

የዚህ ክፍል ጉዳይ፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ የሚያከናውነው ሥራ ብቻ ሳይሆን፥ ለአንድ ሰፊ ጽሑፍ መሪ አሳብን የሚሰጥም ነው። በዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ በቂ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ግንዛቤና እጅግ አደገኛ የሆኑ ኑፋቄዎች ሲነሡ ታይተዋል። ቢሆንም ትምህርቱ ሙሉ በሙሉና በጥልቀት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነው። ቀደም ሲል በመንፈስ ስለተሞላ ሕይወት የቀረቡት ሁለት ትእዛዞች በባሕርያቸው አሉታዊ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ከፈለግን፥ መንፈስ ቅዱስን እንቢ ማለት፥ ማጥፋትና በመደጋገም እርሱን ማሳዘን

የለብንም። በመንፈስ ተመላለሱ የሚለው ሦስተኛ መመዘኛ ግን የእውነቱ አዎንታዊ ገጽታ ሲሆን፥ በይዘቱም ከሌላው ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ነው።

*ፍቺ።* "በመንፈስ ተመላለሱ" (ገላ. 5፡16) የሚለው ትእዛዝ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መኖር እጅግ አስፈላጊ መሆኑንና አሁኑኑ መፈጸም ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ምክር እንደሆነ እንገነዘባለን። 'ኒዩማቲ ፔሪፓቴተ' ['pneumati peripateite'] የሚለው የግሪክ ቃል ቀላልና ቀጥተኛ ነው። 'ኒዩማቲ' በመንፈሱ ውስጥ ከማለት ይልቅ በመንፈስ ተብሎ ሊተረጎም የተገባ ነው። በገላትያ 5፡5 እንደተጻፈው ቃሉ የሚያመለክተው ሌላ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን ራሱን ነው። ቻርልስ ጄ. ኤሊካት [Charles J. Ellicott] ስለ ገላትያ 5፡5 አሳብ ሲሰጥ፥ ጥቅሱ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገር መሆኑን በሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች እናረጋግጣለን ብሏል።

ስለዚህ አተረጓጎሙ እጅግ ግልጥ ነው። ክርስቲያኖች ከሥጋ ምኞት ለመራቅ ከፈለጉ፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መመላለስ አለባቸው። 'ፔሪፓቴተ' የሚለው የግሪክኛ ቃል በመንፈስ መመላለስ ያለማቋረጥ ሊደረግ የሚገባ ነገር መሆኑን ያሳያል። አሳቡ በመንፈስ "መመላለሳችሁን ቀጥሉ" የሚል ስሜት አለው። ያለማቋረጥ በመንፈስ መመላለሳችንን ስንተው ወዲያውኑ መንፈሳዊ ውድቀት በሕይወታችን ይከሠታል።

*የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት መለኪያ።* የክርስቲያንን በከፍተኛ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ መመላለስ አስፈላጊነት ከመጽሐፍ ቅዱስ በምንመለከትበት ጊዜ የጉዳዩ ጠቃሚነት ይበልጥ ግልጥ ይሆንልናል። እስራኤላውያን እንዲኖሩበት በሕግ የተሰጣቸው የሕይወት ደረጃ ከፍተኛ ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስም ሆነ ለክርስቲያን ሁሉ የተሰጠው ችሎታ ስላልነበራቸው፥ ከክርስቲያን የሕይወት መመዘኛ አንጻር ሲታይ፥ የኖሩት ሕይወት ክርስቲያን ከሚጠበቅበት ለየት ያለ መለኪያ ነበረው። ወደፊት የሚመጣው የክርስቶስ መንግሥት መለኪያም እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም፥ መመዘኛዎቹ የወጡት ግን የተለዩ ሁኔታዎች እጅግ ከተመቻቹላቸው በኋላ ነው። በዚያን ጊዜ ሰይጣን ይታሰራል፥ ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ይሆናል፥ በአጠቃላይ በዓለም ሁሉ ሰላምና ጽድቅ ይሰፍናል፤ ያም ቢሆን የአኗኗሩ ሁኔታ በባሕርዩ ሕጋዊ ይሆናል። ለዚህ ስፍረ-ዘመን የሚሆኑ የአኗኗር መለኪያዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሐዋርያት ሥራ፥ በመልእክቶችና በአንዳንድ የወንጌል ክፍሎች ይገኛሉ። እነዚህን የአኗኗር መለኪያዎች ስንመረምር፥ በመንፈስ የሚራመዱ ሰዎች ብቻ ሊደርሱበት የሚቻላቸው መሆኑን እንመለከታለን። በሙሴ ሕግ የሚገኙት አንዳንድ ትእዛዛት ከእነዚህ እኩል የማይታዩ የሕይወት መመዘኛዎች ቢሆኑም፥ በመካከላቸው ልዩነት መኖሩ ግን ግልጥ ነው። የሙሴ ሕግ በሰዎች ላይ ፍርድን

ለማምጣት ወይም ሰዎችን ለመኮነን የታቀደ ነበር። በዚህ ዘመን ያሉ የጸጋ የሕይወት መለኪያዎች ግን ሰዎችን ለመቀደስ ታቅደዋል። ሰው በሕግ ሊፈጽመው ያልቻለውን ነገር በጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይፈጽመዋል። በዚህ እውነት ውስጥ ክርስቲያን፥ ቀደም ባሉት ስፍረ-ዘመናት ቅዱሳን ባልነበራቸውና ከእግዚአብሔር በነጻ በተገኘው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመኖር ኃላፊነት እንዳለበት ይታያል።

እነዚህን የሕይወት መለኪያዎች በአጭሩ ማጥናት ጉዳዩን በበቂ ሁኔታ ግልጥ ያደርገዋል። ክርስቶስ እንደወደደን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ታዘናል (ዮሐ. 13፡34፤ 15፡12)። "አእምሮን ሁሉ" እንኳ ለክርስቶስ መማረክ አለብን (2ኛ ቆሮ. 10፡5)። "ሰውን ሁሉ ልንታገሥና መልካም የሆነውን ለማድረግ ልንተጋ" ያስፈልጋል (1ኛ ተሰ. 5፡14-15)። "ሁልጊዜ ደስ ሊለን ሳናቋርጥ ልንጸልይና በሁሉ ልናመሰግን ይገባል" (1ኛ ተሰ. 5፡16-18)። ለሥጋ ጨርሶ የማይቻሉትን ተመሳሳይ የሕይወት መለኪያዎች መዘርዘር ይቻላል። ሰው ሊያደርገው የማይቻለው ነገር በመንፈስ ለሚመላለስ ሁሉ ይቻለዋል። በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፍጹም አስፈላጊነት ከልምምድም ሆነ ከመገለጥ ታላላቅ እውነታዎች አንዱ ነው።

*የዓለም አሠራር ኃይል።* የክርስትና ሕይወት የዚህ ዓለም የተበላሸ አኗኗር ከሚያስከትለው የአመለካከት ተጽዕኖ አንጻር ሲታይ፥ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። ክርስቶስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ የጸለየው ከዓለም እንዲወጡ ሳይሆን፥ በዓለም ከክፉት እንዲጠበቁ ነበር (ዮሐ. 17፡15)። በሥጋ በምድር ቢሆኑም አሳባቸው ሁሉ ሰማያዊ እንዲሆን ጸለየላቸው። ቅዱሳት መጻሕፍት የዓለምን አስጸያፊነት በግልጥ ይናገራሉ። ከዓለም ጋር ወዳጅነትን መፍጠር፥ መንፈሳዊ ምንዝርና ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ የዓለም ወዳጅ መሆን ደግሞ የእግዚአብሔር ጠላት መሆን ነው ተብሏል (ያዕ. 4፡4)። ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ይሽራል (1ኛ ዮሐ. 2፡15)። ከዓለም ጋር መመሳሰስና ዓለምን መምሰል ተከልክሏል (ሮሜ 12፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14)። ከሰው ልጅ ነፍስ ጋር ሲወዳደር የዓለም ሁሉ ዋጋ ኢምንት እንደሆነ ተጽፏል (ማቴ. 16፡26)። ዓለማዊነት ክርስቲያን እንዳያፈራ እንደሚያደርገውና ውስጡ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያንቅም ተጽፏል (ማቴ. 13፡22)። ዓለም በክርስቶስ መስቀል እንደተሰቀለ ተገልጧል (ገላ. 6፡14)። ክርስቲያን ለዓለም ይመሰከር ዘንድ በዓለም ቢኖርም ዓለም እንድትበርዘው ስለማይፈቅድ ከዓለም አይደለም። ከዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ በእግዚአብሔር መንፈስ ካልሆነ በቀር ብርቱውን የዓለም ኃይል ለማሸነፍ አይቻልም።

*የሰይጣን ኃይል።* ሰይጣንን ስለሚያስተምረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በብዙ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ውስጥ ቸል መባሉ የክርስትናን ሕይወት ደረጃና ኃላፊነት ይበልጥ አስቸጋሪ አድርጎታል። ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ከሁሉ የሚልቅ ኃይል ያለው ሰይጣን ሲሆን፥ የክርስቲያን ውጊያም ከርሱ ጋር ነው። ጳውሎስ ከልምምድም ሆነ ከመገለጥ እንደተረዳው፥ "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ" (ኤፌ. 6፡12)። ሰይጣን፥ የማያምኑ ሰዎች የወንጌልን ብርሃን እንዳያዩ አሳባቸውን ያሳውራል (2ኛ ቆሮ. 4፡4)። ለዚህ ነው የማያምኑ ሰዎች ወደ እምነት ይመጡ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊ የሚሆነው። ክርስቲያኖች ቀጥሎ ያለው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። "በመጠን ኑሩ ንቁም፤ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና" (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። በሌላ በኩል ደግሞ ሰይጣን ራሱን የብርሃን መልአክ እንደሚያስመስል መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (2ኛ ቆሮ. 11፡14)። ክርስቶስ ራሱ እንደመሰከረው ሰይጣን ሐሰተኛና ነፍሰ ገዳይ ነው (ዮሐ. 8፡44)። የሰይጣን ኃይል ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ፥ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለ ሙሴ ሥጋ ከእርሱ ጋር በተነጋገረ ጊዜ፥ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ቃል ሊናገረው አልደፈረም (ይሁዳ 9)። የእግዚአብሔር ጠላት የሆነ ሁሉ የቅዱሳንም ጠላት መሆኑንና ከመለኮታዊ ኃይልና ጥበቃ ውጪ በእርሱ ላይ ድል ማግኘት እንደማይቻል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ክርስቲያን በመንፈስ እስካልተመላለሰ ድረስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር የማይችለው በዚህ ጠላት ምክንያት ነው። የሐሰት አባት የሆነው ሰይጣን ራሱ የሌሰ አስመስሎ ብዙዎችን እስከማሳመን የሚደርስ ጠላታችን ነው። የዘመኑ ሰው ሰይጣን ነክ ስለሆነ ትምህርት ፍላጎት ከማጣቱ አንጻር ሲታይ፥ በመንፈስ ስለመመላለስ ያለው ግንዛቤ ጥቂት መሆኑ የሚገርም ነውን?

*ኃጢአታዊ ተፈጥሮ።* እያንዳንዱ ነፍስ በድል ለመኖር በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ ያለበት፥ ከውጭ ባለ ጠላት ብቻ ሳይሆን ከውስጥም ባለ ድካም ምክንያት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የአዳም ልጆች ሁሉ ከአዳማዊ ተፈጥሯቸው የተነሣ ኃጢአትን የማድረግ ዝንባሌ እንዳላቸው ይናገራሉ። ኃጢአታዊ ተፈጥሮ (ሮሜ 5፡21፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡8)፥ አዳማዊ ተፈጥሮ፥ ሥጋ (ሮሜ 13፡14፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡1፤ 10፡2-3፤ ገላ. 5፡16-24፤ 6፡8፤ ኤፌ. 2፡3)፥ አሮጌው ሰው (ሮሜ 6፡6፤ ኤፌ. 4፡22፤ ቈላ. 3፡9-10) ወይም ሌሎች አገላለጦችን ስንጠቀም ያላቸው አሳብ የሚያመለክተው ሰብአዊ ተፈጥሮን ነው። ሰብአዊ ተፈጥሮ ነፍስን፥

መንፈስንና ሥጋዊ አካልን የሚጨምረው ነው። ለምሳሌ ኃጢአት የሚለው ቃል በሮሜ 6 እና 7 እንደምናገኘው በነጠላ ቁጥር ሲጠራ ከተግባር ይልቅ የኃጢአት ተፈጥሮን የሚያመለክት ነው። ይህ ነገር ኃጢአት ለማድረግ ለሚፈልግና የሰይጣንን ድምፅ ለሚሰማ፥ በውስጣችን ላለ ክፋት ሁሉ ምንጭ ነው። በመንፈስ የመመላለስን አስፈላጊነት በግልጥ ለመገንዘብ ይህን መሠረታዊ ትምህርት አጥርቶ መረዳት ይገባል።

ከተግባር አንጻር ስናየው ሐሰተኛ የቅድስና ትምህርት ወይም ፍጹምነትን የሚመለከት የተሳሳተ የእምነት ትምህርት መለያዎች ወይም የኑፋቄዎች ሁሉ መነሻቸው፥ ስለ ኃጢአት ተፈጥሮ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሰጡትን ትምሕርት ለመገንዘብ አለመቻል ነው። በአሁኑ የውይይት ክልል የተካተቱትን እውነቶች ሁሉ በጥልቀት ለመመርመር ባይቻልም፥ ዋና ዋናዎቹን መገንዘቡ ግን አያዳግትም።

*የፍጹምነት ፅንሰ-ሐሳብ።* የፍጹምነት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ በሚያምኑ ሰዎች ዘንድ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። የዌብስተር [Webster] እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ፍጹምነትን ለሚያመለክተው የእንግሊዝኛው ቃል የሚሰጠው ትርጉም፥ ለሁሉም ክፍሎች የሚስማማ ሳይሆን አይቀርም፡- “በመሠረታዊ የእምነት ትምህርት አመለካከት ፍጹምነት ሲባል በምድራዊ ሕይወት፥ ያለ ኃጢአት ወደ መሆን ደረጃ መድረስ ይቻላል” የሚል ነው። አንዳንድ የፍጹምነት ትምህርት መምህራን፥ ይህን ፅንሰ-አሳብ በፈቃድ በሚሠራ ኃጢአት ብቻ ይወስኑታል። ሌሎቹ ደግሞ ለሚታወቁ ኃጢአቶች ብቻ ያደርጉታል። በዚህ አመለካከታቸው በቸልተኝነት የሚደረግን ኃጢአት ወይም በምንም መንገድ ይሁን በፍጹምነት ውስጥ ጣልቃ ሊገቡ አይችሉም የሚሏቸውን ኃጢአቶች አያካትቱም። የቀሩት የኃጢአት ባሕርይ ራሱ ይወገዳል ይላሉ። የኃጢአትን ባሕርይ በጥንቃቄ መመርመር ግን ትምህርቱ የኃጢአትን መሠረታዊ ነገሮች ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የፍጹምነት ትምህርት አራማጆቹ በያዙት መልክ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጨርሶ የሌለ መሆኑን እንረዳለን።

ብሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ የዕብራይስጥ ቃሎች “ፍጹም” ተብለው ቢተረጎሙም፥ ከአገባቡ እንደምንረዳው ቃሉ የሚያመለክተው በጉዳዩ የተጠቀሱትን ሰዎች ኃጢአት የለሽነት አይደለም (ዘፍጥ. 6፡9፤ 1ኛ ነገሥት 15፡14፤ 2ኛ ነገሥት 20፡3፤ 1ኛ ዜና 12፡38፤ ኢዮብ 1፡1፥ 8፤ መዝ. 37፡37፤ 101፡2፥ 6 ወዘተ.)።

በአዲስ ኪዳን ሦስት የግሪክኛ ቃላት “ፍጹም” በሚል የአማርኛ ቃላት የተተረጎሙ ሲሆን፥ ከእነዚህ ሁለቱ ብቻ የፍጹምነትን ትምህርት ከኃጢአት ከመንጻት አሳብ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚያሳዩ ናቸው።

'ካታርቲዞ' ['katartizo'] የሚለው ቃል አንደኛው ሲሆን (ይህ ቃል እንደ ግሥ፥ ስምና ቅጽል "ፍጹም"፥ "ፍጹማን"፥ "መቃናት"፥ "መሞላት"፥ "መዘጋጀት" እና "መተባበር" የሚሉ ትርጉሞች ተሰጥቶታል)። ቃሉ "በነገር ሁሉ የተሞላ መሆን"፥ "ተገቢ"፥ "የተስተካከለ" የሚል አሳብንም አዝሏል። ሌላው የግሪክ ቃል 'ቴሌዮ' ['teleioo'] ("ፍጹም"፥ "ፍጹማን"፥ "ፍጹምነት"፥ "ሙሉ"፥ "መብሰል"፥ "መሞላት" እና "መሻል" ተብሎ ተተርጉሟል) "ወደ ፍጻሜ ማምጣት" ወይም "ወደ ግብ ማድረስ" ማለት ነው። ስለዚህ የቃሉ ትርጉም "አንድን ነገር የመጨበጥን" አሳብ የያዘ ነው።

ፍጹምነት ከኃጢአት ጋር በተያያዘ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሦስት መልክ ይገኛል። አንደኛው፥ ስፍራዊ (የመብት ስፍራን የሚመለከት) ፍጹምነት ሲሆን፥ ያም የሁሉም ክርስቲያን መብት መሆኑ ተገልጧል። ዕብራውያን 10፡14 እንዲህ ይላል፡- "አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን ['ቴቴሌዮኬን'/'tetelioken'] አድርጓቸዋልና።" ቃሉ የቅርብ ጊዜ ኃላፊ ግሥ ስለሆነ ፍጹምነት ለአንዴና ለመጨረሻ በመፈጸሙ የማይደጋገም መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራው የተሟላ ፍጹምነት ነው። በመሆኑም ስለ ክርስቲያናዊ ሕይወት ጥራት በዚህ ስፍራ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም። ያለ ኃጢአት የመሆን ነገርም አልተጠቀሰም። ቅዱሳን ሁሉ (አንድ ጊዜ የተቀደሱት) በክርስቶስ የተከናወነው ፍጹምነት ተካፋዮች ናቸው።

ሁለተኛው፥ አንጻራዊ ፍጹምነት፥ በጽሑፉ አገባብ እንደተመለከተው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ብስለት እንደ ፍጹምነት ይታያል። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ፡- "እንግዲህ ፍጹማን ['ቴሌዮ'] የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ" (ፊልጵ. 3፡15) ብሏል። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የሚናገረው ያለ ኃጢአት ከሆነ ፍጹምነት ይልቅ፥ ስለ መንፈሳዊ ብስለት መሆኑን ሌላ ስፍራ ከገለጠው ቃል እንገነዘባለን፡- "አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ" (ፊልጵ. 3፡12)። ይህ ቁጥር የሚናገረው የመጨረሻውን ፍጹምነት ሲሆን፥ ጳውሎስም አሁን ፍጹም መሆን የሚለውን አይቀበልም። መንፈሳዊ ብስለት ከሥጋዊ እድገት ጋር ሊወዳደር ይችላል። ዳሩ ግን ይህ አሳብ ሙሉ እድገትን የሚያሳይ ቢሆንም ፍጹምነትን ግን አያመለክትም። ፊልጵስዩስ 3፡15 ውስጥ ግን ፍጹምነት እንደተደረሰበት ሆኖ ቀርቧል። በሌሎች ክፍሎች የመንፈሳዊ

ብስለት የተለየ ገጽታ ይታይ ይሆናል። ከታወቀው የእግዚአብሔር ፈቃድ አንጻር በመንፈሳዊ ሕይወታችን የበሰልን እንሆን ይሆናል (ቈላ. 4፡12) ['ቴሌዮ']፥ ወይ በፍቅር (1ኛ ዮሐ. 4፡17-18) ['ቴሌዮ']፥ በቅድስና (2ኛ ቆሮ. 7፡1) ['ቴሌዮ']፥ በትዕግሥት (ያዕ. 1፡4) ['ቴሌዮ']፥ "በመልካም ተግባራት ሁሉ" (ዕብ. 13፡21) ['ካታርቲዞ'] የበሰልን ልንሆን እንችላለን። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ለአንዴና ለመጨረሻ ወደዚህ ስኬታማነት (ፍጹምነት) የመድረስን ነገር ጨርሶ አናይም። ፍጹምነት በተሻለ ሁኔታ ላይ ከመድረስ አንጻር በየወቅቱ የሚታይ ነው።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 7፡1፥ "እንግዲህ ወዳጆች ሆይ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።" እንዲሁም በገላትያ 3፡3፦ "እንዲህ የማታስተውሉ ናችሁን? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን?" በሚሉት ዓረፍተ ነገሮች በሰዋሰው ሥርዓት የአሁን ጊዜን የሚያሳይ አሳብ ስላላቸው፥ መንፈሳዊ ብስለት ከማያቋርጥ እድገት ጋር ተገልጦ እናያለን። በክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ስጦታ ዓላማ፥ "...ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ['ካታርቲስሞን'/'katartismon'] እንሆን ዘንድ ነው" (ኤፌ. 4፡12)። ይህ በሁሉም ነገር ቅዱሳንን ፍጹም የማድረግ አሳብ ነው። ስጦታዎቹን በመለማመድ በአንጻራዊነት ወደሚገኝ ፍጹምነት ሊደርስ የሚችል የመንፈሳዊ ብስለት ሂደትም ነው። ይህንና ሌሎችንም ክፍሎች አሁኑ ከሚኖረው ያለ ኃጢአት ከመሆን ጋር ለማያያዝ መሞከር፥ አሳቡን ወደ ራስ አሳብ የመጠምዘዝ ተግባር ነው። ይህን የመጠምዘዝ አሳብ፥ ግሪክኛው ቃልና በአጠቃላይም የተገለጡት እውነቶችና የሕይወት ልምምዶች ውድቅ ያደርጉታል።

የዚህ እውነት ሦስተኛ ገጽታ ስለ መጨረሻው ፍጹምነት በሚናገሩ ክፍሎች የተገለጠው አሳብ ነው። ለዚህ ጉዳይ ግልጥ የሆነውን አሳብ የምናገኘው፥ ከላይ በጠቀስነው በፊልጵስዩስ 3፡12፥ "አሁን ፍጹም እንደሆንኩ አይደለም" ሲል ጳውሎስ በተናገረው ቃል ነው። በክርስቶስ ያለው ስፍራ ፍጹም ቢሆንም እንኳ፥ ጳውሎስ የተጠቀመው ግሥ ('ቴቴሌዮማይ') ['teteleiomai'] የቅርብ ኃላፊ ጊዜን የሚያመለክት ስለሆነ (ዕብ. 10፡14)፥ የመጨረሻ ሙሉ ፍጹምነት ለሙታን ትንሣኤ ቀን እንደተጠበቀ መገንዘቡን ያሳያል (ፊልጵ. 3፡11)። ያን ዕለት በነፍስ፥ በመንፈስና በሥጋ ፍጹም ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ምድር ወደ ሙሉ ፍጹምነት መድረስ እንደሚቻል መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም።

*የቅድስና ፅንሰ-አሳብ።* መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅድስና የተሟላ ትምህርት ያስተምራል። ይህን ትምህርት በትክክል ስንገነዘብ፥

መጠራታችን የተቀደሰ መሆኑ ብሩህ ሆኖ ይታየናል። የቅድስና ትምህርት በተሳሳተ መልክ ከመታየቱ የተነሣ፥ በዚህ ምድር ሙሉ ለሙሉ ፍጹም መሆን እንችላለን የሚል ትምህርት ወደማቅረብ ተደርሷል። በዚሁ መሠረት ክርስቲያኖች ለጠቅላላ ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲለምኑ ተነግሯቸዋል። በአንዳንዶች አመለካከት ይህ ጉዳይ "ሁለተኛው የጸጋ" ሥራ ተብሏል። ከዚህ የተነሣ ፍጹምነትን ያልጨበጡ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ለመከተል ያልፈቀዱ በደለኞች ሆነው ተቆጥረዋል።

መቀደስ፥ ቅድስና፥ ቅዱስ፥ መለየት የተሰኙትና ሌሎችም ቃሎች 'ሃጊያዞ' ['hagiazo'] ከሚለው የግሪክ ቃል የመጡ ናቸው። እነዚህ ቃሎች በሙሉ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን፥ ታየር እንደተባለው ሰው አተረጓጎም፥ "የተለየ ወይም የተቀደሰ" ማለት ነው። ሁለተኛ ትርጉም አድርገን የምንወስደው "ከንቱ ከሆነ ነገር ተለይቶ ለእግዚአብሔር መሰጠት" እና "መንጻት" የሚለውን ነው። ሦስቱ ዋና ዋና አሳቦች (ማቅረብ፥ መለየትና መንጻት) በማዕከላዊው የመቀደስ አሳብ ውስጥ ያሉ ናቸው። ይህ መሠረታዊ ትምህርት በብሉይ ኪዳን መሥዋዕትና ቁርባን ውስጥ ጥሩ መሠረት ያለው ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን በተጨማሪ በተገለጠ እውነት ይበልጥ ተብራርቷል። በአዲስ ኪዳን በአጭሩ እንደቀረበው፥ ቅድስና ፍጹምነትን ከሚመለከተው የእምነት ትምህርት አከፋፈል ጋር በመጠኑ በሚያያዝ መልኩ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተመድቧል። እነርሱም፦ "ስፍራዊ (የመብት ስፍራን የሚመለከት) ቅድስና"፥ "ልምምዳዊ (ተግባራዊ) ቅድስና" እና "የመጨረሻ (የወደፊት) ቅድስና" ናቸው። በሰፊው ያየነው እንደሆነ በቅድስና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ የሚገኘው አሳብ በተለይ የሚያተኩረው ከፍጹምነት ይልቅ ለቅድስና ወይም ለተቀደሰ አገልግሎት መለየት በሚለው ላይ ነው። ቅድስና ሕይወት ለሌላቸው ነገሮችም ያገለግላል። ለምሳሌ ወርቅ በቤተ መቅደስ ተቀድሷል (ማቴ. 23፡17)፥ ያላመነ ባል ባመነች ሚስቱ፥ ያላመነች ሚስት ባመነ ባልዋ ተቀድሰዋል (1ኛ ቆሮ. 7፡14)፥ ምግብ በጸሎት ይቀደሳል (1ኛ ጢሞ. 4፡5)። ቅድስና ክርስቶስን ለተቀደሰ ሥራ ከመለየቱ አንጻርም አገልግሏል (ዮሐ. 10፡36፤ 17፡19፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡ 15)። ቅድስና፥ በዚህ ስሜት፥ ማንጻት ሳይሆን ካልተቀደሰ ነገር ለይቶ ለተቀደሰ አገልግሎት ለእግዚአብሔር ማቅረብ ማለት ነው።

አዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ የሚናገረው፥ ክርስቶስ ለአማኙ ስለሠራውና እርሱም ከዳነበት ጊዜ ጀምሮ ስላገኘው ቅዱስ ስፍራ ነው። በአዲስ ኪዳን በግምት ወደ ስድሳ አምስት ጊዜ ቅዱሳን ተብሎ የተጠቀሰው

ቃል በዚህ ክፍል ይመደባል። በጣም አስፈላጊ የሆኑና ልናነሣቸው የሚገቡ ክፍሎችም አሉ (ሐዋ. 20፡32፤ 26፡18፤ ሮሜ 15፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡2፥ 30 ፤ 6፡11፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13፤ ዕብ. 2፡11፤ 10፡10፥ 14፤ 13፡12፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ ይሁዳ 1)። እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነው አንድ ክፍል በተለይ አስቸጋሪና ብልሹ ዓለማዊ ሕይወት የነበራቸው የቆሮንቶስ ሰዎች "ቅዱሳን" ተብለው የተጠሩበት ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡2)። ቅድስና ማለት ያለ ኃጢአት መሆን ማለት እንዳልሆነ ይህ ክፍል ብቻውን ያረጋግጥልናል።

ልምምዳዊ ቅድስና ስፍራዊ ቅድስናን ያህል ባይጠቀስም፥ እጅግ አስፈላጊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው። በዮሐንስ 17፡17፥ "በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው" ሲል ጌታ በጸለየው ጸሎት የምናገኘው ቅድስና ይህን የመሰለ ቅድስና ነው። ይህ ቅድስና የተጠቀሰበት ሌላ ሁኔታ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ የሰጠበት ጉዳይ እንደሆነ በኤፌሶን 5፡26 ላይ ይናገራል፡- "በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ።" ብዙዎች ይህን ጥቅስ ስለ ውኃ ጥምቀት የሚናገር ነው ቢሉም፥ ጥቅሱ ራሱ የሚደግፋቸው አይደለም። ይልቁን ስለ እግዚአብሔር ቃል የመቀደስ ኃይል የሚናገር ይመስላል። በዕብራውያን 9፡13-14 ደግሞ የክርስቶስ ደም እንደ ማንጻ መሣሪያ ሆኖ ተገልጧል። በምድራዊ ሕይወታችን ከኃጢአት ሊያነጻን እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ ሁሉ ቅድስና በሚለው ቃል ተጠቀሰም አልተጠቀሰ ይህን እውነታ የሚያሳይ ነው። ቅዱሳን የልምምድ ቅድስናን አስፈገላጊነት እንዲገነዘቡ ተነግሯቸዋል (1ኛ ተሰ. 4፡3-4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡18)። የዚህ ቅድስና ገጽታ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ዋና ግብ ሲሆን፥ ተግባራዊ የሚሆነው በመንፈስ በመመላለስ ነው።

ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር በመንፈስ መመላለስ በሚለው ጽሑፉ በሚገባ እንደገለጠው፥ ልምምዳዊ ቅድስና ሦስት ግንኙነቶች አሉት። እነርሱም፡- 1. የአማኙ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር መስጠት፥ 2. የአማኙ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከኃጢአት ኃይል ነጻ መሆን፥ 3. የአማኙ ያለማቋረጥ በጸጋ ማደግ ናቸው። ይህ የመንፈሳዊ ሕይወት መሠረታዊ ትምህርት እምብርት ስለሆነ፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከልቡ ሊያጠናውና ሊጸልይበትም ይገባል።

"የመጨረሻው ቅድስና" እግዚአብሔር በአማኝ የሚያከናውነው ሥራ ውጤት ነው። ስፍራን የሚመለከተው ቅድስና፥ የቅዱሳን የዘላለም ዕድል ፋንታ የሆነው "የመጨረሻ ቅድስና" ነው። ልምምዳዊ ቅድስና በመጪው ሕይወት እንደ መጨረሻ ግብ የሚፈጸም መሆኑ ይታወቃል። የመጨረሻ ቅድስናን የሚመለከተው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የተገኘው፥ በዚህ የሕይወት ዘመናችን ልንደርስበት የምንፈልገውን ግብ

ከሚያሳዩት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ነው። ለምሳሌ በ1ኛ ዮሐንስ 3፡2፥ “ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን” የሚል ቃል እናነባለን። ይህ ጥቅስ የመጨረሻ ቅድስና የሚሆንበትን ጊዜ በመጠቆም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በኤፌሶን 5፡27፥ አሁን ያለንበት ቅድስና ወደፊት ፍጹም በሚሆንበት መልኩ ቀርቧል፦ “እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።” በሮሜ 8፡29 ደግሞ፥ “የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗል” ተብሏል። ይህ ወደፊት የሚፈጸም ነው። በዕብራውያን 12፡14፥ እያንዳንዱ አማኝ ጌታን በሚያይበት ጊዜ ፍጹም እንደሚቀደስ ተገልጧል። እነዚህና ሌሎችም ብዙ ተመሳሳይ ጥቅሶች በአንድ ላይ ሆነው የወደፊቱ ዘላለማዊ ሁኔታ በሁሉም አቅጣጫ የመጨረሻ ፍጹምነት የሚገኝበት መሆኑን ያሳያሉ። እነዚህ ጥቅሶች በግልጥ የሚያሳዩት የመጨረሻ ቅድስና በወደፊት ሕይወት ዘመን የሚደረስበት መሆኑን ነው።

ፍጹም ቅድስና በምድር ላይ ሊገኝ ይችላል የሚለውን አሳብ ለመደገፍ የሚጠቀሱ ጥቅሶችን በጥንቃቄ ስንመረምር፥ ቀደም ሲል ካየናቸው እውነታዎች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን እናያለን። የተሳሳተ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት የሚመነጨው ከሦስት ነገሮች ነው። የመጀመሪያው ስሕተት ስፍራዊ ቅድስና ማለት በዚህ ሕይወት ፍጹም ያለ ኃጢአት መሆን ነው ብሎ መረዳት ነው። ስለ ትምህርቱ የሚናገሩ ክፍሎችን በማጥናት ይህን አሳብ በቀላሉ ውድቅ ለማድረግ ይቻላል። ቅዱሳን በክርስቶስ ያላቸው ስፍራ ፍጹም ቢሆንም፥ ኃጢአት እንደሚያደርጉ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይናገራል። ሁለተኛው የተሳሳተ ግንዛቤ ምክንያት ደግሞ ቅድስና የሚለው ቃል ራሱ ለተለያየ ጥቅም መዋሉን ያለመረዳት ነው። ቅድስና የሚለው ቃል ያለ ኃጢአት የመሆንን ስሜት በሚያመለክት መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አገልግሎት ላይ አልዋለም። መለየትን ወይም መንጻትን በሚያመለክት ሁኔታ ቢጠቀስ እንኳ እንደ ፍጹምነት ሊቆጠር አይገባም። ሦስተኛው የተሳሳተ አሳብ ለደኅንነት ያለ ኃጢአት መሆን ያስፈልጋል የሚል ሲሆን፥ ይህ ነጥብ በአንዳንድ ይህን አሳብ የሚደግፉ በሚመስሉ ምንባቦች ላይ የተመሠረተ ነው። በእነዚህ ምንባቦች ላይ የሚደረግ ጠንቃቃ ጥናት ችግሮቹን ያቃልላቸዋል።

ያለ ኃጢአት መሆን ለደኅንነት አስፈላጊ ነው የሚለው የተሳሳተ አሳብ የተመሠረተው በ1ኛ ዮሐንስ 3፡6-9 ነው፦-

"በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም፥ አላወቀውምም። ልጆች ሆይ፥ ማንም አያስታችሁ። እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአት ያደርጋልና። ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና። ከእግዚአብሔርም ተወልዷልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።"

በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛው ንባብ የዚህን ክፍል ፅንሰ-አሳብ በተሳሳተ መንገድ የመረዳት ሁኔታ አለ። በግሪኩ ግን ችግሩ እምብዛም ነው። ክፍሉ በሙሉ የቀረበው በአሁን ጊዜ ሰዋሰዋዊ አገባብ ነው። በዚህ ስፍራ የተሰጠው መገለጥ የሚያስረዳው፥ ያለማቋረጥ ኃጢአት የሚያደርግ ወይም ባሕርዩ በኃጢአት መኖር የሆነ ሰው ያልዳነ መሆኑ ነው። ዳግም የተወለዱና በክርስቶስ የሆኑ ሰዎች፥ አዲስ ፍጥረት ስለሆኑ ያለማቋረጥ በኃጢአት ውስጥ ሊኖሩ አይችሉም። በሁለት መንገድ ሊታዩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ፍርድ መስጠት አስቸጋሪ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ኃጢአት የሚሠሩ ክርስቲያኖችን እንደሚቀጣ፥ በተለያዩ መንገዶች እየተገናኘም ወደራሱ እንደሚመልሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ራሳቸውን ሳይቆጣጠሩ ያለማቋረጥ በኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ደኅንነት፥ በሰብአዊ አእምሮአችን በጥያቄ የመመልከት መብት አለን።

ከ1ኛ ዮሐንስ 3፡6-9 መልእክት ለሚወጣ የተሳሳተ አተረጓጎም ሌላ መፍትሔ ለመስጠት "አዲስ ፍጥረት" የሚለው ቃል ፅንሰ-አሳብ ጠቃሚ ነው። በዚህ አቀራረብ መሠረት፥ ትምህርቱ አዲስ ፍጥረት፥ ማለት ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን አያደርግም የሚል ይሆናል። በእግዚአብሔር የተሰጠው አዲስ ፍጥረት በአማኙ ሕይወት ውስጥ ኃጢአት የማያመነጭ መሆኑ እውነት ነው። ትርጉሙን እስከዚህ ድረስ ለመቀበል ይቻላል። ነገር ግን ምንባቡ ክፍሉ የሚጠቀምበት ግሥ የአሁን ጊዜ መሆኑ፥ ኃጢአት የሚቀጥል ባይሆንም እንኳ አልፎ አልፎ የመከሠቱን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። አሳቡ አዲሱ ፍጥረት ኃጢአትን ጨርሶ አያደርግም የሚል ቢሆን ኖሮ በሰዋሰው አጠቃቀሙ ከአሁን ጊዜ ይልቅ ያልተወሰነ ጊዜን ይጠቀም ነበር። ምንባቡ በአሁን ጊዜ የመሆኑ ጉዳይ የመጀመሪያውን መፍትሔ የተሻለ ያደርገዋል።

በማንኛውም ረገድ ያለ ኃጢአት መሆን ለደኅንነት አስፈላጊ ነው የሚለው ትምህርት፥ የጸጋንና የዋስትናን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ከመሻሩም ሌላ ደኅንነትን በሰው ሥራ ደረጃ ዝቅ ያደርገዋል። በዚህ

ምክንያት ታሪካዊት በሆነችው ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የእምነት ትምህርቶችን የመገንዘብ ጉድለት ቢኖርም፥ ያለ ኃጢአት መሆን ብቻውን ለደኅንነት መሠረታዊ ነገር አለመሆኑን አበክራ አስገንዝባለች። መሠረታዊው የቅድስና ትምህርት ለእግዚአብሔር ክብር መስጠትን ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈስ መመላለስም አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ መገለጥ ለአማኙ ይሰጠዋል። ደኅንነት ከእግዚአብሔር ኃይል ውጭ በምንም አኳኋን የማይሆን ጉዳይ ነው።

*የኃጢአትን ባሕርይ የመደምሰስ (ከሥሩ ነቅሎ የመጣል) ፅንሰ-ሐሳብ [Eradication/ኤራዲኬሽን]።* በምድራዊ ሕይወት የኃጢአት ባሕርይን ነቅሎ በመጣል እንዳይሠራ ከሚደረግበት ወይም ከሚደመሰስበት መንፈሳዊ የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ይቻላል የሚል ትምህርት በመስፋፋት ላይ ነው። ይህ አሳብ በዚህ ሕይወት ፍጹምነትና ያለ ኃጢአት የመሆን አሳቦችን በአንድነት አቀናብሮ ለማቅረብ የሚሞክርና በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ለማድረግ የሚጥር ነው። ፅንሰ-አሳቡ ከበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር የሚጋጭና ለአዎንታዊ ልምዶች እንግዳ በመሆኑ በአስተዋይ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ከሥጋ ጋር ስለሚካሄድ ትግልና ለመዋጀት በእግዚአብሔር ላይ ስለመደገፍ አጠቃላይ አስፈላጊነት የሚናገሩ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊታለፉ የማይችሉ የዚህ ትምህርት እንቅፋቶች ናቸው።

የኃጢአትን ባሕርይ ማሸነፍ ስለሚቻልበት መለኮታዊ መንገድ ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር እንደጻፈው፡-

> "በአማኙ ሕይወት ውስጥ የኃጢአትን ባሕርይ ማሸነፍን የሚመለከቱ ሁለት የተለያዩ አጠቃላይ መለኮታዊ መንገዶች መኖራቸውን የሚቀበሉ ንድፈ አሳቦች አሉ። የመጀመሪያው ንድፈ አሳብ አሮጌው ተፈጥሮ አንድ ሰው በሚድንበት ጊዜ ወይም ከደኅንነት በኋላ ባሉ መንፈሳዊ በረከቶችና ልምምዶች ይወገዳል የሚል ነው። የአንድ አማኝ ሕይወት ብቃት የሚለካውም የኃጢአት ተፈጥሮው ዝንባሌ ከመወገዱ አንጻር ነው። ሌላው ንድፈ አሳብ ግን አሮጌው ተፈጥሮ ክርስቲያን በአካለ ሥጋ እስካለ ድረስ የሚኖር ሲሆን፥ የሕይወቱ ጥራትና ብቃት የሚለካው የእግዚአብሔር መንፈስ በሥጋ ላይ በሚያደርገው ቀጽበታዊና የማያቋርጥ ቁጥጥር ነው። ይህ ሊሆን የቻለው በክርስቶስ ሞት አማካይነት ነው ይላል። እነዚህ ሁለት ንድፈ አሳቦች አማኝ በእግዚአብሔር የተሰጠውን የድል ተስፋ እንዴት በዕለታዊ ኑሮው በልባዊ ጥረት ሊለማመደው እንደሚችል ያሳያሉ።

የሁለቱም ንድፈ አሳቦች ግብ ከኃጢአት ባርነት ነጻ የወጣ ሕይወት ነው። ስለዚህ በግንዛቤው ውስጥ ያለው ጥያቄ የእግዚአብሔር እቅድና መንገድ የትኛው ነው? የሚል ይሆናል። ሁለቱ ንድፈ አሳቦች እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ እውነት ሊሆኑ አይችሉም።"

ቼፈር የኃጢአት ባሕርይን ስለመደምሰስ የሚያወሳው ንድፈ አሳብ እግዚአብሔር ከአማኙ ጋር ያለውን ጉዳይ የሚያካሂድበት መለኮታዊ መንገድ እንዳልሆነና፥ ንድፈ አሳቡ በልምምድ የሚታየው ነገር ተቃራኒ መሆኑን ከተመለከተ በኋላ ይህ ንድፈ አሳብ ከመለኮታዊ መገለጥ ጋር እንደማይስማማ ለማረጋገጥ ሰባት አሳቦችን አቅርቧል፦

"በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ 'ትምህርት'፥ 'ተግሣጽ' እና 'ምክር' ይገኛል። ስለዚህ ማጠቃለያችን በየትኛውም የአእምሮ አስተሳሰብ ወይም በማንኛውም ግላዊ ልምድ መሆን የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን፦

"1. አማኞች በሙሉ የኃጢአትን ባሕርይ ከመደምሰስ ንድፈ አሳብ እንዲጠነቀቁ መመከራቸውን ነው፤ '[የ]ኃጢአት [ባሕርይ] የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም' (1ኛ ዮሐ. 1፡8)።

"2. መንፈስ ቅዱስ የመጣው ነጻ ሊያወጣን ነው፤ ስለዚህ ድላችን የተመሠረተው በሌላ ነገር ከሆነ ስለርሱ ሕልውና፥ ዓላማና ኃይል ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ነገር ትርጉም የለሽ ይሆናል። ለዚህ ነው ስለ ኃጢአት ባሕርይ መደምሰስ የሚያወሳው ንድፈ አሳብ ለመንፈስ ቅዱስ ሕልውናና ሥራ አነስተኛ ስፍራ የሚሰጠው።

"3. መንፈስ ቅዱስ ነጻ የሚያወጣን በማያቋርጥ ትግል ነው። 'ሥጋ [አሮጌውን ተፈጥሮ የሚጨምረው] በመንፈስ ላይ፥ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ። ስለዚህ [በመንፈስ ስትመላለሱ] የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም' (ገላ. 5፡17ን ከያዕቆብ 4፡5 ጋር ያነጻጽሩ)። ደግሞም በሮሜ 7፡15-24 እንዲሁም 8፡2 በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚታየው የኃጢአት ምንጭ በሥጋ የሚሠራ የኃጢአት ባሕርይ ነው። ድል የሚገኘውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ነው። አክራሪነት የሚታይበትና የኃጢአት ባሕርይን መደምሰስ ንድፈ አሳብ የሚያቀነቅነው ትምህርት፥ ክርስቲያን ነገ ኃጢአት የመሥራት ዝንባሌ አያሳይም ስለሚል፥ ሰው በእውነተኛ ጥንቃቄ ነቅቶና በእግዚአብሔር ላይ ተደግፎ እንዳይኖር ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ድብቅ ኃይል ነዋሪ ስለሆነ

'በመንፈስ መመላለስ' ስናቋርጥ የሥጋ 'አምሮትና' 'ምኞት' ወዲያውኑ ይመለሳል ብሎ ያስተምራል። ስለዚህ 'በመንፈስ የምትመላለሱ እንደመሆናችሁ የሥጋን ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።'በልማድ የምንገዛ ፍጥረታት ስለሆን በመንፈስ የመመላለስን እድገት ልንለማመድ እንችላለን። እውቀትን በልምድ ጭምር እናካብታለን። ስለዚህ 'በሥጋ' መመላለስ በተወሰነ ጊዜ ሊቆም ሲችል፥ 'በሥጋ' የመኖር ችሎታ ግን ሁልጊዜ ይኖራል። በዚህ ረገድ እውነተኛ መንፈሳዊነት ማለት፥ ለጊዜው ኃጢአትን ለማድረግ አለመፈለግ ማለት ነው (ፊልጵ. 2፡13)። ይህ ድርጊት ግን ኃጢአት የማድረግ ችሎታን የሚያስወግድ ወይም የኃጢአት ባሕርይን የሚደመስስ አይደለም። ቢሆንም ብርታትን በሚሰጠው የእግዚአብሔር ኃይል ለአሁን የሚሆን ፍጹም ድል ለማግኘት ይቻላል። ሁልጊዜ በሙላት እርሱን መፈለጋችን እውነት ነው። ጌታ 'ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም' (ዮሐ. 15፡5) ብሏል። የኃጢአት 'መርዝ' ሁልጊዜ በውስጣችን ስላለ፥ በማንኛውም ጊዜ 'አሸናፊ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ የማጥቃት ሥራ' ያስፈልገናል። ማንኛውም መንፈሳዊ እርምጃችን በመለኮታዊ ኃይል እርዳታ የምንራመደው ነው።

"4. እምላክ በቸርነቱ 'የሥጋንና የአሮጌውን ሰው' ጉዳይ ማየቱ የኃጢአት ባሕርይን መጥፋት አያመለክትም። እኛ 'በአዲስ ሕይወት መመላለስ' እንችል ዘንድ፥ እግዚአብሔር በልጁ ሞት በኩል መንገድ አዘጋጅቶልናል። የመመላለሱ ሁኔታ 'ቁጠሩ'፥ 'ስጡ'፥ 'አውልቁ'፥ 'ግደሉ'፥ 'ኑሩ' የሚሉትን በመሳሰሉ ትእዛዛት የተገለጠ ሲሆን፥ የትኞቹም ትእዛዛት በኃጢአት ባሕርይ መደምሰስ ንድፈ አሳብ ውስጥ ካሉ አዛማጅ ትርጉሞች ጋር የሚሄዱ አይደሉም። ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩን፥ ኃጢአታዊ ተፈጥሮ እንደሞተ እንድንቆጥር ሳይሆ ን፥ እኛ ለኃጢአት የሞትን መሆናችንን ነው።

"5. የኃጢአት ባሕርይን መደምሰስ ንድፈ አሳብ የሚከተሉ ሰዎች የያዙት ትምህርት፥ መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ስላለው ኅብረት የሚናገረውን በተሳሳተ መንገድ ከመተርጎም የተነሣ የሚፈጠር ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኝ ስፍራን ይመለከታል ተብሎ የሚታመነው ቅድስና (በእግዚአብሔር አሳብ እንዲሁም እይታ ውስጥ ብቻ ያለው)፥ ለእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚከናወን ነው። ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ አሳብ፥ ራሳቸውን ከኃጢአት ዝንባሌ ነጻ አድርገው በሚመድቡ

በጥቂቶች ዕለታዊ ኑሮ ውስጥ የሚታይ ልምምድ ነው ተብሎ በተሳሳተ መንገድ ተወስዷል።

*"6. የዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ማጠቃለያ የተመሠረተው፥ መጽሐፍ ቅዱስ 'ሥጋ' ስለሚለው ቃል ለሚያስተላልፈው ትምህርት የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ላይ ነው። የዚህ ትምህርት አራማጆች 'ሥጋ' የሚለው ቃል ሁሉንም ማለት የፍጥረታዊውን ሰው መንፈስ፥ ነፍስና አካል የሚያመለክት መሆኑን አይረዱም። የኃጢአት መወገድ፥ በአካል ውሱንነት የተፈጠሩትን ችግሮች ሁሉ የማስወገድ ዝንባሌ የለውም። 'በእኔ [በአካሌ] ምንም መልካም ነገር የለም'። ስለዚህ 'ሥጋ' በ'ሸክላ ዕቃ' የተመሰለውና ያልከበረው (የተዋረደው) አካላችን እስካለ ድረስ ይኖራል። በእርግጥ አካላችን አይደመሰስም።*

*"7. የኃጢአት ባሕርይ መደምሰስን የሚመለከተው ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በልምድ ላይ ያተኩራል። ልምምድን ማስላሰል፥ ማጠቃለያውንም በዚህ አጠናን ላይ መመሥረትና ማረጋገጥ ሁልጊዜ የተለመደ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነጻ የመውጣት ተገቢ ልምምድ 'ኃጢአት የሌለበት ፍጹምነት'፥ 'አጠቃላይ የሆነ ቅድስና' እና 'የኃጢአት ባሕርይን የመደምሰስ' ማረጋገጫ አድርጎ ማቅረብም እንዲሁ ተለምዷል። ነገር ግን የሰው ግምት መለኮታዊ መገለጥን ሊተካ ጨርሶ አይችልም።*

*"ሁለቱ ንድፈ አሳቦች የማይታረቁ ናቸው። ነጻ የወጣነው አንድም የእግዚአብሔር እርዳታ ወይም ኃይል ሳያስፈልገን የኃጢአት ባሕርይ ዝንባሌያችን በቅፅበት ተወግዶ ነው፤ አለዚያም በመንፈስ ቅዱስ ቅጽበታዊና ቋሚ ኃይል ነው የሚለውን መቀበል ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ የሚያስተምረው ሁለተኛውን ነው።"*

*ለራስ የመሞት ንድፈ አሳብ።* የኃጢአት ባሕርይ መደምሰስን ከሚመለከተው ንድፈ አሳብ ጋር የሚቀራረበው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ክርስቲያን ፈቅዶ በሚያከናውነው ተግባር ሙሉ በሙሉ ለራሱ ሊሞት ይችላል የሚለው ነው። ፍጹምነትንም ሆነ የኃጢአት ባሕርይ የመደምሰስን ጽንሰ አሳብ የማይቀበሉ ሰዎች እንኳ ይህን ለራስ የመሞት አቋም ይዘው እናገኛቸዋለን። ችግሩ ያለው ራስን ስለ መስቀል ወይም ለራስ ስለ መሞት የሚናገሩ የመጽሐፍ ክፍሎች የሚገኙበትን የግሪክኛ ጥቅሶች ለመመርመር ካለመቻል ላይ ነው። እነዚህ ግሪክኛ ጥቅሶች የሚያመለክቱት ስላለፈ ጊዜ መሆኑን ያረጋግጣሉ። በክርስቶስ ውስጥ ያለ ክርስቲያን

ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ ሞቷል። ይህ የአሁን ጊዜ ልምምድ ሳይሆን የምትክነት እውነታ ነው። "አሮጌው ሥጋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ" (ሮሜ 6፡6) የሚለው ግሥ በኤሪስት ጊዜ መሆኑ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለዘላለም የፈጸመውን ሥራ ያመለክታል። ይበልጥ ወሳኝነት ያለው በገላትያ 2፡20 የሚገኘው ጥቅስ ነው:- "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፥ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።" "ተሰቅዬአለሁና" የሚለው ግሥ የቅርብ ኃላፊ ጊዜ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ውጤቱ ግን በመቀጠል እስከአሁን ደርሷል። "ተሰቅዬአለሁና" ከሚለው የቅርብ ኃላፊ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር "አሁን የምኖረው እኔ አይደለሁም" በማለት ጳውሎስ ግሡን በአሁኑ ጊዜ ገልጦታል። የጳውሎስ ሕይወት አሁን ድል ሊያገኝ የቻለው፥ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ በመሞቱ ነው። ምክሩ በራሳችን ድርጊት ለራሳችን እንድንሞት ሳይሆን፥ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ መሞታችንን እንድንገነዘብና በዚህ የመገለጥ ብርሃን መኖር እንድንችል ነው። አስፈላጊ የሆነው እውነት ለራሳችን እንደሞትን እንድንቆጥርና ይህም ያለማቋረጥ ልናደርገው የሚገባ መሆኑን መረዳት ይሆናል።

ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ መሞቱ የኃጢአት ባሕርይውን አያስወግድም ወይም ኃጢአት የማይሠራ አያደርገውም። ስለ አማኞች ከክርስቶስ ጋር መሞት የሚናገረውና ሮሜ 6 ላይ ያለው ጠቃሚ ክፍል እንደዚህ በማለት ይመሰክራል:- "እንግዲህ ለምኞቱ እንዳትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ" (ሮሜ 6፡12)። ክርስቲያን ራሱን ለኃጢአት [ባሕርይ] እንደሞተ መቁጠር አለበት፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ ሊሆን ይችላል። የክርስቶስ ሞት ለኃጢአት ቤዛ መሆን ብቻ ሳይሆን፥ አማኝ ከኃጢአት እሥራትና ብልሹነት ነጻ የሚወጣበትን ኃይል ይሰጠዋል።

*የሥጋ ፍጹም ደካማነት።* የፍጹምነት፥ የመቀደስ፥ የኃጢአት ባሕርይ መደምሰስና ለራስ የመሞት መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በእግዚአብሔር ቃል መገለጥ መሠረትነት ብንረዳቸው፥ ስለ ሥጋ ደካማነትና እያንዳንዱ አማኝ ድል ለማድረግ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ የሚገባው ስለመሆኑ ጠንካራ ምስክርነት ይሰጣሉ። ኃጢአታዊ ተፈጥሮን የሚመለከተው መሠረታዊ ትምህርት፥ አማኝ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመኖር የሰይጣን ኃይል፥ የጨለማ ሠራዊትና ሰዎችን የሚያበላሸው የዓለም ባሕርይ ስለሚገጥመው፥ ኃይል ሰጭ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ማግኘቱ እጅግ የሚያስፈልገው

መሆኑን ያመለክተናል። ክርስቲያን የሚቀናቀኑትን ኃይላት ድል ለማድረግ፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከመኖርና በመንፈስ ከመመላለስ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለውም።

*የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን።* መካከለኛ ወይም ያልጸና ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ተገቢ የሆነ የክርስትና ድል እንዳያገኝ የሚያግደውን ችግር የሚረዳው በድንግዝግዝ መሆኑ አያጠራጥርም። የክፋት ኃይላትን ማሳወቅና ያለ እግዚአብሔር እርዳታ እነርሱን መጋፈጥ የማይቻል መሆኑን ግልጥ የማድረግ ትእዛዝ የግድ አስፈላጊ ነበር። ጦርነትን ለማካሄድ መወሰድ ያለበት የመጀመሪያ እርምጃ ጠላትንና የራስን መሣሪያ ማወቅ ነው። በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ የተካተቱት በርካታ ነገሮች “መንፈስ አታጥፉ”፥ “መንፈስን አትሳዝኑ”፥ “በመንፈስ ተመላለሱ” በሚሉ ቀላል ዓረፍተ ነገሮች ተጠቃለዋል። ይህ የትምህርት ጉዳይ ብቻ አይደለም። እውነቱን መረዳትና ሙሉውን የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈለግ ተገቢ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚፈልግ አማኝ ራሱን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚገለጥበት ቃል ጥናት ሊሰጥ ይገባል። ፈቃዱን ለማድረግ ፈቃደኞች ሆነን እንገኝ ዘንድም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆየት ያስፈልጋል። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ባለን ኅብረት መነቃቃትና የርሱን በረከት ከሕዝቡ ጋር መካፈል በጣም አስፈላጊ የሆነ የእርዳታ ምንጭ ነው። በመንፈስ መመላለስና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተያያዙ ናቸው። ይህ ጠላትን የመከላከል አቋም ሳይሆን፥ ለመንፈሳዊ ሕይወት ችግር መፍትሄ መሻትና በእግዚአብሔር ፈቃድና በእርሱ ብቃት ላይ የማረፍ ጉዳይ ነው። ዋናው ነገር ልናደርገው ያልቻልነውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲያደርግልን ያለማቋረጥ በእርሱ ላይ መደገፍና ለምሪቱ ራስን የመስጠት እንዲሁም የታወቁ ኃጢአቶችን ሁሉ የመናዘዝና የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት በእምነት የመፈለግ ጉዳይ ነው፤ “ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና” (ፊልጵ. 2፡13)። በመንፈስ መመላለስ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግ ጥልቅ ደስታ የሚታወቅበት፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በአማኙ ልብና ሕይወት ውስጥ የሚታይበትና ከፍተኛ ደስታ የሚያገኝበት ነው። በመጨረሻም እርሱ ድል ባደረገበት በዚህ ዓለም ላይ ድል ይኖረን ዘንድ የተሠቃየውን ከሞት በድል አድራጊነት የተነሣውን ጌታ የከበረ ፊት ስናይ የሚኖረንን ወሰን የሌለው በረከት አሻግረን የምናይበት ይሆናል።

# 23

# የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤቶች

በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤት በሁሉም የክርስትና ሕይወት ልምምድ ውስጥ ይገለጣሉ። የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን የታጠቀና በርሱ የተመራ ሕይወት የተለያዩ መንፈሳዊ ብቃቶች እንደሚታዩበት ግልጥ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመር እግዚአብሔር በቅድስና፥ በመንፈሳዊነትና በአገልግሎት ውስጥ ያለው የአሁን እቅድ በመንፈስ በመሞላት የሚረጋገጥ መሆኑን ለመረዳት ይረዳል። ቢያንስ ቢያንስ ሰባት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤቶች አሉ።

## 1. ልምምዳዊ ቅድስና

ቀደም ሲል እንደተነጋገርነው ቅድስና በሦስት ዓይነት ሁኔታዎች ይታያል። እነርሱም ስፍራዊ ፥ ልምምዳዊ እና የመጨረሻ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በተለይ የተያያዘው በአሁኑ ጊዜ ከሚሆነው ከምንለማመደው ቅድስና ጋር ነው። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የሆነና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽም ኃይል የተሰጠው ክርስቲያን መሠረታዊ የባሕርይ ለውጥ ያሳያል። የቀድሞው የኃጢአት ባሕርይ አሁንም ያለ ቢሆንም፥ እንደሞተ ስለሚቆጠር አዲሱ ባሕርይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመንፈስን ፍሬ ያፈራል። በገላትያ 5፡22-23 በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ፍሬ እንደሚያፈራ ተጽፏል፦ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።" ይህን ክፍል በቅርበት ልናጠናው ይገባል። ስኮፊልድ የተባለው ጸሐፊ እንደጠቆመው፥ በአንዳንዶች ዘንድ ይህ በሦስትዮሽ ሊቀርብ የሚችል ነው ተብሏል።

> "ክርስቲያናዊ ባሕርይ የሥነ-ምግባር ወይም የሕግ ትክክለኛነት ብቻ አይደለም። ነገር ግን የዘጠኝ ጸጋዎች ባለቤትነትና መግለጫ ነው፦ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም- የውስጣዊ ክፍል ባሕርያት መግለጫ፤ ትዕግሥት፥ በጎነት፥ ቸርነት- ለሰዎች የሚገለጥ ባሕርይ መግለጫ፤ እምነት፥ የዋህነት፥ ራስን መግዛት- ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ ባሕርያት መግለጫ ናቸው። በአንድነት ያየናቸው እንደሆን እነዚህ የክርስቶስን ግብረ ገባዊ ሥዕል ያቀርባሉ። በመሆኑም ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ 2፡20፥ 'እኔ አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል' ሲል የተናገረውን ቃል የሚገልጡ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ደግሞም በዮሐንስ 15፡1-8 የተጻፈው 'ፍሬ'

የሚለው ቃል መግለጫ ሆነው እንደቀረቡ አድርገን ለማሰብ እንችላለን። አማኝ ይህ ባሕርይ ሊኖረው የቻለው፥ ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት ነው (ዮሐ. 15፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። ራሳቸውን በሰጡ ክርስቲያኖች ሕይወትም የሚታይ የመንፈስ ፍሬ ነው" (ገላ. 5፡22-23)።

በዚህ ክፍል የምናገኘው ሌላ አመለካከት፥ የመንፈስ ፍሬ ፍቅር ሲሆን፥ ቀጥሎ ከርሱ የፍቅር ማስረጃዎች የሆኑት ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ በጎነት፥ ቸርነት፥ እምነት፥ የዋሃት፥ ራስን መግዛት ይፈልቃሉ። በአንጻራዊነት ሲታይ የአቀራረቡ ዘዴ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ማዕከላዊው እውነት፥ ልምምዳዊ ቅድስና የሚመነጨው፥ ከግል ጥረት ወይም ከፍጥረታዊ ሰው ፍላጎትና ፈቃድ ወይም ከአዲሱ ባሕርይ አይደለም። ለእግዚአብሔር በተሰጠ ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውነው ሥራ ነው። አጠቃላዩ እውነት የሚያሳየው እውነተኛ ክርስቲያናዊ ባሕርይ ከመንፈስ ቅዱስ ተነጥሎ ሊኖር እንደማይችል ነው። ስለዚህ በመሠረቱ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጠይቁት በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት ትክክለኛ ኅብረት እንዲኖር ሲሆን፥ በዚሁ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አዲሱ ፍጥረት በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር ያለው ምኞት ይረካል።

## 2. ማስተማር

የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር አገልግሎት ለሐዋርያት አገልግሎት አስፈላጊ የሆነ መገለጥን እንደሚሰጥ ክርስቶስ አስቀድሞ የተናገረ ሲሆን (ዮሐ. 16፡12-15)፥ በመጀመሪያ የተፈጸመውም በእነርሱ ነው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ረገድ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለሁሉም ተሰጥቷል። የእግዚአብሔር ቃል በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈ ሲሆን፥ መለኮታዊ ደራሲው መንፈስ ቅዱስ፥ ከሁሉም የተሻለ አስተማሪ ነው። ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን ያለማወቅ ችግር አይቶ እንዲህ አለ፦ "የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፥ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፥ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል" (ዮሐ. 16፡12-13)። ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ሞቱና ትንሣኤው፥ እንዲሁም ለአሁኑ ዘመን ያለውን ዓላማ ስለሚመለከት ታላቅ እውነት አልነገራቸውም። ምክንያቱም ይህን ትምህርት ለመረዳት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም። ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በሰጠው አገልግሎት እነዚህ ነገሮች ቢኖሩም፥ ከዚያ በኋላ ግን ዋናው መምህር መንፈስ ቅዱስ ነበር።

መንፈሳዊ ለሆኑ፥ ማለት በመንፈስ ለተሞሉ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ሊገልጥላቸው ይችላል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡9-3፡2 ያለው አሳብ የሚያስተምረን፥ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ሊረዱ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ለመማር መመዘኛዎችን ያለፉ ብቻ እንደሆኑ ነው። ፍጥረታዊው ሰው መንፈስ ለሚያስተምራቸው ሰዎች ቀላል የሆነውን እውነት እንኳ ለመረዳት አይችልም። ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያለማወቃቸው ምክንያት፥ ሥጋዊ መሆናቸውና በመንፈስ የተሞላ ሕይወት የሚያገኘውን በረከት ከመሻት መቆጠባቸው ነው። የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ ከስሕተት በማስጠንቀቅ ይመክራል። በ1ኛ ዮሐንስ 2፡27 የእርሱ ቅባት (የእርሱ በሰው ማደር) እውነትን ያለ አስተማሪ እንኳ ለመማር ያስችለናል። ይህን በጣም አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ እዚህ በሰፊው መመልከት ባይቻልም፥ በክርስቲያን እውቀትና ልምምድ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የመንፈሳዊ እውቀትንና ያለማወቅን ምክንያቶችም ይገልጣል።

## 3. ምሪት (አመራር)

ከመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ ጋር በቅርብ የተዛመደው ሌላ ጉዳይ ክርስቲያንን መምራቱ ነው። ምሪት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለሚኖር ሕይወት ጠቃሚና በክርስቲያናዊ ልምምድ ውስጥም ዋና ነገር ነው። ምሪት ከመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፥ ልዩነትም አለው። የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር ሥራ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል ግልጥ ማድረግ ሲሆን፥ ምሪት ግን በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ችግር በሚከሠትበት ጊዜ ያ ሰው የተማረውን እውነት በተግባር የሚገልጥበት መንገድ ነው። ምሪት ሁልጊዜ አጠቃላይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎችን አሁን ላለ ልዩ ችግር ተግባራዊ ያደርጋል። ወንጌል በዓለም ሁሉ እንዲሰበክ የእግዚአብሔር ዓላማ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ የገለጠው ቢሆንም፥ ማንኛውንም ክርስቲያን ወደ አንድ አገልግሎት የሚጠራና የሚሾም መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ለሚከሠት ዝርዝር ጉዳይ አስፈላጊውን ምሪትም ይሰጣል።

በዚህ አንጻር መጠቀስ ያለበት አስፈላጊ ነጥብ፥ ምሪት የሚሰጠው በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ለጀመሩና ለሚመላለሱ ሰዎች ብቻ መሆኑን ነው። በሮሜ 12፡1-2 መሠረት ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ያስፈልጋል፦ "ይህን ብታደርጉ እግዚአብሔር የሚደሰትበትን ፍጹምና በጎ ፈቃዱ ምን እንደሆነ ማወቅ ትችላላችሁ።" በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳ የአብርሃም ሎሌ ለዚህ ነገር ምስክርነት ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፦ "...እኔ በመንገድ ሳለሁ እግዚአብሔር ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት መራኝ"

(ዘፍጥ. 24፡27)። ምሪት በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላ ሰው የሕይወት አቅጣጫው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን የማድረግ ተግባር ነው። ምሪት እግዚአብሔር ለክርስቲያን ከሰጣቸው የቸርነት ስጦታዎች ውስጥ አንዱና አስፈላጊ ነገር መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ቀርቧል። በሮሜ 8፡14 መሠረት፥ ምሪት የእውነተኛ ደኅንነት ምልክት ነው፡- “በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።” በገላትያ 5፡18፡- “በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም” ተብሎ እንደተጻፈ ምሪት ግላዊ ካልሆነውና በዘፈቀደ ይታይ ከነበረው የእስራኤላውያን ሕግ መመዘኛ ይልቅ፥ ነጻነትን የሚሰጥ የአሁኑ ዘመን ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው።

## 4. ዋስትና

ለእውነተኛ መዳን የደኅንነት ዋስትና የግድ አስፈላጊ ባይሆንም፥ የእያንዳንዱ ክርስቲያን መብት ነው። ይሁን እንጂ ዋስትናን ማግኘት የእግዚአብሔርን ቃልና የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት በተገቢው በመረዳት ላይ ይመሠረታል። አንዳንድ ክርስቲያኖች የደኅንነት ዋስትና ያለማግኘታቸው ዋና ምክንያት ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ቅድመ ሁኔታዎችን ስላላሟሉና፥ ልባቸው ይህን ተከትሎ ለሚመጣው ሌላ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ዝግጁ አለመሆኑ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት አንዱ አስደናቂ ነገር፥ እኛ የእርሱ እርሱም የእኛ መሆኑ ነው። ስለዚህ እውነት መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክረው ነገር አለ። በተለይ ሮሜ 8፡16 እንዲህ ይላል፡- “የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።” ሌሎች ክፍሎችም ተመሳሳይ ምስክርነት ይሰጣሉ (ገላ. 4፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ 4፡13)። የሰው አእምሮ ያለመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ወደተለያዩ ማጠቃለያዎች ሊደርስ ይችላል። ሆኖም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ በኩል በተገኘው ደኅንነት ውስጥ ከአባቱ ጋር ያለውን ዘላለማዊ ግንኙነት ያረጋግጣል። የዚህ ደኅንነት ማኅተምም ነው። ብዙዎች የዋስትናን በረከት ማጣታቸውና ለጊዜውም ቢሆን ይህን በረከት መገፈፋቸው፥ በክርስቲያኑ ሕይወት ከሚታየው ሥጋዊነትና የኃጢአት ቅጣት አንዱ ነው።

## 5. አምልኮ

በአንዳንድ ክርስቲያኖች አመለካከት፥ አምልኮ ከምድራዊ አምልኮ ቤቶች፥ ከሥርዓቶች እንዲሁም ከተለመዱ ሌሎች የሕዝብ አምልኮ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ግን፥

አምልኮ የእግዚአብሔር በሚያውቁት ሰዎች መወደስ፥ በሙሉ ልብ መከበርና መመስገን ነው። ይህ የሚሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ ግንኙነት ባለው ሰው ነው። በኤፌሶን 5፡18-20 በመንፈስ ተሞሉ ከሚለው ትእዛዝ ቀጥሎ፥ ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት የምትኖር ነፍስ ፍሬ የሆነውና መንፈስ ራሱ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን ደስታን፥ ሰላምንና ዋስትናን በማምጣቱ የሚገኙት ምስጋናና አክብሮት ተጠቅሰው እናያለን። ከእግዚአብሔር ጋር በማያቋርጥ ኅብረት የምትኖር ነፍስ፥ እጅግ ክቡር በሆነው የእግዚአብሔር በረከት ውስጥ የሚገኘውን ነገር ማስተዋል ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉም ረገድ እርሱን ማመስገንና ማክበር ሥራዋ ነው። “እግዚአብሔርን ለሚወዱ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ” ለሚያውቅ ሰው ይህ የተባረከ እውነት ነው (ሮሜ 8፡28)። ምንም ዓይነት ሁኔታ በሕይወት ዘመናችን ይግጠመን፥ የምንገነዘበው ነገር የእግዚአብሔር ፍቅር ኃይልና ጥበብ ድል ነሺ መሆኑን ነው። እውነተኛ አምልኮን ለማካሄድ የሚችሉት በመንፈስ የተሞሉ ሰዎች ብቻ ናቸው።

## 6. ጸሎት

የአማኝ የጸሎት ሕይወት ከመንፈሳዊ ሕይወቱ ጋር ሊነጣጠል በማይችል አኳኋን የተዋሐደ ነው። የመንፈስ ቅዱስ የማስተማር አገልግሎት በርካታ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋዎችን ያስታውሰናል። የመንፈስ ቅዱስ ምሪት የእግዚአብሔርን የተገለጠ ፈቃድ በመለመን ረገድ በማስተዋል ለሚደረግ ጸሎት አስፈላጊ ነው። ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወትም ሆነ እድገት እስትንፋስ በመሆኑ፥ ከልምምዳዊ ቅድስና ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው። የጸሎት አስፈላጊ ክፍል በሆኑት ምስጋናና ውዳሴ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መኖሩ ግልጥ ነው። የመንፈሳዊ ሕይወት ገጽታ ሆኖ፥ ከጸሎትና ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ጋር ያልተያያዘ ነገር ጨርሶ የለም። የጸሎት ሕይወት የሚበለጽገው አማኙ በክርስቶስ ባለው መንፈሳዊ ሕይወት መጠን ነው።

በጸሎት ውስጥ ካሉት ከእነዚህ ግልጥ ጉዳዮች ሌላ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምልጃ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ይነግረናል። በሮሜ 8፡26 እንዲህ ይላል፦ “እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል።” የዚህ አገልግሎት ባሕርይ ምን እንደሆነ የሚናገር መግለጫ የለም። ከክርስቶስ ምልጃ ጋርም የተያያዘ አይደለም። ነገር ግን የዚህ ክፍል ይዘት እንደሚያመለክተው፥ የሚገባንን ያህል መጸለይ ሲያቅተን፥ መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አካል እንደመሆኑ፥

በእኛ ውስጥ ባለው ስፍራ ሆኖ ስለ እኛ ይማልዳል። አገልግሎቱ የሚያስፈልገንን ነገር በመግለጥ፣ ጸሎታችንን በመምራት ከሰው ጥበብ በላይ የሆነውን ነገር እንድንለምን እንደሚያግዘን ጥርጥር የለውም። የመንፈስ ቅዱስ አግልግሎት በሁሉም ገጽታው ሲታይ፣ አስፈላጊ ከሆነ የጸሎት ሕይወት ፈጽሞ አይለይም።

## 7. አገልግሎት

ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሰፊው በተነጋገርንበት ክፍል፣ ፍጥረታዊው ሰው እግዚአብሔርን ማገልገል እንደማይችል ሁሉ፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሉት አማኝም በስጦታዎቹ በሙላት ሊሠራባቸው የሚችለው፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲኖረው ብቻ መሆኑን ተመልክተናል። በዚህ መሠረት ለእግዚአብሔር የሚሰጥ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ፍሬያማ ይሆን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መደገፍ አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚገኝ ገደብ የሌለው በረከት፣ በክርስቶስ ተገልጦ ነበር። “በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፣ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፣ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና” (ዮሐ. 7፥38-39)። በጥሩ ሁኔታ የተገለጠው ምሳሌ ስለ ፍጥረታዊው ሰው ብቁ አለመሆን፣ ስለ አገልግሎት፣ ስለ በረከት ምንጭ፣ ስለ “ሕይወት ውኃ ወንዝ” ይናገራል። ያ የበረከት ሁሉ ምንጭ የሚፈልቀው አማኝ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ ሲሆን፣ ሊታገድ የማይገባው ነው። አማኝ በክርስቶስ የተፈጠረበትን መልካም ሥራ ሊያከናውን የሚችለው ይህ ሲሆን ብቻ ነው (ኤፌ. 2፥10)።

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት የሚሰጠው አገልግሎት፣ እንደ ሌሎቹ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤቶች እርስ በርሱ የተዛመደ ነው። አገልግሎትና ልምምዳዊ ቅድስናችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለን እውቀት፣ ምሪት፣ ዋስትና፣ አምልኮና የጸሎት ሕይወት የተለያዩ አይደሉም። ይልቁንም በአንድ ላይ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚሆን የተቀደሰ ሕይወት ይፈጥራሉ። ሰብአዊ ፍልስፍና ከሆነው ግላዊ እድገት ወይም ድርጊት ባሻገር፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ለማንኛውም ክርስቲያን የልምምድና የፍሬያማነት ምንጭ ሆኖ እንዲገኝ የሚያደርግ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል። ይህ ብቻ አይደለም፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈስን ሳያጠፋና ሳያሳዝን በተጣመረ ኅብረት በመንፈስ እንዲመላለስም ይማጸናል።